ኢፕድ
# አዲስ ዘመን
ሐሙስ
82ኛ ዓመት ቁጥር 278 ሰኔ 8 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00
ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!


ፎቶ ፡- ከጸክመንት

ዶክተር በለጠ ሞላ

# በኢትዮጵያ የዲጂታል ክፍያ ሥርዓቱ በኢኮኖሚ ዕድገት ላይ አዎንታዊ ተፅዕኖ እያሳረፈ ነው

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በፍጥነት እያደገ የመጣው የኢትዮጵያ ዲጂታል ክፍያ ሥርዓት በኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ዕድገት ላይ አዎንታዊ ተፅዕኖ እያሳረፈ መሆኑን የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር አስታወቀ።ሰባተኛው የአፍሪካ ኢኖቬሽንና ዲጂታል ጉባዔ "ዲጂታል አፍሪካ" በሚል መሪ ሐሳብ ከትናንት ጀምሮ መካሄድ ጀምሯል።

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ዶክተር በለጠ ሞላ በጉባዔው ላይ እንደገለጹት፤ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በኢትዮጵያ የዲጂታል ክፍያ ሥርዓት እያደገ ነው።በዚህም ባለፉት ዘጠኝ ወራት ከፍተኛ ብር በዲጂታል ክፍያ ማስተላለፍ በመቻሉ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ላይ አዎንታዊ ተፅዕኖ አሳርፏል።

የዲጂታል ክፍያ ሥርዓት ዕድገቱ የሥራ ዕድል ፈጠራን እያሳደገና የአገልግሎትና አቅርቦት ዘርፉን እያሳለጠ መሆኑን የገለጹት ሚኒስትሩ፤ በቴሌኮም ዘርፉ ተግዳሮቶች ቢኖሩም ወሳኝ የሆነ ዕድገትን እያሳየ ስለመሆኑ ገልጸዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለፃ፤ መንግሥት የአይሲቲ ዘርፉን ለማሳደግ ቁርጠኛ ነው።ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የኢትዮጵያ መንግሥት ለኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ዘርፉ ትልቅ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ይገኛል። ከሚስተዋሉ

በኢትዮጵያ የዲጂታል... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# አገራዊ ምክክሩ የተሳካ እንዲሆን ሕዝብን ማዕከል ያደረገ ውይይት ይካሄዳል

**መክሊት ወንድወሰን**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ የሚደረገው አገራዊ ምክክር ስኬታማ እንዲሆን ሕዝብን ማዕከል ያደረገ ውይይት እንደሚካሄድ የአገራዊ የምክክር ኮሚሽን ገለጸ፡፡ የሌሎች አገራት የስኬት ተሞክሮዎች ተለይተው በአገራችን ተግባራዊ ለማድረግ እየተሠራ መሆኑም ተጠቁሟል፡፡

የኢትዮጵያ የምክክር ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶክተር ዮናስ አዳዬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ባለቤትነት፣ ግልጽነት እና አካታችነት በዓለም አቀፍ ደረጃ ለአገራዊ ምክክሮች ያላቸው ሚና ወሳኝ ናቸው፡፡ በኢትዮጵያም ለሚካሄደው ምክክር ስኬታማነት ሕዝብ


ዶክተር ዮናስ አዳዬ

የውይይት ማዕከል እንዲሆን ይደረጋል፡፡

በዓለማቀፍ ተሞክሮዎች ደረጃ እንደ ኢትዮጵያ ሁሉ ደቡብ አፍሪካ፤ ቱኒዚያ እንዲሁም በከፊል ኬኒያ ምክክሩን ከታች ወደ ላይ የጀመሩ ሀገራት መሆናቸውን አውስተው፤ የሦስቱም አገራት ምክክር የተሳካው ሕዝቡን ባለቤት በማድረጋቸው መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡


በየመን እና በጓቲማላ የተደረገው ምክክር ላይ በአጀንዳ መረጣና በፋይናንስ የውጭ ጣልቃ ገብነት በመኖሩ ምክክሩ ሳይሳካ መቅረቱን እንደ አብነት አንስተው፤ በኢትዮጵያ እየተካሄደ የሚገኘው አገራዊ ምክክር ስኬታማ እንዲሆን ሕዝብን መሠረት ማድረግ እና በአጀንዳ መረጣና በፋይናንስ የውጭ ጣልቃ ገብነት ላይ ጥንቃቄ ሊደረግ እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡

አገራዊ ምክክሩ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል










# የኢፕድ ሥልጠና ማዕከል ተቋማት የተሻለ አፈፃፀም እንዲኖራቸው እያስቻለ ነው

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- የኢፕድ የሥልጠና ማዕከል አመራሮችና ሠራተኞች የነበራቸውን ችሎታ በማጎልበት ተቋማቱ የተሻለ አፈፃፀም እንዲኖራቸው ከፍተኛ ሥራ እየሠራ መሆኑ ተገለጸ።

የኢፕድ ሥልጠና.. ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## "የግል ትምህርት ቤቶች ባደረጉት ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ ሌላ አማራጭ ለመፈለግ ተገደናል"

-የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ወላጆች

## "ያልተስማሙትን ትምህርት ቤቶችና ወላጆች ለማስማማት እየሠራን ቢሆንም ዋጋ ትመና ውስጥ ግን አንገባም"

-የትምህርትና ሥልጠና ጥራት ቁጥጥር ባለሥልጣን

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- ለ2016 የትምህርት ዘመን ምዝገባ የግል ትምህርት ቤቶች ባደረጉት ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ መጨነቃቸውንና ለልጆቻቸው ሌላ የትምህርት ቤት አማራጮችን እያፈላለጉ መሆኑን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አስተያየታቸውን የሰጡ የተማሪ ወላጆች ገለጹ።

የትምህርትና ሥልጠና ጥራት ቁጥጥር ባለሥልጣን በበኩሉ ያልተስማሙትን ትምህርት ቤቶችና ወላጆች ለማስማማት እየሠራ እንደሆነ ገልፆ፤ ዋጋ ትመና ውስጥ ግን አንገባም ብሏል፡፡

ልጆቻቸውን በካሪዝማ አካዳሚ የሚያስተምሩት አቶ ሙሳ ሰይድ እንደተናገሩት፤ የግል ትምህርት ቤቶች ከወላጆች ጋር በመስማማት የዋጋ ጭማሪ ማድረግ እንደሚችሉ በሕግ ተቀምጧል። ትምህርት ቤቱ የኑሮ ውድነትን አስመልክቶ ልጆቼ የሚማሩበት ትምህርት ቤት እጥፍ ጭማሪ ለማድረግ ወላጆችን ሰብስቦ አነጋግሯል።

በስብሰባው የዋጋ ጭማሪው ከፍተኛ በመሆኑ ወላጆች ቅሬታ አሰምተዋል። በዚህም የዋጋ ጭማሪው ከእጥፍ ወደ 75 በመቶ ቢቀንስም አጠቃላይ ጭማሪው ግን አሁንም የሚቻል አይደለም። ምክንያቱም ቋሚ ደመወዝ ያለኝ በመሆኑ ጭማሪውን መቋቋም

"የግል ትምህርት ቤቶች... ወደ ገጽ 4 ዞሯል





አኔ ናባሳ

# ዑጋንዳ ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን የቱሪዝም ዘርፍ ግንኙነት አጠናክራ ትቀጥላለች

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- ኡጋንዳ ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን የቱሪዝም ዘርፍ ግንኙነት አጠናክራ እንደምትቀጥል በኢትዮጵያ የዑጋንዳ ኤምባሲ አስታወቀ፡፡

የዑጋንዳ ቱሪዝም ሚኒስቴር በኢትዮጵያ ለሚገኙ የሚዲያ አካላት በአገሪቱ ስለሚገኙ የቱሪስት መዳረሻዎች በትላንትናው ዕለት የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ አካሂዷል፡፡

በኢትዮጵያ የዑጋንዳ ኤምባሲ የሁለትዮሽ ትብብር ዴስክ ኦፊሰር አኔ ናባሳ እንደተናገሩት፤ ዑጋንዳና ኢትዮጵያ ለረጅም ዘመናት የቆየ ግንኙነት አላቸው፡፡ በተለይ ዑጋንዳ ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን የቱሪዝም ዘርፍ ግንኙነት አጠናክራ ትቀጥላለች፡፡

እንደ አኔ ገለጻ፤ የኢትዮጵያና የዑጋንዳ የሁለትዮሽ ትብብር በማደግ ላይ ይገኛል፡፡ በዚህም በቱሪዝም፣ ኢንቨስትመንት፣ ንግድ፣ ባሕል፣ ትምህርት እና ሌሎችም ያለው ትስስር ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መጥቷል።

ባለፉት ዓመታት በአገራቱ መካከል ሁሉን አቀፍ የጋራ ልማትን ለማረጋገጥ በርካታ የትብብር መስኮች ተግባራዊ ተደርገዋል ያሉት ኦፊሰሯ፤ ዑጋንዳ የአፍሪካ ኅብረት ከተመሠረተ ጀምሮ ከኢትዮጵያ ጋር ግንኙነት አላት ብለዋል፡፡

አገራቱ በጋራ ከሚሠሩባቸው የተለያዩ ጉዳዮች መካከል የጋራ ቋሚ የሚኒስትሮች ኮሚሽን አንዱ መሆኑን ጠቅሰው፤ በተለይም በንግድ፣ በኢንቨስትመንት፣ በባሕል፣ በስፖርት፣ በጤና፣ በትምህርትና በኢሚግሬሽን ዘርፎች በጋራ እንደሚሠሩ ገልጸዋል።

ኮሚሽኑ ኢትዮጵያና ዑጋንዳን በተለያዩ ዘርፎች የሚያገናኝ ነው ያሉት ኦፊሰሯ፤ አገራቱ በማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ሌሎች ጉዳዮች ላይ ትብብር የሚፈጥር መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ኢትዮጵያና ዑጋንዳ በቱሪዝም ማስተዋወቅ ላይ ስምምነት እንዳላቸው በመግለጽ የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሐ ግብሩ በሁለቱ አገራት መካከል ያለው የቱሪዝም ልማት ለማስተዋወቅ የተፈረመውን ስምምነት የማስፈጸሚያ አካል መሆኑን ገልጸዋል።

አገራቱ ዜጎች የቱሪስት መዳረሻዎችን እንዲጎበኙና የእርስ በእርስ ግንኙነት እንዲኖራቸው በጋራ ለመሥራት አስፈላጊ መሆኑን ተናግረዋል።

በሌላ በኩል የኢትዮጵያ አየር መንገድ በቀን ሦስት ጊዜ ወደ ዑጋንዳ የሚያደርገው የቀጥታ በረራ ለዘርፉ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያደርጋል ብለዋል፡፡

በተጨማሪም "በቀን ሦስት በረራዎች ወደ ዑጋንዳና ሦስት በየቀኑ ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡ ስድስት በረራዎች መኖራቸውን ጠቅሰው የአገራቱን የቱሪዝም ዘርፍ በማስተዋወቅ የሚደግፍ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

በመድረኩ የዑጋንዳ ቱሪዝም ሚኒስቴር በኢትዮጵያ ለሚገኙ አስጎብኚ አካላት በአገሪቱ በሚገኙ የቱሪስት መዳረሻዎች ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ መስጠቱ በመድረኩ ተገልጿል፡፡

# በጢዮ ወረዳ በሰብል ከሚሸፈነው መሬት 15 በመቶው በተፈጥሮ ማዳበሪያ ይለማል

**ውብሸት ሰንደቁ**



ጢዮ፡- በኦሮሚያ ክልል፣ አርሲ ዞን ጢዮ ወረዳ ዘንድሮ በሰብል ከሚሸፈነው 25 ሺህ ሄክታር መሬት 15 በመቶው በተፈጥሮ ማዳበሪያ ለማልማት መታቀዱን የጢዮ ወረዳ ግብርና ጽሕፈት ቤት አስታወቀ፡፡

የጢዮ ግብርና ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ሐጂ ቶላ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በወረዳው የኮምፖስት ዝግጅት በዘመናዊ መንገድ ተጀምሮ እየተሠራ ነው፡፡ ኮምፖስቱ በሚራቡ ትሎች አማካኝነት በቶሎ እንዲብላላ እና በፍጥነት ለታለመለት ግብ እንዲደርስ ይሆናል፡፡

የከብቶችን ፅዳጅ በመሰብሰብ ከሚዘጋጀው የተፈጥሮ ማዳበሪያ የመሬት ለምነትን ለመጨመር ከመርዳቱም ባሻገር አርሶ አደሩ የሚያወጣውን አላስፈላጊ ወጪ እንዲቀንስ ያደርጋል ያሉት አቶ ሐጂ፤ በዘንድሮው ዓመት በሰብል ለመሸፈን ከታቀደው 25 ሺህ ሄክታር መሬት 15 በመቶ ያህሉ በተፈጥሮ ማዳበሪያ ብቻ የሚዘራ ይሆናል ብለዋል፡፡

አርሶ አደሩ ለኬሚካል ማዳበሪያ የሚያወጣውን ወጪ ለማስቀረት በችግኝ ጣቢያዎች እና በአንዳንድ አካባቢዎች የሚመረተው ብቻውን በቂ አይደለም ያሉት የግብርና ጽሕፈት ቤት ኃላፊው፤ ገበሬውን አነሳስቶ ወደ መስመር እንዲገባ ግን ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል ብለዋል፡፡ የተፈጥሮ ማዳበሪያ ለመጀመሪያ ጊዜ በምንጠቀምበት ጊዜ ፍጅታው ከፍ ያለ ቢሆንም ከዓመት ዓመት ግን እየቀነሰ ይሄዳል ሲሉም አስረድተዋል፡፡

የኦሮሚያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ተሾመ ቦጋለ ጉዳዩን አስመልክቶ በሰጡት ማብራሪያ፤ የተፈጥሮ ማዳበሪያ አብዛኛውን በምርምር ደረጃ ላይ ያለ እና በሚገባው ልክ ወደ አርሶ አደሩ ያልተስፋፋ ምርት ነው ብለዋል፡፡

በየገበሬ ማኅበራቱ እና በየችግኝ ጣቢያው መገኘት ያለበት ምርት መሆኑን በመጥቀስ፤ ያን ያህል የሰፋ አይሁን እንጂ በአርሲ ዞን ወረዳዎች ግን በገበሬ ማኅበራት እና በችግኝ ጣቢያዎች በጥሩ ሁኔታ እየተሠራበት ይገኛል ሲሉ ጠቅሰዋል፡፡

የተፈጥሮ ማዳበሪያውን እያዘጋጁ የሚሸጡ የችግኝ ጣቢያዎች እና አንዳንድ የገበሬ ማኅበራትም ወደ ሥራ መግባታቸው አበረታች መሆኑን በመጥቀስ፤ አንድ ኩንታል የተፈጥሮ ማዳበሪያ ከአንድ ሺህ ብር እስከ አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር እየተሸጠ ስለመሆኑ ማረጋገጣቸውን ተናግረዋል፡፡ ይህ ሊበረታታ የሚገባው እና የተለየ ሁኔታ ነውም ብለዋል፡፡

በሌላ በኩል የገበሬ ማኅበራት እና የችግኝ ማልሚያ ጣቢያዎች ምርምር ላይ ተወስነው የቀሩ የግብርና ግብዓቶችን ወደ አርሶ አደሩ ለማድረስ እንደ አንድ ዋነኛ መሣሪያ ሆነው እያገለገሉ ብለው፤ ይህ የግብርና ምርት ዕድገት ላይ አዎንታዊ ተፅዕኖ የሚያመጣ ከመሆኑም በላይ አገሪቱ ከውጭ የምታስገባው የኬሚካል ማዳበሪያ እንዲቀንስ የራሱን አስተዋፅዖ ያደርጋል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ለወደፊቱ ከችግኝ ጣቢያዎች ከመግዛት አልፎ አርሶ አደሩ በራሱ ጓሮ የተፈጥሮ ማዳበሪያ እንዲያዘጋጅ የሚሠራ መሆኑንም ተናግረዋል፡፡

# የሲሚንቶ አቅርቦት ችግሮችን ለመፍታት እየተሠራ ነው

**ኃይሉ ሣሕለድንግል**



አዳማ ፡- በሲሚንቶ አቅርቦት ላይ ለዛሬ ብቻ ሳይሆን ለነገም ጭምር መሠራት እንዳለበት የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስትር ዴኤታው ኢንጂነር ወንድሙ ሴታ አስታወቁ፡፡

ኢንጂነር ወንድሙ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ የኮንስትራክሽን ዘርፉ አንዱ ማነቆ የግንባታ አቅርቦት ችግር ነው፡፡ ሀገሪቱ አሁን ባለችበት የኢኮኖሚ ዕድገት የሲሚንቶ አቅርቦት ችግር ዋነኛ ማነቆ ሆኗል፡፡

የልማት ግቦቻችን ሁሉ የሚሳኩት በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ በኩል ነው ካልን በኢንዱስትሪው ውስጥ ያሉትን ማነቆዎች በሙሉ መፍታት ይገባል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፣ ከማነቆዎቹ አንዱ የሲሚንቶ አቅርቦት ችግር መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

አሁን ባለንበት የኢኮኖሚ እድገት ደረጃ 50ና 60 ሚሊዮን ቶን አካባቢ ሲሚንቶ የማምረት አቅም ላይ መድረስ ነበረብን ያሉት ኢንጂነር ወንድሙ፤ የዛሬ አምስትና ስድስት ዓመት ሲሚንቶ በማምረት የደረስንበት አቅም በወቅቱ ለደረስንበት የኢኮኖሚ አቅምና ፕሮጀክቶች በቂ ነበር ብለዋል፡፡

በሲሚንቶ አቅርቦት ላይ ለዛሬ ብቻ ሳይሆን ለነገም ጭምር መሠራት እንዳለበት ሚኒስትር ዴኤታው ጠቁመው፤ ለነገ መሠራት የነበረበት ሥራ የዛሬ አምስትና ስድስት ዓመት አለመሠራቱ ሀገሪቱ ስር የሰደደ የሲሚንቶ አቅርቦት እጥረት ውስጥ እንድትገባ ማድረጉን አስታውቀዋል፡፡ ይህን ታሳቢ አድርገን ያንን የሚያካክስ ሥራ መሥራት ካልቻልን በስተቀር ዘርፉ እንደታነቀ ይቆያል ሲሉም አሳስበዋል፡፡

ሚኒስትር ዴኤታው እንዳሉት፤ የሲሚንቶ አቅርቦት ችግር በመኖሩ ምክንያት የሥራ እድል ፈጠራውም እየተጎዳ ነው፤ የመንግሥት የግንባታ ፕሮጀክቶችም እየተጓተቱ ናቸው፡፡ ችግሩ ግንባታዎቹ ቢሳኩ አብረው ሊመጡ በሚገባቸው ቱሩፋቶች ላይም አሉታዊ ተፅዕኖ እያሳረፈ ይገኛል፡፡ በዚህ የግብዓት አቅርቦት ችግር ምክንያት ፕሮጀክቶች በተጓተቱ ቁጥር የሥራ ተቋራጮች አቅም ይዳከማል፤ የሥራ ዕድል ፈጠራው አብሮ ችግር ውስጥ ይገባል፡፡ በአጠቃላይ ዘርፉ ችግር ውስጥ ይገባል፡፡ ይህን ችግር መፍታት አለብን ሲሉ አስታውቀዋል፡፡

አሁን ባለው ሁኔታ የግብዓት አቅርቦትና የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት ችግር መኖሩን ተከትሎ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ወደ መቀዛቀዝ እየሄደ መሆኑንም ጠቅሰው፣ ኢንዱስትሪውን ተነቃቅቶ ወደ ነበረበት ሁኔታ መመለስ እንደሚገባም ነው ያመለከቱት፡፡ የግብዓትና የውጭ ምንዛሪ እጥረት የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው እንዳይንቀሳቀስና ችግሮቹን እንዳይፈታ ቀፍድዶ እንደያዘውም አስታውቀዋል፡፡

ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው አዲስ ፖሊሲ ለማዘጋጀት በቀረቡ ጥናቶች ላይ ለመወያየትና ግብዓት ለማሰባሰብ ሰሞኑን በአዳማ የተካሄደው የውይይት መድረክ የተዘጋጀውም ከግብዓት አቅርቦት፣ ከተቋራጮች ተወዳዳሪነት፣ ለኢንዱስትሪው ከሚያስፈልገው የፋይናንስ አቅርቦት አኳያ ያሉትን ችግሮች በደንብ ተወያይተን መፍታት ከቻልን ኢንዱስትሪው የነበረበትን ሁኔታ ይዞ መቀጠል የሚችልበት ዕድል አለ ተብሎ ስለታመነ ነው ብለዋል፡፡

በመድረኩ በቀረበው ጥናት በዘርፉ አለ የተባለው ዕድል በመጥቀስ ሚኒስትር ዴኤታው እንዳብራሩት፤ በአስር ዓመቱ እቅድ ከ102 ሺ ኪሎ ሜትር በላይ የአዳዲስ መንገዶች ግንባታ፣ ከ28 ሺ ኪሎ ሜትር በላይ የመንገዶችን ደረጃ የማሳደግና ማጠናከር ሥራ፣ ከ3 ሺ ኪሎ ሜትር በላይ የባቡር መስመር ግንባታ፣ ከ4 ሚሊዮን በላይ ቤቶች ግንባታ እና ሌሎችም ግንባታዎች የኮንስትራክሽን ዘርፉን የሚፈልጉ ናቸው፡፡

ይህንን እድል በመጠቀም የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን ችግር መፍታት እንደሚያስፈልግ ኢንጂነር ወንድሙ ጠቁመዋል፡፡ በእነዚህ ዕድሎች የተመለከቱ ግቦች ያለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ተወዳዳሪነትና ብቃት እንደማይሳኩም አስታውቀው፤ የዘርፉን ችግር መፍታት ለእነዚህ ግቦች መሳካት አስተዋፅዖ እንደሚያደርግ አመልክተዋል፡፡ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው በዘላቂነት ተወዳዳሪ ሆኖ አቅሙም ተገንብቶ ለሚቀጥሉት የልማት ግቦቻችን አቅም የሚሆንበትን ምቹ ሁኔታ መሥራት ይኖርብናልም ብለዋል፡፡

# መንግሥት የሥራ ዕድል ከመፍጠር በዘለለ ሥራ ፈጣሪ ዜጋ ለመገንባት እየሠራ ነው

## -አገር አቀፍ የነጋዴ ሴቶች ኤክስፖ ተከፍቷል

**ዳግማዊት አበበ**


ፎቶ-አጋፔ ገዮን

ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬ ሃገር አቀፍ የነጋዴ ሴቶች ኤክስፖን ሲከፍቱ

አዲስ አበባ፡- መንግሥት ቋሚ የሥራ እድል ከመፍጠር በዘለለ ሥራ ፈጣሪ ዜጋ ለመገንባት እየሠራ ነው ሲል የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳዮች ሚኒስቴር አስታወቀ። አገር አቀፍ የነጋዴ ሴቶች ኤክስፖ በትናንትናው እለት ተከፍቷል።

ኤክስፖው ከሰኔ ሰባት እስከ ዘጠኝ የሚቆይ ሲሆን በመክፈቻ መርሐግብሩ ላይም የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳዮች ሚኒስትር ኤርጎጌ ተስፋዬ (ዶክተር )ን ጨምሮ ከፕላንና ልማት ሚኒስቴር፣ ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የተወከሉ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች እንዲሁም ባለድርሻ አካላት እና አምራቾች ተገኝተዋል።

ኤክስፖውን በይፋ የከፈቱት የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ኤርጎጌ ተስፋዬ (ዶክተር) እንደገለጹት፤ መንግሥት ለሥራ ፈላጊ ዜጎች ቋሚ የሥራ ዕድል ከመፍጠርም በዘለለ ሥራ ፈጣሪ ሆነው ራሳቸውን እንዲችሉ ለማድረግ እየሠራ ነው። ለዚህም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎችን በመቅረጽ ምቹ ሁኔታዎችን እየፈጠረ ይገኛል።

እንደ ሚኒስትሯ ገለጻ፤ በአምራች ዘርፉ የሴቶችን ተሳትፎ ለማረጋገጥ እና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚ ለማድረግ እየተሠራ ነው። ይህ የነጋዴ ሴቶች ኤክስፖም መንግሥት ለዘርፉ ትኩረት መስጠቱን ማሳያ ነው።

ኤክስፖው የሴት ሥራ ፈጣሪዎች፣ አምራቾችና ንግድ ተቋማት መሪዎች በሥራቸው ዙሪያ በመመካከርም ጭምር ልምድ የሚለዋወጡበት ነው ያሉት ሚኒስትሯ በዋናነትም በሴት ሥራ ፈጣሪዎች የሚመረቱ የተለያዩ ምርቶች የሚተዋወቁበት እና የገበያ ትስስር የሚፈጠርበት ነው ሲሉ ገልጸዋል።

የማሌሳ ኢቨንትስ ሥራ አስፈጻሚ ወጣት ሰላማዊት ደጀኔ በበኩሏ እንደተናገረችው፤ ኤክስፖው የሴቶች የሥራ ፈጠራ፣ አምራችነት፣ የገበያ ትስስር፣ ተወዳዳሪነት፣ ተሳታፊነትና ተጠቃሚነትን የሚያሰፋ ነው።

በተለያዩ የንግድ ዘርፎች የተሠማሩ ሴት ሥራ ፈጣሪዎች፣ አምራቾች እና የንግድ ተቋም መሪዎች ምርትና አገልግሎታቸውን ለ35 ሺህ በላይ ጐብኝዎች የሚያስተዋውቁበት መድረክ እንደሆነም ጠቁማለች።

በስካይ ላይት ሆቴል የተዘጋጀው የነጋዴ ሴቶች ኤክስፖ ለሦስት ቀናት የሚቆይ ሲሆን ከ100 በላይ አምራቾችና ድርጅቶች ምርትና አገልግሎታቸውን እያስተዋወቁበት ይገኛሉ።

ኤክስፖው የተዘጋጀው በሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እና በማሌሳ ኢቨንትስ ጥምረት መሆኑ ታውቋል።



ቋሚ ኮሚቴው ግምገማ ሲያካሂድ

# ኤጀንሲው የተሰበሰበው ገንዘብ ለታለመለት ዓላማ መዋሉን እንዲቆጣጠር ቋሚ ኮሚቴው አሳሰበ

**ማሕሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ ፡- የጤና መድሕን አገልግሎት ኤጀንሲ ከአባላት የተሰበሰበው ገንዘብ በትክክል ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እንዳለበት የመንግሥት ወጪ እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አሳሰበ፡፡

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ወጪ እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በትናንትናው እለት የጤና መድሕን ተደራሽነትና የገቢ አሰባሰብ አፈጻጸምን በተመለከተ የ2013/2014 በጀት ዓመት የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት ላይ ውይይት አድርጓል፡፡

የቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ ክርስቲያን ታደለ በውይይቱ ላይ እንደገለጹት፤ የማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድሕን ተቋማት ከአባላት የሚሰበስቡትን ገንዘብ በወቅቱ ስለመሰብሰቡና የዓመታዊ ድጎማ በጀት ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ የጤና መድሕን አገልግሎት ኤጀንሲ ዋና ተግባሩ መሆን አለበት፡፡ ለዚህም ተቋሙ በአዋጅ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የመከታተልና የመቆጣጠር ሥራ በትኩረት መሠራት ይጠበቅበታል፡፡

ኤጀንሲው በወረዳ የተበታተኑ የጤና መድሕን ቋቶችን በማሰባሰብ አንድ ጠንካራ ቋት የመፍጠር አሠራርን መዘርጋት እንዳለበት አመልክተው፤ የበለጠ ተደራሽነትንና ፍትሐዊነትን በማረጋገጥ ኅብረተሰቡ ከአገልግሎቱ ተጠቃሚ የሚሆንበትን መንገድ መፍጠር እንደሚኖርበት ተናግረዋል፡፡

አቶ ክርስቲያን፤ የጤና መድሕን ደንበኞች አያያዝ ሁኔታና የመድኃኒት አቅርቦት ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችን ለመፍታት ጠንካራ የቁጥጥር ሥራ መሥራት አለበት ብለዋል፡፡

የፌደራል ዋና ኦዲት መሥሪያ ቤት ዋና ኦዲተር መሠረት ዳምጤ በበኩላቸው፤ ከገቢ አሰባበስና አፈጻጸም አንጻር ጠንካራ የአሠራር ሥርዓቶችን በመዘርጋት በትክክል በማስረጃ የተደገፈ አሠራርና ተጠያቂነት እንዲኖር የማድረግ ሥራ ይበልጥ መሠራት አለበት ብለዋል፡፡

የተገኙ የኦዲት ክፍተቶችን አስቸኳይ ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ፣ ተመላሽ የሚሆኑትም ገንዘብ ተመላሽ እንዲደረጉ ክትትል የማድረግና የመፈጸም ጉዳይ ከክልል ኃላፊነት ባለፈ ዘላቂ የፋይናንስ ተቋም ለመፍጠር መሥራት ያስፈልጋል፡፡ የሚሰጠውንም አገልግሎት ዘመናዊ በሆነ መንገድ ቀልጣፋ ማድረግ እንደሚጠበቅበትም ነው የተናገሩት፡፡

በውይይት መድረኩ ላይ ማብራሪያና ምላሽ የሰጡት የጤና ሚኒስትር ዶክተር ሊያ ታደሰ ፤በጤና መድሕን አባላት የሚሰበሰብ ገንዘብ በወቅቱ ስለመሰብሰቡ ክትትል ፤የማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድሕን ምዝገባ እና መዋጮ አሰባሰብ ተግባር በዋናነት በክልል ባሉ መዋቅሮች የሚሠራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ለኅብረተሰቡ በማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድሕን ዙሪያ ግንዛቤ እንዲኖረው ሰፊ ሥራዎች ተሠርተዋል ያሉት ሚኒስትሯ፤ ኤጀንሲው አገልግሎቱንና የመድኃኒት አቅርቦትን ተደራሽ ለማድረግ እንደሚሠራም ተናግረዋል፡፡

የኅብረተሰቡን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ከጤና አገልግሎት አቅርቦት አንጻር የሚነሱ ተግዳሮቶችን እንዲያግዝ በተደረገ ዳሰሳ ጥናትም ከሁለት ሺህ በላይ ጤና ተቋማት ላይ የተስተዋሉ ክፍተቶች እንዲስተካከሉ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ግብረ መልስ መሰጠቱን ጠቁመዋል፡፡

የኢትዮጵያ ጤና መድሕን አገልግሎት አማካሪ አቶ አብዱልጀሊል ረሺድ በበኩላቸው በሰጡት ማብራሪያ ከአባላት የምዝገባ እና የመዋጮ ገንዘብ የመሰብሰብ ሂደት በክልል ደረጃ በተፈቀደና በተረጋገጠ ደረሰኝ መሠረት እየተሠራ ነው፡፡ ለዚህም የአባላት ምዝገባ በተጠናቀቀ ወቅት ባሉት ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች መሠረት በየወረዳው በተቀናጀ መንገድ የተሰበሰበውን ገንዘብ በባንክ ደረሰኝ በማረጋገጥ እየተሠራ ነው፡፡ ይህንንም ለማጠናከር በስፋት ይሠራል ብለዋል፡፡ ቋሚ ኮሚቴው ኢጀንሲው የኦዲት ማሻሻያ መርሐ ግብሩን በአስር ቀናት ውስጥ አጠናቆ እንዲልክ አቅጣጫ አስቀምጧል፡፡

# በክልሉ ከወርቅና ኦፓል ገቢ 8 ሚሊዮን ዶላር የሚጠጋ ገቢ ተገኝቷል

**ሄለን ወንድምነው**



አቶ ታምራት ደምሴ





አዲስ አበባ፡- በበጀት ዓመቱ ዘጠኝ ወራት ከወርቅና ጥሬ ኦፓል ማዕድናት ከሰባት ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ መገኘቱን የአማራ ክልል ማዕድን ሀብት ልማት ቢሮ አስታወቀ፡፡

የአማራ ክልል ማዕድን ሃብት ልማት ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ ታምራት ደምሴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በበጀት ዓመቱ ለውጪ ገበያ ከቀረቡት የወርቅና ጥሬ ኦፓል ማዕድናት 15 ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ዶላር ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዷል፡፡

አቶ ታምራት እንዳመለከቱት፤ በዘጠኝ ወሩ ሰባት ሚሊዮን 914 ሺህ 299 ዶላር ገቢ ተገኝቷል፤ በቀጣይ ጊዜያት የዕቅዱን አፈጻጸም ለማሳካት በትኩረት እየተሠራ ይገኛል።

በበጀት ዓመቱ ዘጠኝ ወራት 33 ሺህ 569 ነጥብ 07 ኪሎ ግራም ያልተዋበ እና 456 ነጥብ 65 ኪሎ ግራም የተዋበ ኦፓል ለውጭ ገበያ ቀርቦ አንድ ሚሊዮን 988 ሺህ 399 ዶላር ገቢ ማግኘት መቻሉን አስታውቀዋል፡፡

በወርቅ ወጪ ንግድ 84 ነጥብ 980 ኪሎ ግራም ወርቅ ቀርቦ አምስት ሚሊዮን 925 ሺህ 900 ዶላር ገቢ ተገኝቷል ብለዋል፡፡

የሀገር ውስጥ የማዕድናት ገቢን ለማሳደግ በተከናወኑ ሥራዎች 75 ሚሊዮን 300 ሺህ ብር ከሀገር ውስጥ ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ 42 ሚሊዮን 57 ሺህ 78 ብር መሰብሰቡን አስታውቀዋል፡፡

ከውጭ የሚገቡ የማዕድን ውጤቶችን በአገር ውስጥ ለመተካት የሚረዱ ጅብሰም፣ ላይም ስቶን፣ የሸክላ አፈር፣ ሲሊክ ሳንድ፣ ቤንቶናይት እና ሌሎች ማዕድናትን 313 ሺህ 460 ቶን ማምረት ተችሏል ሲሉ አስታውቀዋል፡፡

የአማራ ክልል የበርካታ ማዕድናት መገኛ ነው ያሉት አቶ ታምራት፤ ክልሉ ያለውን ማዕድን በይበልጥ በማልማት በአገር አቀፍ ደረጃ ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችል ጥረት እየተከናወነ ይገኛል ብለዋል።

አቶ ታምራት እንዳመለከቱት፤ ከክልሉ የማዕድን ሃብት ይበልጥ ተጠቃሚ ለመሆን የማዕድን ላብራቶሪ ማቋቋም፣ ሰፊ የሥነ ምድር ጥናት፤ የማዕድናትን ክምችት መጠን እና የጥራት ደረጃ መለየትና ለባለሀብቶች ማስተላለፍ ያስፈልጋል።

ዘርፉን በአዳዲስ የቴክኖሎጂና ግብዓት መደገፍ ዋነኛ የትኩረት አቅጣጫ በመሆኑ ክልሉ እየሠራበት ይገኛል ሲሉ ተናግረዋል።

የክልሉን የማዕድን ሀብት በማስተዋወቅ ሀገሪቱን ተጠቃሚ ለማድረግ በሚሠራው ሥራ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ይበልጥ ተሳታፊ እንዲሆኑ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# በክልሉ አንድ አርሶ አደር 300 የፍራፍሬ ችግኞች እንዲኖሩት እየተሠራ ነው

**ዓመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- በክልሉ በቀጣዮቹ ሦስት ዓመታት አንድ አርሶ አደር 300 የፍራፍሬ ችግኞች እንዲኖሩት እየተሠራ መሆኑን የደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የደንና አካባቢ ጥበቃ ልማት ቢሮ አስታወቀ፡፡ በክልሉ በሚገኙ ከተሞች የመግቢያና መውጫ መንገዶች ላይ የፍራፍሬ ችግኞች እንደሚተከሉም ተመላክቷል፡፡

የክልሉ የደንና አካባቢ ጥበቃ ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ ዳንኤል ዳምጠው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በዘንድሮ የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር በክልሉ በሚገኙት የዞን እና የወረዳ ከተማዎች ላይ “ከተማችንን እናልማ” በሚል መሪ ሃሳብ የፍራፍሬ ችግኝ ለመትከል እየተሠራ ይገኛል፡፡

በዚህም ክልሉ በቀጣዮቹ ሦስት ዓመታት አንድ አርሶ አደር 300 የፍራፍሬ ችግኞች እንዲኖሩት እየተሠራ መሆኑን እና ከነዚህ ውስጥ 100 የተለያዩ የፍራፍሬ ችግኞች ቀሪዎቹ 200 ደግሞ የሙዝ ችግኞች መሆናቸውን ጠቁመዋል፡፡

በክልሉ በሚገኙት ከተሞች የመግቢያና መውጫ መንገዶች ላይም አምስት ኪሎ ሜትር የሚረዝም ቦታ ድረስ የፍራፍሬ ችግኞችን ለመትከል እየተሠራ እንደሚገኝ አስታውቀዋል፡፡

አቮካዶ፣ ሙዝ፣ ፐሪም፣ አፐል እና ፓፓያ የፍራፍሬ ችግኞች ለተከላ ተዘጋጅተዋል ያሉት አቶ ዳንኤል፤ የአከባቢውን ሥነምሕዳር መሠረት ባደረገ መልኩ እንደሚተከሉ አመላክተዋል፡፡

የፍራፍሬ ችግኞች ካላቸው ዘርፈ ብዙ ጥቅም አንጻር በክልሉ የሚገኙ አርሶ አደሮች የፍራፍሬ ችግኝ እንዲተክሉ በትኩረት ይሠራል ያሉት አቶ ዳንኤል፤ አንድ አርሶ አደር በሦስት ዓመት ውስጥ አንድ መቶ የፍራፍሬ ችግኞችን እንዲተክል የማድረግ ሥራ እንደሚሠራ ጠቁመዋል፡፡

በዚህም አርሶ አደሮቹ በመጀመሪያው ዓመት 30፣ በሁለተኛው 40 እና በሦስተኛው 30 የፍራፍሬ ችግኞችን እንዲተክሉ የማድረግ ሥራ በትኩረት ይሠራል ብለዋል፡፡

በክልሉ የሙዝ ተክል በስፋት የሚለማ እንደሆነ ገልጸው፤ አርሶ አደሮች ካላቸው ተጨማሪ እንዲያለሙ ለማድረግ ዕቅድ መያዙን አብራርተዋል፡፡ አንድ አርሶ አደር በሦስት ዓመት 200 የሙዝ ተክል እንዲያለማ ይደረጋል ያሉት ኃላፊው በዚህም በመጀመሪያው ዓመት 60፣ በሁለተኛው 80 እና በሦስተኛው 60 የሙዝ ችግኞችን ይተክላል ብለዋል፡፡

በተጨማሪም በዘንድሮ የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር ከአንድ ቢሊዮን በላይ ችግኝ ለመትከል ዝግጅት የተደረገ ሲሆን፤ የሚተከሉት ችግኞችም ከደን አኳያ ከውጭ አገራት የሚገባውን የጣውላ ግብዓት የሚተኩ፣ የአትክልትና ፍራፍሬ፣ ለማገዶ የሚውሉ እና ሀገር በቀል ችግኖች መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡

እንደ ኃላፊው ገለጻ፣ በከተማና ገጠር አካባቢ የሚደረገው የችግኝ ተከላ እንዳለ ሆኖ ተራራዎችንም ለማልማት በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ ነው፡፡ በዚህም ለችግኝ ተከላው 114 ተራራዎች ተለይተው ተዘጋጅተዋል፡፡

ለተከላው የሚሆን ከ400 ሄክታር በላይ መሬት እንደተዘጋጀ የተናገሩት አቶ ዳንኤል፤ ለአካባቢው የሚስማማውን ችግኝ ለመትከል ጥናት የማድረግ ሥራ ተጀምሯል፡፡ በዚህም በካርታ ሥራ 150 ሄክታሩ የተጠናቀቀ ሲሆን ቀሪው በቀጣይ ጊዜያት ይጠናቀቃል ብለዋል፡፡

በሌላ በኩል በክልሉ በበልግ ወቅት በሚተገበረው የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር 350 ሚሊዮን ችግኞች መተከላቸውን አስታውሰዋል፡፡



አቶ ዳንኤል ዳምጠው

በክልሉ የአረንጓዴ አሻራ መርሐግብር በበልግና በክረምት ወቅቶች እንደሚከናወን የተናገሩት ኃላፊው፤ በክልሉ በአንዳንድ አካባቢዎች ከግብርና ሥነምሕዳር አንጻር ክረምት ላይ ዝናብ የማይዘንብባቸው አከባቢዎች በበልግ ወቅት እንዲተክሉ ይደረጋል ብለዋል፡፡

በዚህም ከሚያዚያ ወር ጀምሮ እስካሁን ባሉት ጊዜያት በደን ልማት 150 ሚሊዮን ችግኞች የተተከሉ ሲሆን በአግሮ ፎረስተሪ 200 ሚሊዮን ችግኝ ተተክለዋል ሲሉ አስረድተዋል፡፡

# የኢፕድ ሥልጠና...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ማዕከሉ “ትጋት፣ ዕውቀት፣ ፈጠራና ትብብር ለውጤት” በሚል መሪ ሃሳብ በኢፕድ ሥልጠና ማዕከል ለኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር አመራሮች ሥልጠና ሰጥቷል፡፡

በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የሥራ አመራር ዋና ሥራ አስፈፃሚ ዶክተር አንተነህ ተስፋዬ እንደተናገሩት፤ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በቀጣይ በጀት ዓመት በርካታ ሥራዎችን ከኢፕድ ጋር ለመሥራት እቅድ ይዟል። በኢፕድ ሥልጠና ማዕከል ከአመራር እስከ ባለሙያ ድረስ በሥልጠናው መሳተፉ ቅንጅታዊ አሠራርን በማጎልበት ውጤታማ የሚያደርግ ነው።

የሰው ሃብት አስተዳደር ሥራ አስፈፃሚ አቶ ስበር አንዱዓለም በበኩላቸው፤ ሚኒስቴሩ የተሻለ አቅምና ገጽታ እንዲኖረው ለማድረግ በኢፕድ ያገኘነው ሥልጠና በዓይነቱ ለየት ያለና ወሳኝ ነው ብለዋል።

በተለይ በቀጣይ በጀት ዓመት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ውጤታማ ሥራዎችን ለማከናወን አዲስ መዋቅር ተግባራዊ እያደረገ በመሆኑ ሥልጠናው ጠቀሜታው የጎላ ነው ሲሉ ገልጸዋል። ሥልጠናው እያንዳንዱ የተቋሙ ሠራተኛ በተሰጠው መዋቅር ማድረግ ያለበትን ጉዳይ እንዲገነዘብ ዕድል የፈጠረ እንደሆነም ገልጸዋል፡፡



ፎቶ - ኢጋፒ ገዮን

ለኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር አመራሮች ሥልጠና ሲሰጥ

የኢፕድ ሥልጠና ማዕከል የተቋማት አመራሮችንና ሠራተኞች የነበራቸውን ችሎታ በማጎልበት የተሻለ አፈፃጸም እንዲኖር እየሠራ በመሆኑ ሊደነቅ ይገባል ያሉት ደግሞ የአሻጋሪ ኮንሰልቲንግ መሥራች ወይዘሮ መቅደስ ገብረወልድ ናቸው።

የተቋማት አመራሮች ከሌሎች ሠራተኞች ጋር የሚኖራቸውን ግንኙነት ይበልጥ ለማሻሻል የኢፕድ ሥልጠና ማዕከል የሚሰጣቸው ሥልጠናዎች ወሳኝ ናቸው ያሉት ወይዘሮ መቅደስ፤ ሠራተኛ ተኮር ሥራዎችን የማይሠሩ ተቋማት ይወድቃሉ። ስለዚህ እየተሰጠ ያለው ሥልጠና ጉልህ ሚና አለው ብለዋል።

ሥልጠናው አመራሮች እና ሠራተኞች በተቋማቸው ያለውን ጥንካሬና ድክመት ተገንዝበው የተቋሙን ግብ ማሳካት እንዲችሉ እንደሚረዳ ገልፀው፤ ኢፕድ ራሱን የቻለ የሥልጠና ማዕከል ማዘጋጀቱ የሚደነቅ ነው። ይህም አንዱ ልዩ ነገሩ ሲሆን ሌላው ማዕከሉ ከሌሎች የሚለየው የሠልጣኞች ቁጥር የተመጠነ መሆኑ ሥልጠናው ውጤታማ እንዲሆን ያደርገዋል። ከዚህም ባለፈ ማዕከሉ ብቁ አሠልጣኞች እንዳሉት ተረድቻለሁ ብለዋል።

ኢፕድ በሥልጠና ማዕከሉ ከዚህ በፊት በተለያዩ የሥልጠና ርዕሶች ዙሪያ ከ70 በላይ ለሚሆኑ የፌዴራልና የክልል ተቋማትና የግል ድርጅቶች በአዲስ አበባና ከአዲስ አበባ ውጭ ተመሳሳይ ሥልጠናዎችን በመስጠት አስመርቋል።

በአሁኑ ወቅትም የልማት ባንክ፣ አዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን፣ አዲስ አበባ ንግድ ቢሮ፣ የምኒሊክ ሆስፒታል፣ ቅርስ ጥበቃ ባለሥልጣን እና ቡናና ሻይ ባለሥልጣንም በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ አጫጭር ሥልጠናዎችን እየወሰዱ ይገኛሉ።

# በኢትዮጵያ የዲጂታል...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ችግሮች ውስጥ በተለይ በገጠራማ የሀገሪቱ አካባቢዎች አነስተኛ የሆነ የኢንተርኔት ተደራሽነት ችግር መኖሩ አንዱ ተግዳሮት ነው።

ችግሩን ለመፍታት በመጪው በጀት ዓመት ግልጽ የሆነ የትግበራ እቅድን ተግባራዊ በማድረግ እያጋጠሙ ያሉ ችግሮችን መቅረፍ፣ የዲጂታል ክፍያ ሥርዓትን ማሳደግና አልሚዎችን የመሳብ ሥራ እንደሚሠራ የገለጹት ሚኒስትሩ፤ በአይሲቲ ዝርጋታ ለሚሰማሩ የግል ባለሀብቶች አመቺ ፖሊሲ ስለመኖሩና ለዚህም የመንግሥት ድጋፍ እንደሚኖር ተናግረዋል።በዚህም ኢትዮጵያ ምቹ የኢንቨስትመንት መስሕብ እንድትሆን ይደረጋል ብለዋል፡፡

አይሲቲን ማስፋፋትና መጠቀም የሥራ እድል ፈጠራንና የዲጂታል ዕድገትን ለማፋጠን ያለው አስተዋፅዖ የጎላ ነው ያሉት ዶክተር በለጠ፤ ኢትዮጵያ ወደ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሽግግር ለማድረግ በትምህርት፣ በፋይናንስ፣ በግብርና፣ በጤናና በሌሎች ዘርፎች ዲጂታል ኢትዮጵያን ለማረጋገጥ በስፋት እየሠራች እንደምትገኝ አስረድተዋል።

የቴሌኮም ዘርፉ ከፍተኛ የሆነ ዕድልና ተግዳሮት ያለበት ሰፊ ዘርፍ ቢሆንም ዘርፉን ለማዘመን ቴክኖሎጂን መጠቀምና የመሠረተ ልማት ዝርጋታዎችን የማሟላት ሥራ በመንግሥት በኩል እየተተገበረ ይገኛልም ብለዋል፡፡

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የቴሌኮም ዘርፉ በከፍተኛ ለውጥ ውስጥ ይገኛል ያሉት ሚኒስትሩ፤ መንግሥት ዘርፉን በከፍተኛ ሁኔታ የመለወጥ እርምጃ ወስዷል፤ ከዚህም ውስጥ በመንግሥት ብቻ ተይዞ የነበረው የቴሌኮም ዘርፍ የግል ባለሀብቶች እንዲሰማሩበት የፖሊሲ ለውጥ መደረጉ ተጠቃሽ ነው ብለዋል።

ይህም ከአንድ በላይ በሆኑ የቴሌኮም ኦፐሬተሮች መካከል ውድድር እንዲኖር በማድረግ ቀልጣፋ የሆነ አገልግሎት እንዲኖርና የፈጠራ ሥራዎችን እንዲበራከቱ በማድረግ የዲጂታል ኢኮኖሚውን ያሳድገዋል።በአሁኑ ወቅት ከ60 ሚሊዮን በላይ ዜጎች የሞባይል ተጠቃሚዎች መሆናቸውና ካለፉት ሦስት ዓመታት ወዲህ የኢንተርኔት ተጠቃሚ ቁጥር መጨመሩ የቴሌኮም ዘርፉ በፍጥነት እያደገ ለመሆኑ ማሳያ ነው ሲሉ ጠቁመዋል፡፡

# አገራዊ ምክክሩ የተሳካ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

“ሕዝብ የእኔ ነው ይመለከተኛል፤ ያገባኛል ብሎ የሚያስፈልገውን ሁሉ መስዋዕትነት ከፍሎ ውይይቱ ላይ ሲገባበትና ሂደቱንም ሲቆጣጠር ለስኬቱ ዋስትና ይሆናል።” ነው ያሉት ኮሚሽነሩ።

ግልጽነት የተሞላበት አካሄድና አካታች የሆነ ውይይት ለአገራዊ ምክክሩ ያለው ሚና ከፍተኛ መሆኑን የገለጹት ዶክተር ዮናስ፤ ኅብረተሰቡ ስለ ምክክሩ በግልጽነት ማወቅ እንዳለበትና በዋናነት የምክክሩ ተጠቃሚ ራሱ ሕዝቡ መሆኑን መገንዘብ እንደሚገባው አብራርተዋል።

ምክክሩ አዲስ የባሕል ግንባታን የሚፈጥር፣ ማኅበራዊ ውልና ሕገመንግሥት እስከማደስ ሊደርስ የሚችል መሆኑንም አብራርተው፤ በክልል መንግሥት እና በፌዴራል መንግሥት መካከል ያለውን ግንኙነት ሊቀይር ይችላል ብለዋል። ሕዝብ በምክክሮቹ በሚያነሳቸው ሃሳቦች መንግሥት አካሄዱንም በድጋሚ እንዲፈትሽ ሊያደርግ እንደሚችል ገልጸዋል።

አገራዊ ውይይቱ አካታች እንዲሆን በርካታ ሥራዎች መሠራታቸውን ገልጸው፤ ለአብነትም ተፈናቃዮችን፣ ሴተኛ አዳሪዎችን፤ ጎዳና ተዳዳሪዎችን እንዳካተቱም አስረድተዋል። በቀጣይም ሌሎች ያልተካተቱ የኅብረተሰብ ክፍሎች ካሉ እንደሚጨመሩ አብራርተዋል።

የአገራችን ምክክር አካሄዱ ሦስት አይነት መሆኑን የተናገሩት ኮሚሽነሩ፤ አገር በቀል እውቀቶችን በመጠቀም 60 በመቶ ከታች ወደ ላይ ሃሳቦች እንደሚመጡ ገልጸው፤ ከላይ ወደታችና ከጎን ያሉ ሃሳቦች ጭምር እንዲያዙ እንደሚደረግ ገልጸዋል።

# “የግል ትምህርት ቤቶች...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

አልቻልኩም። በመሆኑም በመጪው ዓመት ልጆቼን ከተቻለ ወደመንግሥት ትምህርት ቤት ለማስገባት አልያም አነስተኛ ክፍያ ወደሚጠይቅ ትምህርት ቤት ለማስገባት እሞክራለሁ ብለዋል፡፡

ወይዘሮ ወይንሸት ካሳ በበኩላቸው፤ በኖቤል አካዳሚ ትምህርት ቤት የሚያስተምሯቸው ሁለት ልጆች እንዳሏቸው ገልጸው፤ ለሁለት ልጆቼ የምከፍለው ክፍያ በተደረገው የዋጋ ጭማሪ ምክንያት በእጥፍ ጨምሮብኛል ብለዋል። ይህም ከባድ በመሆኑ በክፍያ መጠን ዝቅ ወደሚል ትምህርት ቤት ለማስገባት እቅድ መያዛቸውን ተናግረዋል።

“ራዲካል ትምህርት ቤት የእጥፍ ጭማሪውን አስመልክቶ ከወላጆች ጋራ ስብሰባ ቢያካሂድም ያለስምምነት ተበትኗል። ሆኖም ባለፈው ሳምንት በመጪው ዓመት ወላጆች አሁን በሚከፍሉት ክፍያ ላይ 65 በመቶ ጭማሪ ሊደረግ መሆኑን ልጄን ከትምህርት ቤት ላመጣ ስሄድ ሰምቻለሁ” ያሉት ደግሞ አቶ ዘሚካኤል አለሙ (ስማቸው የተለወጠ) ናቸው።

እንደ አቶ ዘሚካኤል አለሙ ገለፃ፤ ትምህርት ቤቱ ለጭማሪው በመነሻነት የሚያቀርበው፥ የቤት ኪራይ፣ የወረቀት እና የመሳሰሉት ግብዓቶች ዋጋ መናርንና የመምህራን ደመወዝ ጭማሪን ነው። ሆኖም ከፍተኛ ጭማሪ እያደረጉ ካሉት ትምህርት ቤቶች አንዳንዶቹ፣ የራሳቸው ሕንፃ ያላቸው ጭምር በመኾናቸው፣ የተጠቀሱት ምክንያቶች ተቀባይነት የላቸውም።

አቶ ዘሚካኤል እንደሚሉት የወላጅ ተማሪ መምህራን ኅብረት ይህንን ጉዳይ በዋናነት እየተከታተለ ከወላጆች ጋር በጋራ መሥራት ቢኖርበትም ይህንን ግን እያደረገ አይደለም። ለአብነትም እሳቸው ልጆቻቸውን በሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት የዋጋ ጭማሪው ሲወሰን እነዚህ ኮሚቴዎች ከወላጆች ጋር አልተማከሩም። ከዚያ በኋላም ይዘው የመጡት የጭማሪ እቅድ ትምህርት ቤቱ ካቀረበው ጋር ተመሳሳይ ነበር፡፡

ወላጆች የተለየ የገቢ ጭማሪ ባላገኙበትና የኑሮ ውድነቱ ከፍተኛ ጫና በፈጠረበት በአሁኑ ወቅት ትምህርት ቤቱ የወሰነው የክፍያ ጭማሪ ተመጣጣኝ መሆን አለበት ያሉት አቶ ዘሚካኤል፤ በትምህርት ቤት ክፍያ የዋጋ ጭማሪ ዙሪያ ወላጆች እና የግል ትምህርት ቤት ባለቤቶች ሳይስማሙ ሲቀሩ መንግሥት እጁን ማስገባት ይኖርበታል ብለዋል።

የአዲስ አበባ የትምህርትና ሥልጠና ጥራት ቁጥጥር ባለስልጣን ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ ወይዘሮ ፍቅርተ አበራ በሰጡት ምላሽ፤ ወላጆች እና ትምህርት ቤቶች ባልተስማሙባቸው አካባቢዎች ሁለቱን ለማስማማት እየገባን ቢሆንም ዋጋ ትመና ውስጥ ግን አንገባም ብለዋል።ከወላጆች ጋራ በቂ ውይይት ሳይደረግ የጭማሪ ዕቅዱን መተግበር እንደማይቻልም ገልጸዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የርዳታ ተቋማቱ የርዳታ አቅርቦቶችን ለማቆም የደረሱበትን ውሳኔ ዳግም ሲያጤኑት ይገባል

አገራችን ብዙ ዋጋ ካስከፈለን ጦርነት ወጥታ የሰላም አየር መተንፈስ ከጀመረች ወራቶች ቢቆጠሩም፤ ጦርነቱ ከፈጠረው ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ሥነልቦናዊ ስብራቶች በአግባቡ አላገገመችም። ከነዚህ ስብራቶች ለማገገምም ብዙ የቤት ሥራዎች ይጠብቋታል።

በጦርነት የወደሙ ማኅበራዊ መገልገያ ተቋማትን ጨምሮ፣ የመሠረተ ልማቶችን መልሶ መገንባት፤ በጦርነቱ የልብ ስብራት የደረሰባቸውን ዜጎች ሕይወት ወደ ቀደመ ቦታው እንዲመለስ ለማድረግ የሚደረገው ሀገራዊ ጥረት በብዙ መልኩ ለሀገርና ለሕዝብ ትልቅ የቤት ሥራ እንደሆን ይታመናል።

በተለይም አህገሪቱ ላለፉት አምስት ዓመታት ካለፈችባቸው የፈተና መንገዶች፣ እንዲሁም በጦርነቱ ምክንያት ከወደሙ አያሌ ምጣኔ ሃብታዊ ሃብቶች አንጻር፤ እነዚህን ስብራቶች አክሞ ለመሻገር ከ20 ቢሊዮን ዶላር በላይ እንደሚያስፈልጋት ተደጋግሞ እየተነገረ ነው። ይሄን ሁሉ ሀብት ደግሞ በሀገር ውስጥ ብቻ ማሰባሰብና ማግኘት የሚቻልበት ዕድል ባለመኖሩ ለዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ ተደጋጋሚ ጥሪዎች እየተደረጉ ነው።

መንግሥት ፈተናዎችን ተሻግሮ የቤት ሥራዎቹን ለመወጣት ጦርነቱን በውይይት/በሰላም ስምምነት እንዲቋጭ ከማድረግ ጀምሮ፤ በጦርነቱ ወቅት እና ከዚያም በፊት ሆነ በኋላ እንደሀገር ሲፈታተኑን የኖሩ እና ያሉ ችግሮችን ለመፍታት የተለያዩ ስትራቴጂዎችን ነድፎ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። በዚህም ተስፋ ሰጭ ውጤቶች እየታዩ ነው ።

በተለይም እንደሀገር አንገት የሚያስደፋን ተመጽዋችነት ለዘለቄታው ከላያችን ላይ ለማውረድ በምግብ እህል እራሳችንን ለመቻል የሚረዱ የተለያዩ ስትራቴጂዎችን ነድፎ እየተንቀሳቀሰ ነው። ለዚህም የበጋ ስንዴ እርሻን ጨምሮ በስንዴ፣ ሩዝ እና ሌሎችም አትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች እየተገኘ ያለው ስኬት ተጠቃሽ ነው።

ይሁን እንጂ ለዓመታት ብሔራዊ ክብራችንን እየተገዳደረ የሚገኘውን ተመጽዋችነት ከሀገራችን ስምና ከሕዝባችን ጫንቃ ላይ ለመጣል የሚደረገው ጥረት፤ በይቻላል መንፈስ ሀገራዊ መነቃቃትን በመፍጠር ብዙ መሥራት/መልፋትን የሚጠይቅ እንደሆነ ይታመናል።

ዓለም አቀፉም ኅብረተሰብም ቢሆን በኢትዮጵያ የታየው ሀገራዊ መነቃቃቱ የፈጠረው ስኬት ለሌሎች ሀገራትን ሕዝቦችም የነጋቸው ተስፋ ሰጪ ተሞክሮ መሆኑን በመገንዘብ ተገቢውን ድጋፍ መስጠት ይጠበቅበታል። ኢትዮጵያ እንደ አገር ከመጣችባቸው የፈተና መንገዶች አንጻር ይህን የማድረግ የሞራል ግዴታም አለበት።

በተለይም ከትናንት ያደሩ የቤት ሥራዎቻችንን፣ ብሩህ ነጋችንን ታሳቢ አድርገን ዛሬ ላይ ለምንሠራቸው ሥራዎች ተግዳሮት እንዳይሆኑ እና ወደ ኋላ እንዳይመልሱን ዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ ከፍ ያለ ኃላፊነት ይጠበቅበታል። ይሄ ኃላፊነትም ነገን ብሩህ ለማድረግ የተጀመረውን ሀገራዊ መነቃቃትን ከመደገፍ እና ለስኬቶቹ እውቅና ከመስጠት የሚጀምር ነው።

ከዚህ ውጪ ጥቃቅን ክፍተቶችንና የጥቂቶች እንከኖችን በመፈለግ እነዚህን እንደመልካም አጋጣሚ በመውሰድ ሕዝባችን እራሱን ለመሆን የጀመረውን መነቃቃት የሚያደበዝዙ፤ ብሔራዊ ክብሩንና ሥነልቦናውን የሚጎዱ ተግባራትን በአደባባይ መፈጸም ከሁሉም በላይ የሞራል ተጠያቂነት መፍጠሩ የማይቀር ነው።

በዚህ ረገድ በተለይም ተረጅነትን አሸንፎ ለመውጣት እያደረግናቸው ያሉ ብሔራዊ ጥረቶች ተስፋ ሰጭ እየሆኑ ባለበት ወቅት፤ የርዳታ እህል ተሰርቋል በሚል ለሰብዓዊ ድጋፍ የሚውሉ የርዳታ አቅርቦቶችን በማቋረጥ ተረጂ ዜጎችን ለከፋ አደጋ ተጋላጭ ማድረግ ተገቢ ያልሆነ የሞራል ተጠያቂነትን የሚያስከትል ስህተት ነው።

በርግጥ በችግሩ ዙሪያ ክስ የሚሰነዝሩ አካላት ከክሳቸው በስተጀርባ እውነት ሊኖርም ላይኖርም ይችላል። ይህ ሊረጋገጥ የሚችለው ግን "ከሳሽና ተከሳሽ" በሚያቀርቡት ሃሳብ ላይ ተመሥርቶ በገለልተኛ አካል በሚደረግ ማጣራት ብቻ ነው። እነሱ ከሳሽ እነሱ ዳኛ በመሆን የሚደርሱበት ውሳኔ ግን በየትኛውም መመዘኛ ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም።

ተቋማቱ የርዳታ አቅርቦቶችን በራሳቸው ተቋማዊ አደረጃጀት ለተረጂው ሕዝብ የሚያቀርቡበት አሠራር ባለበት ሁኔታም አንድን አካል/መንግሥትን በተናጠል ተጠያቂ ለማድረግ የሄዱበት መንገድ በራሱ ችግሩ ግልጽነት የጎደለው ነው። ይሄ ደግሞ ችግሩ እንኳን ተፈጽሞ ቢሆን ተገቢውን ተጠያቂነት ማስፈን የሚያስችል አይደለም።

ምክንያቱም በሀገሪቱ ለሚገኙ ተረጂዎች የሚቀርበው የእርዳታ አቅርቦት ባልተገባ መንገድ እንዲቋረጥ ያደረጉ ተቋማት፤ ከሁሉም በፊት በችግሩ ዙሪያ ተገቢውን ማጣራት ከሚመለከታቸው የፌደራል ሆነ የክልል መንግሥታት ጋር በማድረግ ለችግሩ ባለቤት ሊሰጡ ይገባ ነበር። ለዚህ ደግሞ መንግሥት ቀደም ሲል ክሱን ለመመርመር ካቋቋመው ብሔራዊ ኮሚቴ ጋር ተቀናጅቶ መሥራት የሚያስችላቸው የተመቻቸ ሁኔታ ነበር።

ከዚህ ውጪ እራሳቸው ከሳሽ እና ዳኛ ሆነው አሁን ላይ በርዳታ ፈላጊ ዜጎቻችን ጉሮሮ ላይ የወሰኑት የርዳታ አቅርቦቶችን የማቋረጥ ውሳኔ ከተቋማቱ ተልዕኮ ጋር የማይጣጣም፤ ከጉዳዩ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የሌላቸውን ቀድሞውንም የችግሩ ሰለባ የሆኑትን ተረጂ ዜጎችን ለተጨማሪ አደጋ የሚዳርግ ነው።

በመሆኑም በመጀመሪያ ደረጃ፣ እነዚህ የእርዳታ ተቋማት ካለባቸው ዓለም አቀፍ ኃላፊነት አንጻር ተፈጠረ ለተባለው ችግር ባለቤት ለማግኘት መንግሥት ካቋቋመው ብሔራዊ ኮሚቴ ጋር ተቀናጅተው ለመሥራት እራሳቸውን ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል። በሁለተኛ ደረጃም፣ የደረሱበት ያልተገባ ውሳኔ ችግሩ የማይመለከታቸውን ዜጎች ያለ ኃጢያታቸው መቅጣት በመሆኑ ውሳኔውን ዳግም ሊያጤኑት ይገባል።


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው።በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

## ከአረንጓዴ ዐሻራ የአፍሪካ ቀንድ ተጠቃሚነት

እስማኤል አረቦ

የአፍሪካ ቀንድ ከድርቅ አልፋታ ካለ ከአራት አሥርታት በላይ አስቆጥሯል፡፡ አሁን፤ አሁን ደግሞ በየ10 ዓመቱ ይከሰት የነበረው ድርቅ በየዓመቱ እየተደጋገመ መምጣት ጀምሯል፡፡ ድርቁም ከጊዜ ወደ ጊዜ ወደ አስከፊነት እየተሸጋገረ ከሰው እስከ እንስሳት መልከዓ ምድሩን ጨምሮ ዋጋ እያስከፈለ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ በዋነኝነት ኢትዮጵያ፣ ሶማሊያ፤ ኬንያና ጂቡቲ የበለጠ ተጋላጭ ናቸው፡፡

ሮይተርስ እንደዘገበው ከ1970ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ ምስራቅ አፍሪካ በድርቅ ሲጎዳ ኖሯል፡፡ ለችግሩ መከሰት ደግሞ በዋነኝነት ከአየር መዛባት ጋር በተያያዘ የሚፈጠረው የዝናብ መዋዠቅ እንደሆነ አስምሮበታል፡፡ ድርቅ በተደጋጋሚ በሚያጠቃው የምስራቅ አፍሪካ ቀጣና እ.ኤ.አ. በ2011 በተከሰተው ቸነፈር ህጻናትን ጨምሮ ከሩብ ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ሰዎችን ሕይወት ቀጥፏል፡፡

በምግብ ደህንነትና ሥነ ምግብ ላይ የሚሠራው ዓለም አቀፋዊ ተቋም የሆነው (ኤፍ.ኤስ.ኤን. ደብሊው.ጂ) ባወጣው ልዩ የድርቅ ዘገባ መሠረት ከ8 ነጥብ 9 ሚሊዮን በላይ የአርብቶ አደር ቤተሰቦች ለምግብና ለኑሮ የሚተማመኑባቸውን ከዘጠኝ ሚሊዮን በላይ የቤት እንስሳት ድርቁ ገድሎባቸዋል። በኢትዮጵያ 3 ነጥብ 5 ሚሊዮን፣ በኬንያ 2 ነጥብ 4 ሚሊዮንና በሶማሊያ 3 ነጥብ 5 ሚሊዮን የሚደርሱ ከብቶች በመሞታቸው ከእነሱ የሚገኘው ከፍተኛ መጠን ያለው የወተት ምርትም እንዲታጣ ሆኗል።

በድርቁም አንዳንድ አካባቢዎች ከአምስት ዓመት በታች የሆኑ 1 ነጥብ 6 ሚሊዮን ሕፃናት በቀን አንድ ብርጭቆ ወተት ለማግኘት መቸገራቸውን በምሕፃሩ ፋኦ ተብሎ የሚታወቀው የምግብና የእርሻ ድርጅት ገልጿል። እንግዲህ ለአርባ ዓመታት ያህል እየተመላለሰ የሰዎችንና የእንስሳትን ሕይወት የሚቀጥፈው ድርቅ ለዘመናት መፍትሄ ሳይገኝለት ቆይቷል፡፡ መንስኤው እየታወቀ መፍትሄ ላይ ያልተደረሰበት ምክንያትም እንቆቅልሽ እንደሆነ ቆይቷል፡፡

ከአምስት ዓመታት በፊት ወደ ሥልጣን የመጡት የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ለዘመናት ሲንከባለል ለመጣው ጥያቄ መልስ ይዘው የመጡ ይመስላል፡፡ በምስራቅ አፍሪካ ቀጣና ለአርባ ዓመታት ያህል እየተመላለሰ መጠነ ሰፊ ጉዳት እያደረሰ ያለው ድርቅ መነሻው የአካባቢ መራቆት ነው፡፡ መፍትሄውም ከዚህ ብዙ የሚርቅ አይደለም፡፡ መፍትሄው የተራቆተውን አካባቢ መልሶ እንዲያገግም ማድረግና አካባቢውን በደን ማልበስ መሆኑንም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገና ከጅምሩ ተረድተውታል፡፡

በእርግጥ ከዚህ ወቀደም የነበሩ የኢትዮጵያ መሪዎች ለአካባቢ ጥበቃ ልዩ ትኩረትን ሲሰጡ ቆይተዋል፡፡ ከዳግምዊ ሚኒልክ ጀምሮ ያሉ መሪዎች በየዘመናቸው ችግኞችን ሲተክሉ ኖረዋል፡፡ ሆኖም የጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ አስተዋጽኦ ግን በአይነቱ ለየት ያለና ግዝፈት ያለውም ነው፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገና ወደ ሥልጣን እንደመጡ ኢትዮጵያ በአረንጓዴ ዐሻራ ዘመቻ ሃያ ሚሊዮን ዛፎችን ለመትከል ማቀዷን ይፋ ሲያደርጉ ከልቡ የተቀበለው ጥቂቱ ነበር፤ ለመዘባበት የሚሞክሩም ብዙ ነበሩ፡፡ ሆኖም በመጀመርያ ዙር ከ4 ቢሊዮን በላይ ችግኞችን ለመትከል እቅድ በመያዝ በአንድ ቀን ብቻ ደግሞ ከ350 ሚሊዮን በላይ ችግኞችን በዘመቻ በመትከል ኢትዮጵያ ታሪክ መጻፍ ቻለች፡፡

ጉዳዩን በቅርብ ሲከታተሉ የነበሩና የተረዱ ወገኖች በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ መሪነት የሚካሄደው የአረንጓዴ ዐሻራ እንቅስቃሴ ዘመቻ በህዝብ ዘንድ ተቀባይነት በማግኘቱ የችግኝ ተከላው የአገሪቱን የአረንጓዴ እጽዋት ሽፋንን እንዳሳደገ፤ ብሎም የአየር ንብረት ለውጥን እየተከላከለ እና የሰዎች ሕይወት ላይ ለውጥ እያመጣ መሆኑን ሲመሰክሩ ተደምጠዋል። በተወካዮች ምክር ቤት አባላትና በገለልተኛ አካላት በተደረገ ጥናትና በመንግሥት የሚደገፈው የአረንጓዴ ዐሻራ እንቅስቃሴ የቴክኒክ ኮሚቴ እንዳስታወቀው በአውሮፓውያኑ አቆጣጠር 2019 ከተተከሉት ችግኞች ውስጥ ውስጥ 83 ነጥብ 4 በመቶው እንዲሁም እአአ በ2020 ከተተከሉት ውስጥ ደግሞ 79 በመቶው ጸድቀዋል።

በተጨማሪ ኢትዮጵያ እያከናወነችው ያለው የችግኝ ተከላ መርሃ ግብር አገሪቱን በአረንጓዴ ከማልበስ በሻገር በጥቂት ዓመታት ውስጥም ለምግብነት ሊውሉ የሚችሉ። እንዲሁም የችግኝ ተከላን ከግብርና ጋር አቀናጅቶ በማካሄድ አቦካዶን እንዲሁም ፓፓያን የመሳሰሉ ፍራፍሬዎችን ጨምሮ የተለያዩ ችግኞች እንዲተከሉ ያስቻለ ሲሆን፤ ይህም አጠቃለይ በአገሪቱ ላለው የምግብ ሥርዓት ትልቅ ፋይዳ የሚያመጣም ነው።

ባለሙያዎች እንደሚናገሩት የደን ሽፋን መልሶ እንዲያገግም ማድረግ የአየር እርጥበትን ለመጠበቅ ይረዳል ይላሉ። ይህ ደግሞ በተደጋጋሚ የሚመጣውን ድርቅ እስከወዲያኛው ለመሸኘት ዋነኛ ምፍትሄ ነው፡፡ ኢትዮጵያ የጀመረችውም የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር ከራሷ አልፎ ለአካባቢውም መድህን ይሆናል ለማለት ያስደፍራል። ይህ የአረንጓዴ ዐሻራ እንቅስቃሴ ከኢትዮጵያ ባሻገር ካለው አፍሪካ አቀፍ የታላቁ የአረንጓዴ ግድግዳ ልማት ፕሮጀክት ዕቅድ ጋር የተያያዘም ነው።

ዛሬ ላይ ኢትዮጵያ እያደረገች ያለውም ጥረት በአውሮፓውያኑ እአአ 2007 ላይ በአፍሪካ ኅብረት አማካይነት የተጀመረውን የታላቁ አረንጓዴ ልማት ፕሮጀክት እንዲሳካ የሚያደርግም ነው፡፡ ይህ ደግሞ ከጂቡቲ እስከ ሴኔጋል የሚዘረጋ 8 ሺህ ኪሎ ሜትር የሚሸፍን የዛፎች ከለላ መፍጠርን ዓላማ ያደረገ ነው። የአፍሪካ ህብረት የያዘው ዕቅድም እስከ እአአ 2030 ድረስ በሚለማው የአረንጓዴ ግድግዳ ደን የሰሃራ በረሃ ወደ ደቡብ አቅጣጫ እንዳይስፋፋ ለማድረግ የሚደረግ ጥረት ነው።

የጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አስተዳደር ከመምጣቱ በፊት የአፍሪካ ህብረት የያዘው ዕቅድ ከዕቅድነት ብዙም የዘለለ አልነበረም፡፡ ከአፍሪካ ህብረት በተገኘውም መረጃም ህብረቱ የአረንጓዴ ዐሻራን በተመለከተ ያከናወነው ሥራ ከ15 በመቶ ብዙም የዘለለ አልነበረም፡፡ አሁን ግን ክንውኑን በእጥፍ ለማሳደግ ኢትዮጵያ ከፍተኛ ሚና እየተጫወተች ነው፡፡

ኢትዮጵያ በመጀመርያው ዙር 25 ቢሊዮን ችግኞችን ለመትከል ከመቻሏም በላይ በዘርፉ ባለፉት አራት ዓመታት ከ767 ሺህ በላይ የስራ ዕድል መፍጠር ችላለች፡፡ የ25 ቢሊዮን ችግኝ ተከላን ዕውን ለማድረግ ያስቻሉም ከ120 ሺህ በላይ የችግኝ ማፊያ ጣቢያዎች ተመስርተዋል፡፡

ይህንኑ ውጤት ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገርም ሰኔ አንድ ቀን ሁለተኛውን የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐግብር ጀምራለች፡፡ በዚሁ መርሃ ግብር የመጀመርያ ዓመትም ከ6 ቢሊዮን በላይ ችግኞችን በመትከል የተተከሉትን ችግኞች ቁጥር ከ31 ቢሊዮን በላይ ለማድረስ ዕቅድ ይዛለች፡፡ በቀጣይ ሶስት ዓመታት መጨረሻ ደግሞ 50 ቢሊዮን ችግኞች የሚተከሉ ይሆናል።

ኢትዮጵያ እንዳጠቃላይ በሁለተኛው ዙር የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር መጨረሻም ከ50 ቢሊዮን በላይ ችግኞችን በመትከል ታሪክ ለመጻፍ መዘጋጀቷ ይታወቃል፡፡ አገሪቱ ባለፉት አራት ዓመታት ካላት ስኬት አንጻር ሲመዘንም ያቀደችውን ወደ መሬት ለማውረድ ብዙም እንደማትቸገር መረዳት ይቻላል፡፡ ከዚሁ ጎን ለጎንም ከፕሪቶርያው ስምምነት በኋላ በትግራይ ሙሉ በሙሉ ሰላም መስፈኑ አረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብሩ በመላ አገሪቱ እንዲተገበር አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

# ከ "አረንጓዴ ወርቅ ..." በላይ ነው ፤

በአገራችን ቡና ለኢኮኖሚው ባለው የገዘፈ አስተዋጽኦ አረንጓዴው ወርቅ በመባል ይታወቃል። የቻይናው ፕሬዚዳንት ሺን ዥንፒንግ የአካባቢ ጥበቃ ማለትም የችግኝ ተከላን ፤ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎችንና ከአየር ንብረት ጥበቃ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ተግባራት "አረንጓዴ ወርቅ ናቸው !" ሲሉ ያሞካሿቸዋል። በሰብዓዊነትና በተፈጥሮ ሕብርነት ላይ በመከረ "የ2023 ኤርሀይ መድረክ" ላይ ተፈጥሮና ልማት ሳይጠፋፉ መሳ ለመሳ ስምም ሆነው መሔድ እንደሚችሉ ተመልክቷል ።

ሥነ ምህዳርና ሲቪላይዜሽን እጅና ጓንት ሊሆኑ እንደሚችሉ ከቻይናዋ ዳሊ ቤይ ክፍለ አገሯ ኤርሀይ በላይ ማሳያ የለም ይላል ሰሞኑን ለንባብ የበቃውና ከቻይና መንግሥት ልሳኖች አንዱ የሆነው "ቤጂንግ ሪቪው" መጽሔት በርዕሰ አንቀጹ ። ይች ደሴት ሲቪላይዜሽንንና ሥነ ምህዳርን እርቅ አውርደው በአንድነት መኖር ለመቻላቸው ጥሩ አብነት ናት። በግሌ የአካባቢ ጥበቃ ስራ ለሰው ልጅም ሆነ ለምንኖርባት ፕላኔት ህልውና ወሳኝ ስለሆነ በአልማዝም ሆነ በወርቅ አይለካም ብዬ አምናለሁ። ከየትኛውም የከበረ ማዕድን በላይ ነው ። ሰሞነኛው የቻይና መድረክ ከአገራችን ሁለተኛ ዙር የአረንጓዴ ዐሻራ ጋር ስለተገጣጠመ አነሳሁት እንጂ በዓለማችን የዘንድሮውን ጨምሮ ከ31 ቢሊዮን በላይ ችግኞችን በመትከል አገራችንን መወዳደር ቀርቶ አጠገቧ የሚደርስ አገር የለም።

በአገራችን የዘንድሮን የአረንጓዴ ዐሻራ ተከላ ስናገባድድ ፤ ኢትዮጵያ በ31 ቢሊዮን ችግኞች ትለብሳለች። ኑ ! ይህንን ታሪክ አብረን እንሥራ ! ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ጥሪ አስተላልፈዋል። "ዛሬ ነገን እንትከል !" ይህ ዛሬ ለምንጀምረው የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር የሁለተኛው ምእራፍ ጅማሮ መሪ ሃሳብ ነው፡፡ 25 ቢሊዮን ችግኞችን የተከልንበት የመጀመሪያ ምእራፍ ተሳክቷል። በሁለተኛው ዙር ደግሞ ኢትዮጵያ 25 ቢሊዮን ችግኞችን ትተክላለች። አረንጓዴ ዐሻራ ለትውልድ የሚተርፍ ቅርስ ነው።

የአየር ንብረት ለውጥን እና የአካባቢ መራቆትን ለመቋቋም የወጠንነው አገር በቀል አካሄዳችን ነው። የሥራ ዕድል ለመፍጠር አንዱ መንገዳችን ነው። እንዲሁም ለምግብ የሚውሉ ዕጽዋትን በመትከል የምግብ ዋስትናችንን የምናረጋግጥበት ሌላው ስልት ነው ይላሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ። እውነት ለመናገር የአረንጓዴ ዐሻራ ከየትኛውም አገራዊ ሜጋ ፕሮጀክት ይበልጥብኛል። አገርንና ኢትዮጵያውያንን ይዞ የሚነሳ ርዕይ ነው።

በመንግሥታቱ ድርጅት የአየር ንብረት ፕሮግራም (ዩኤንኢፒ)አገራችን ኢትዮጵያን ለአየር ንብረት ለውጥ ክፉኛ ከተጋለጡ 10 አገራት አንዷ መሆኗን ይገልጣል። መልሶ ኢትዮጵያውያን ግን የአየር ንብረት ለውጥን ከማያባብሱ ዜጎች ተርታ ይሰለፋሉ ይለናል። ኢትዮጵያውያን በአማካኝ ወደ ከባቢ አየር የሚለቁት ግሪንሀውስ ጋዝ 1.3 ሜትሪክ ቶን ወይም 1300 ኪ.ግ ሲሆን በአንጻሩ የአሜሪካውያን 20ሺህ ኪ.ግ ፤ ኳየታውያን ደግሞ 60ሺህ ኪ.ግ ግሪንሀውስ ጋዝ ወደ ከባቢ አየር ነው።

የቻይናና የሕንድማ አይነሳ ። ይህ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ለከባቢ አየር ሙቀት መጨመር እዚህ ግባ የሚባል ድርሻ የሌላቸው አገራት የበለጸጉ አገራት ከኢንዱስትሪ አብዮት ጀምሮ ወደ ከባቢ አየር በለቀቁት ከፍተኛ መጠን ያለው ግሪንሀውስ ጋዝ በተፈጠረ የአየር ንብረት ለውጥና የከባቢ አየር ሙቀት የተነሳ ለተደጋጋሚ የዝናብ ዕጥረት ፤ ለድርቅና ርሃብ ተዳርገዋል ።

አገራችን ከ1966 ዓ.ም ጀምሮ በየአስር ዓመቱ ይጎበኛት የነበረው ድርቅ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በየዓመቱ የሚከሰት ሆኗል። ዘንድሮ እንኳ በቦረና፣ በሶማሌና በደቡብ ክልል የተከሰተው ድርቅ በእንስሳትና በአርብቶ አደሩ ላይ ያስከተለውን ከፍተኛ ጉዳት አይተናል። በመንግሥት ርብርብ ድርቁ በሰዎች ላይ የከፋ ጉዳት ባያስከትልም የህልውናቸው መሠረት የሆኑ እንስሳቱ ላይ ግን የከፋ ጉዳት አድርሷል። መጠኑ ቢለያይም እንደ 1966ቱ ፤ 77ቱና 87 ሰዎች በርሃብ እንደ ቅጠል አልረገፉም።

የሕዝብ ቁጥር ዕድገቱን የሚመጥን ምርት ባለመመረቱ ፤ በፍላጎትና በአቅርቦት መካከል ያለው ሰፊ ክፍተት ባለመጥበቡ ፤ በሰሜኑ የአገራችን ክፍል ሕወሓት በከፈተው ጦርነትና እዚህም እዚያም በተከሰቱ ቀውሶች ፤ በኮቪድ 19ኝና ራሽያ ዩክሬንን በመውረሯ በተፈጠረ የዋጋ ግሽበቱና የኑሮ ውድነቱ የተነሳ በከተሞች ሳይቀር ኑሮው አልቀመስ ብሏል ።

አገራችን ዛሬ ለምትገኝበት ውስብስብ ችግር በርካታ ምክንያቶችን መደርደር ቢቻልም ዋነኞዎቹ ግን ሁለት ናቸው ። እነሱም አበክረን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አለመገንባታችን ፤ የተፈጥሮ ሀብታችንና የሰው ኃይላችንን በአግባቡ አቀናጅተንና አልምተን አለመጠቀማችን ናቸው ። ሰፊ ለም መሬት ፤ ዓመቱን ሙሉ የሚፈሱ ወንዞች ፤ የከርሰ ምድር ውሃ ፤ ዝናብና ወደ 117 ሚሊዮን ከሚገመተው ሕዝብ 70 በመቶው ወጣት ስለሆነ ከምግብ ዋስትና አልፈን የተትረፈረፈ ምርት አምርተን ኢንዱስትሪውን ፤ የአገልግሎት ዘርፉንና የውጭ ንግዱን ይዘን መነሳት እየቻልን ዛሬም እርዳታን የምንቀላውጥ መሆናችን አንገት ያስደፋል።

ከለውጡ ወዲህ ግን ችግኝ ተከላውን ከግብርና ልማቱ ፤ ከአካባቢ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ጋር መሳ ለመሳ በማስኬድ በአጭር ጊዜ ውስጥ ያልተጠበቀ ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገብ ችለናል ። በ2025 ዓ.ም ደግሞ የግሪንሀውስ ጋዝ ልቀቷን ወደ ዜሮ ለማውረድ ግብ ተጥሎ እየተሰራ ነው። ባለፉት አራት ዓመታት 25 ቢሊዮን ችግኞችን የተከለች ሲሆን የኤሌክትሪክ ፍላጎቷንም ከታዳሽ ኃይል ማለትም ከግድብና ከንፋስ እያገኘች ሲሆን በቀጣይም ከእንፋሎት ለማመንጨትም እየሰራች ትገኛለች።

አገራችን በታሪኳ ከፈጸመቻቸው፤ እየፈጸመቻቸው ካሉ ግዙፉን ፕሮጀክቶች ታላቁን የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ጨምሮ አንድ ላይ ቢደመሩ የ " አረንጓዴ ዐሻራን" ያህል ክብደት አልሰጣቸውም ፡፡ የህዳሴውም ሆነ የሌሎች ታላላቅ ግድቦች ህልውና እንዲሁ 80 በመቶ አገሬው ኑሮ የተመሰረተበት ግብርና እጣ ፈንታ የሚወሰነው ዛሬ በትጋት በምንከውነው የአካባቢ ወይም የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራ ነውና ፡፡ በቀደሙት ሶስት ዓመታት ከ18 ቢሊዮን በላይ አገር በቀል ችግኞችን ለዛውም ከሞላ ጎደል ሥነ ምህዳርን ታሳቢ ያደረጉ በመላው የአገሪቱ ክፍሎች መትከል ተችሏል። ከተተከሉ ችግኞች መካከል እንደ አቡካዶ፣ ማንጎ፣ አፕል፣ ፓፓዬ፣ ሙዝ እንዲሁም ቡና የመሳሰሉት ይገኙበታል። በአራቱም ዙር ከ90 ሚሊዮን በላይ ሕዝብ በችግኝ ተከላው ተሳትፏል።

ከፍ ብዬ ለመግለጽ እንደሞከርሁት ችግኝ መትከል የአየር ንብረት ለውጥን ፤ የዓለም ሙቀት መጨመርን ወይም የአካባቢ ጥበቃ ችግሮቻችን ለመፍታት የማይተካ ሚና አለው። ድህነትን ፤ የምግብ ዋስትና ጉድለትን ፤ የምርታማነት ተግዳሮትን ፤ ድርቅን፣ ርሃብን ፤ የዝናብ መቆራረጥንና መቅረት ፤ የውሃ እጥረትን ፤ የኑሮ ውድነትን ፤ በፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገትና በምርት አቅርቦት መካከል ያለውን ክፍተትት፣ ሥራ አጥነት ፤ ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ ፍልሰትን ፤ የጸጥታና የደህንነት ችግርን ፤ ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ የሚደረገውን ሽግግር በማሳለጥ እና ሁለንተናዊ ብልፅግናን ለማለም መስፈንጠሪያ በመሆን ያገለግላል። ለዚህ ነው ችግኝ ተከላን የችግሮቻችን ሁሉ መፍቻ ማስተር ኪይ ነው የምለው፡፡

በየዓመቱ በአገራችን ከ92ሺህ ሔክታር መሬት በላይ ደን ይመነጠራል። ይጨፈጨፋል። በዚህ የተነሳ የደን ሽፋናችን ከ50 ዓመታት በፊት ከ35 በመቶ ከነበረበት ደረጃ ወደ ሶስት በመቶ አሽቆልቁሎ ነበር። ለዝናብ እጥረት ፤ ለድርቅና ለከባቢ አየር ሙቀት ተዳረግን። በየዓመቱ ምርታችን ከ10 በመቶ በላይ መቀነስ ጀመረ ። በየዓመቱ ከ35 እስከ 40 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይቀንሳል። ሆኖም ባለፉት አራት ዓመታትም ሆነ ከዚያ በፊት በተከናወኑ የችግኝ ተከላና የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎች የደን ሽፋኑን ወደ 17 በመቶ ማገገሙ ይበል የሚያሰኝ ነው።

የበጋ ስንዴ ፤ የኩታ ገጠም ግብርናን ፤ በተወሰነ ደረጃ ሥነ ምህዳርን ታሳቢ ያደረገ የቴክኖሎጂና የሜካናይዜሽን እገዛ ፤ የከርሰና የገጸ ውሃን አሟጦ የመጠቀም ፤ ፍራፍሬና አትክልት ላይ ለመስራት ፤ በተለይ ከአለፈው ዓመት ጀምሮ የከተማ ግብርና ትኩረት ማግኘቱ ፤ በአርብቶ አደሩ የሚገኙ ጦም ያደሩ ሰፋፊ መሬቶችን በመስኖ ለማልማት አበረታች ጥረትና ርብርብ መደረጉ እና ከውጭ የሚገባውን ስንዴ ማስቀረት መቻሉ የአተያይ ለውጥ በማምጣቱ ተስፋ ያስቆረጠን ግን ደግሞ ብቸኛ ሊባል በሚችለው ግብርና ከምግብ ዋስትና ባሻገር ተስፋችንን እንድናድስ አድርጎናል፡፡ ለዚህ ነው ተስፋ ሰጪ ጅምር እውቅና መስጠት የሚያስፈልገው፡፡

ችግሮቻችንን ሁሉ ፈታተን ፤ በታትነንና አገላብጠን ብንመረምራቸው አብዛኞዎቹ ከአንድ ቅርጫት የሚገኙ ናቸው ፡፡ የተፈጥሮ ሀብታችንን በአግባቡ ካለመንከባከብ ፤ ካለመጠበቅና ካለማልማት ቅርጫት። የዓለም ሙቀት መጨመርን ተከትሎ በመጣ የአየር ንብረት ለውጥ የተነሳ የተፈጥሮ ሀብታችን እየተጎሳቆለ በመምጣቱ ማለትም መሬታችን የተራቆተ ፤ ዝናባችን የአጠረና የተቆራረጠ በመሆኑ የከርሰና የገጸ ምድር ውሃችን በመመናመኑ ግብርናው ውጤታማ ሊሆን አልቻለም ፡፡

በዚህ የተነሳ በግብርና ላይ የተመሰረተው የዜጋው ሕይወት ፤ የአገሪቱ ልማት ችግር ላይ ወድቋል ፡፡ ይህ የሀብት ውስንነትን ፈጥሯል ፡፡ በዚህ የተነሳ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮች ከዓመት ዓመት እየተባባሱ መጡ፡፡ እነዚህን ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት ደግሞ የተፈጥሮ ሀብታችን እንዲያገግም ሌት ተቀን መሰራት አለበት፡፡ መሬት ማገገም ፤ ውሃ መያዝ አለባት፡፡ ይህ ደግሞ እውን ሊሆን የሚችለው ችግኝ በመትከልና የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎችን በስፋት በማከናወን ነው፡፡ "አረንጓዴ ዐሻራ" የበሽታውን ምልክት ከማከም ይልቅ መነሻውን በማያዳግም ሁኔታ የመፈወስ አቅም እንዳለው በማመን ነው፤ "አረንጓዴ ዐሻራ !" የእንቆቅልሾቻችን ሁሉ መፍቻ ቁልፍ (ማስተር ኪይ) የምለው ፡፡

ለዚህም ነው 31 ቢሊዮን ችግኞችን መትከል ከቁጥርና ከአኃዝ በላይ በየዓመቱ የሚከሰተውን ድርቅ፣ የበርሃማነት መስፋፋት ፤ የአፈር መከላት ፤ የዝናብ ዕጥረትና መቆራረጥ ፤ የገጸና የከርሰ ምድር ውሃ መቀነስን በመከላከል ፤ የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ ባሻገር ከተመጽዋችነት የመላቀቅ የማሪያም መንገዳችን፤ ሉዓላዊነታችን ሙሉኡ ማድረጊያችን፤ የአገሪቱ ሁለንተናዊ ብልጽግና ማርሽ መቀየሪያ ፤ አስተማማኝ ሰላም ማስፈኛችን ፤ እውነተኛ አንድነትና እርቅ ማረጋገጫችን ፤ ወዘተረፈ ስለሆነ አረንጓዴ ዐሻራ ከአኃዝ በላይ ከመሆኑ ባሻገር ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳሉትም እንደ አገርና ሕዝብ ብቸኛ መዳኛችን ነው።

የአራት ዓመቱ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብርን መጠናቀቅ አስመልክቶ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ያስተላለፉት መልዕክትም የአረንጓዴ ዐሻራው 25 ቢሊዮን ችግኝ ተተክሏል ከሚለው የአኃዝ ዜና በላይ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው ።

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ የአራት ዓመቱ የአረንጓዴ ዐሻራ ዘመቻ መጠናቀቅን አስመልክተው ባለፈው ዓመት ባወጡት መግለጫ በአረንጓዴ ዐሻራ ሥራዎች ከችግኝ ማፍላት እስከ እንክብካቤው 25 ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን መሳተፋቸውን ፤ በኢትዮጵያ ሲካሄድ የቆየው የአረንጓዴ ዐሻራ ዘመቻ በአገሪቱ አረንጓዴ ባህልን በመፍጠር ስኬታማ መሆኑን መግለጻቸውን የኢትዮጵያ ፕሬስ ኤጀንሲ ዘገባ ያወሳል።

ኢትዮጵያ የከተሞቿን የአረንጓዴ ሽፋን ለማሳደግ የአረንጓዴ ዐሻራ ዘመቻን መጀመሯን ፤ ለአራት ዓመት በቆየው ዘመቻ 20 ቢሊዮን ችግኞችን ለመትከል ወጥና ብትነሳም ፤ ዜጎቿ 25 ቢሊዮን ችግኞችን በመትከል ካስቀመጡት ግብ በላይ ፈጽመዋል ። የአረንጓዴ ዐሻራ ዘመቻው ሲጀመር 40 ሺህ ብቻ የነበሩት የችግኝ ማፍያዎች አሁን ላይ ወደ 121 ሺህ ማደጋቸውንና በዓመት ሰባት ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ችግኝ የማፍላት አቅም ላይ መደረሱን ፤ አረንጓዴ ባህልን ከመፍጠር ባለፈ ዘመቻው ለ767 ሺህ ዜጎች የሥራ ዕድል በመፍጠር ያበረከተውን ኢኮኖሚያዊ አስተዋፅኦም ማንሳታቸውን የኤጀንሲው ዘገባ ያመለክታል ።

ከዚህ ባለፈ ለችግኝ ተከላ የሚያስፈልጉ ቦታዎችን በመምረጡ እና ለተከላ በማዘጋጀቱ ረገድም የታየው ውጤት አበረታች መሆኑን ፤ በመላው አገሪቱ የሚገኙ ከተሞች አሁን ላይ የአረንጓዴ ስፍራ አስፈላጊነትን ተረድተው ቦታ እያዘጋጁ መሆኑ ለተፈጠረው አረንጓዴ ባህል ማሳያ ነው ። የአረንጓዴ ዐሻራ ባህል ለቀጣዩ ትውልድም የሚቆይ መሆኑን ፤ በዚህ ስኬት ውስጥ የፖለቲካ ፍላጎት እና ቁርጠኝነት ቁልፍ ሚና መጫወቱን ፤ በአረንጓዴ ዐሻራ መርሀ ግብሩ በርካቶች መሳተፋቸውን ፤ አሁንም ብዙ ሥራ የሚጠበቅብን ቢሆንም ንቅናቄው በአገሪቱ ፍሬ እንዳፈራ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አስታውቀዋል ።

ያለፉትን ጥቂት ሳምንታት ብቻ በዓለም ዙሪያ የተስተዋሉት የጎርፍ አደጋ ፤ የደን ቃጠሎ ፤ ኃይለኛ ማዕበል እና ያልተለመደ ሙቀትን የመሰሉ ሁኔታዎች ለአየር ንብረት ለውጥ ዓይነተኛ ማሳያዎች መሆናቸውን፤ የአፍሪካ ቀንድ ያስተናገደው ድርቅ የዚሁ የአየር ንብረት ለውጥ ውጤት መሆኑን ፤ በኢትዮጵያም የአየር ንብረት ለውጥ የውሃ ምንጮችን ማድረቁን በአንዳንድ የአገሪቱ ክፍሎችም የድርቅ አደጋን ማስከተሉን ፤ አሁን ላይ ዓለም እየተሰቃየ ያለበትን ይህን ችግር ለመፍታት ከስብሰባዎች ያለፈ ተግባራዊ መፍትሄ መውሰድ ያስፈልጋል ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ማሳሰባቸውን ኤጀንሲው ዘግቧል ።

አገሪቱ የታዳሽ ኃይል በሆኑት የውሃ ፤ ንፋስ ፤ ፀሐይ እና የእንፋሎት የኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች ላይ የምታውለው መዋዕለ ንዋይ የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል በበኩሏ እየተወጣች የምትገኘው ኃላፊነት መሆኑን ፤አሁንም ብዙ ሥራ ቢጠበቅም በአገሪቱ አረንጓዴ ባህልን በመፍጠሩ ረገድ ዘመቻው እንደተሳካ፤ አፍሪካ ብሎም ዓለም ተፅዕኖው እየከፋ የመጣውን የአየር ንብረት ለውጥ ለመከላከል ልክ እንደ ኢትዮጵያ ተግባራዊ የአረንጓዴ ዐሻራን በመፍትሄነት ሊጠቀሙ እንደሚገባ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ መልዕክት አስተላልፈዋል ።

አረንጓዴ ዐሻራ የሕዳሴያችን ዋልታና ማገር ነው !

ሻሎም ! አሜን ።

# ወቅታዊ

# «ከጋምቤላ ነፃ አውጪ ግንባር ጋር ሠላም በመፈጠሩ፤ በአንዳንድ ቦታዎች የነበሩ ወንጀሎች ቀርተዋል»

- አቶ ቸንኮት ቾት
የጋምቤላ ክልል ሠላምና ፀጥታ ቢሮ ኃላፊ

**ክፍለዮሐንስ አንበርብር**

ከጥቂት ዓመታት በፊት የጋምቤላ ክልል በርካታ ፀረ ሠላም ኃይሎች የሚንቀሳቀሱበት ክልል የነበረ ሲሆን፤ በርካታ ንጹሃንም ለህልፈት መዳረጋቸው ይታወሳል። በተለይም የጋምቤላ ነፃ አውጪ ግንባር እና ከዚህ ቡድን ጋር አብረው የሚሰሩ አካላት የክልሉን ኢንቨስትመንት፣ ሰላምና ደህንነት አደጋ ውስጥ ጥለውበት የቆዩ መሆኑ የቅርብ ዓመታት ትውስታ ነው።

ሆኖም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የጋምቤላ ነፃ አውጪ ግንባር የሠላም ሥምምነት ከተፈጠረ በኋላ እፎይታ ስለመገኘቱ እየተገለፀ ይገኛል። በክልሉ ያለስጋት ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ መንቀሳቀስ ስለመቻሉም እየተጠቆመ ነው። ቀደም ሲል የነበረው ስጋት በከፍተኛ ደረጃ ቀንሷል።

ይህ ቡድን በሰላማዊ መንገድ ለመታገል መሞከሩ ክልሉን የተረጋጋ እንዲሆን እያስቻለው ነው። በአሁኑ ወቅት ከአንዱ ወረዳ ወደ ሌላ ወረዳ ለመንቀሳቀስ ዋስትና የሚሰጡ ሁኔታዎች እየተስተዋሉ ሲሆን፤ ይህ ህብረተሰቡን እንዲረጋጋ አድርጎታል።

ቀደም ባሉት አመታት በክልሉ ይፈጠሩ ከነበሩ ሁኔታዎች መካከል ለአብነት ሚያዚያ 7 ቀን 2008 ዓ.ም ከደቡብ ሱዳን በመጡ ሙርሌ ጎሳዎች በጋምቤላ ክልል የተፈጠረው የነዋሪዎች ሞት ይታወሳል። በተጨማሪ ልጆች እና እንስሳት ተወስደዋል፤ ታግተዋልም። ይህን ችግር ለመመከት በወቅቱ የአገር መከላከያ ሰራዊት፣ ፌደራል ፖሊስ፣ የጋምቤላ ክልል የፀጥታ መዋቅር በሙሉ ከፍተኛ ትግል ማካሄዳቸውም ይታወሳል። በዚህም በርካታ ልጆች እና እንስሳት የተመለሱ መሆናቸውም ይታወቃል።

በሌላ በኩል ደግሞ ከደቡብ ሱዳን ከኢትዮጵያ ጋር በሰፊ ከሚዋሰኑ አገራት መካካል አንዷ ስትሆን፤ በዚህ በሚዋሰኑ አካባቢዎችም በርካታ ችግሮች ሲፈጠሩ መቆየታቸውም ይታወቃል። ለዚህም በርካታ ምክንያቶች የሚነሱ ሲሆን፤ ከደቡብ ሱዳን ጋር ያለው የመልክዓ ምድር አቀማመጥና የጸረ ሠላም ኃይሎች እንቅስቃሴ ለችግሩ መባባስ አንድ ምንጭ መሆኑም ይጠቀሳል። በዚህ አካባቢም ዘርፈ ብዙ ወንጀሎች የሚከሰቱ ስለመሆኑም በተደጋጋሚ ይነገራል። ድንበር ዘለል ወንጀል መባባሱም በእዚህ የተነሳ ስለመሆኑም የዘርፉ ባለሙያዎች ጭምር የሚያስረዱት ነው።

የሙርሌ ጎሳዎች ደግሞ ከኢትዮጵያ ተነስተው ደቡብ ሱዳን ድረስ የሚዘልቁ ወንዞችን ተገን አድርገው ወደ ኢትዮጵያ ይገባሉ። አብዛኞቹም ወንዙን ተከትለው የሚመጡ ናቸው። አካባቢው በተፈጥሮ ደንም የታደለ ስለመሆኑ ይነገርለታል። አካባቢው በጣም ሰፊና እና ጥቅጥቅ ያለ ጫካ አለ። በዚህ አካባቢ ደግሞ ፀረ ሰላም ኃይሎች ሾልከው የሚገቡበት አጋጣሚም ይፈጠራል።

በድንበር አካባቢ ወንዝ እና ጫካ አለ። በዚህ ህዝቡ እንደፈለገው መውጣት እና መግባት ይችላል። ነገር ግን ድንበሩን ለመቆጣጠር እና የጸጥታ መዋቅሩን ለማጠናከርም ዘርፈ ብዙ ተግባራት ሲከናወኑ መቆየታቸውንና በአሁኑ ወቅትም እየተከናወነ መሆኑ ይነገራል።

አዲስ ዘመን ከጋምቤላ ክልል ሠላምና ፀጥታ ቢሮ ኃላፊ አቶ ቸንኮት ቾት ጋር የክልሉን አጠቃላይ የሠላምና ፀጥታ ሁኔታ፣ ቀደም ሲል በተከናወኑ ተግባራት የተገኙ ውጤቶች ብሎም በቀጣይ ሊከናወኑ የታሰቡ ተግባራትን አስመልክቶ ቃለ መጠይቅ አድርጎ ፤ በዚህ መልኩ አቅርቦታል።

**አዲስ ዘመን፡- አሁናዊ የጋምቤላ ክልል ሠላምና ፀጥታ እንዴት ይገለፃል?**

**አቶ ቸንኮት፡-** የክልሉ አሁናዊ የሰላምና ጸጥታ ሁኔታ በጣም የተረጋጋ ነው። ሰሞኑን የተወሰነ ግጭት ለመፍጠር የሞከሩ አካላት ነበሩ፤ ከሚመለከታቸው ጋር በመቀናጀት በፍጥነት ወደ ህጋዊ መስመር እንዲገቡ አድርገናል።



“

**በጋምቤላ ክልል**
**የትኛውም አቅጣጫ ለመንቀሳቀስም ሆነ ለመውጣትና ለመግባት አስቸጋሪ ሁኔታ የለም። ይህም በጥረትና በትዕግስት በመሥራት የመጣ ውጤት ነው። ለዚህ ደግሞ ህብረተሰቡ ትልቅ ድርሻ አለው**

በክልሉ ዘላቂ ሰላም ለማስፈን አገር ሽማግሌዎችን ጨምሮ ከበርካታ ወጣቶች ጋር በተለያዩ ደረጃዎች መክረናል። በዚህም የታሰበውን ውጤት ማምጣት ችለናል። የማረጋጋት ሥራዎችን ሰርተን ውጤታማ ሆነናል። በፀጥታው ዘርፍ ላይ የሚሰሩት አካላት በሙሉ ተናበው ሲሰሩ ቆይተዋል። በአሁን ወቅት የአገር መከላከያ ሰራዊት፣ የፌደራል ፖሊስ፣ የክልሉ ፖሊስ እና ሌሎች የፀጥታ መዋቅሮችም ተናበው እየሰሩ ናቸው። በዚህም ችግሮች ሲያጋጥሙ በፍጥነት ለመቆጣጠር አስችሎናል ።

በአሁኑ ወቅት በጋምቤላ ክልል የትኛውም አቅጣጫ ለመንቀሳቀስም ሆነ ለመውጣትና ለመግባት አስቸጋሪ ሁኔታ የለም። ይህም በጥረትና በትዕግስት በመሥራት የመጣ ውጤት ነው። ለዚህ ደግሞ ህብረተሰቡ ትልቅ ድርሻ አለው።

**አዲስ ዘመን፡- በክልሉ ያሉ ግጭቶች እና የፀጥታ ችግር መነሻ ምክንያት ምንድን ነው?**

**አቶ ቸንኮት፡-** በክልሉ ቀደም ሲል ይንቀሳቀሱ የነበሩት ይታወቃሉ። ለአብነትም የጋምቤላ ነፃ አውጭ ግንባር አንዱ ነው። የአሁኑ ግጭት ግን ከእነዚህ ጋር የሚገናኝ አይደለም። ይህ ቡድን ትጥቅ ፈትቶ በሰላማዊ መንገድ ለመኖር እና ለመታገል ወደ ህብረተሰቡ ተቀላቅሏል። የተለያዩ ጥርጣሬዎች እና ግምቶች ቢኖሩም ተፈጥሮ የነበረው ግጭት መነሻው የጋምቤላ ነፃ አውጭ ግንባር ነው የሚል ግምገማ የለንም።

**አዲስ ዘመን፡- በቅርቡ ከጋምቤላ ነፃ አውጪ ግንባር ጋር የሠላም ሥምምነት መደረጉ ይታወሳል። በህብረተሰቡ ዘንድ የነበረው ስሜትና ያገኛችሁት ምላሽ ምን ይመስላል?**

**አቶ ቸንኮት፡-** እንግዲህ ከዚህ ቡድን ጋር የተደረገው ሥምምነት ውጤታማ ነው። የመጀመሪያው ሥራችን ከማህበረሰቡ ጋር ተቀራርቦ መነጋገርና መወያየት ነው። በዚህም ሁላችንም የሚጠበቅብንን እየሠራን ቆይተናል። የጋምቤላ ነፃ አውጪ ግንባር በሰላማዊ መንገድ ወደ ክልሉ ገብቷል። ይህ ብዙ ስጋቶችን ቀንሷል።

**አዲስ ዘመን፡- ምን ዓይነት ስጋቶችን ቀነሰ?**

**አቶ ቸንኮት፡-** የጋምቤላ ነፃ አውጪ ግንባር ሠላም ሥምምነት ከተፈጠረ በኋላ እፎይታዎች ተገኝቷል። ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ መንቀሳቀስ ተችሏል። ቀደም ሲል የነበረው ስጋት አሁን የለም። ከአንዱ ወረዳ ወደ ሌላ ወረዳ ለመንቀሳቀስ በትራንስፖርት ላይም ሆነ በመንገድ ላይ የሚፈጠር ችግር የለም። ይህ ህብረተሰቡን እንዲረጋጋ አድርጎታል።

በክልሉ የሚንቀሳቀሱ ሌሎች ፀረ ሰላም ኃይሎችም የሚተባበራቸው አካል ባለመኖሩና አመቺ ሁኔታ ባለማግኘታቸው በራሳቸው ጊዜ ከክልሉ እየተገፉ ነው። ግንባሩ የሰላም ጥሪውን ተቀብሎ ወደ ሰላማዊ ትግል መምጣቱ እንደ ክልል በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት።

በዋነኝነት ከዚህ ቀደም በተለያዩ ቦታዎች አንዳንድ የጸጥታ ችግሮች እየተከሰቱ የክልሉ ነዋሪዎችም ሆኑ ከተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች ወደ እኛ በመምጣት የሚንቀሳቀሱ ዜጎች ሰላም አደጋ ላይ ነበር። የየዕለት ሥራቸውን በተረጋጋ ሁኔታ ለመከወን የሚችሉበት ሁኔታም አልነበረም።

ቡድኑ እንቅስቃሴውን ያደርግ የነበረው በጫካ አካባቢ በመሆኑ አርሶ አደሩ በነጻነት የእርሻ ስራውን ማከናወን አስቸጋሪ ስለሚሆንበት ከሰላሙ በተጨማሪ

ወደ ገፅ 8 የዞረ

# ወቅታዊ

## «ከጋምቤላ ነፃ አውጪ ግንባር ...

ከገጽ 7 የዞረ

በምርታማነቱም ላይ ችግር ፈጥሮ ነበር። በአጠቃላይ ዜጎች ይንቀሳቀሱ የነበረው በስጋት ውስጥ ነበር።

አሁን ግን ከጋምቤላ ነፃ አውጪ ግንባር ጋር ሰላም በመፈጠሩ ግድያን ጨምሮ በአንዳንድ ቦታዎች የነበሩ ወንጀሎች ቀርተዋል። እንደ ክልልም የነበረው ስጋት በመቀረፉ ክልሉ በዚህ ረገድ ያለበትን የሰላም ችግር ሙሉ ለሙሉ ማስወገድ ተችሏል።

**አዲስ ዘመን፡- የቀነሰውን ስጋት በምሳሌ አስደግፈው በደንብ ያብራሩልኝ?**

**አቶ ቸንኮት፡-** በርካታ ስጋቶች ቀንሰዋል። አሁን ከሌሎች ፀረ-ሠላም ኃይሎች ጋር አብረው በመተባበር አይሰሩም። ቀደም ሲል በጫካ ውስጥ ግድያ ነበር፤ አሁን ግን ይህ የለም። ህገ-ወጥ የጦር መሳሪያ ዝውውር እና የመሳሰሉትን ተያያዥ ወንጀሎችን ለመፈፀም ይጠቀሙበት ነበር። ይህንንም በብዛት ማስቀረት ተችሏል።

ቀድሞ ከነበረው ግጭት በመውጣት አሁን ሰላማዊ ህይወት ቀጥሏል። በጫካ ውስጥ የነበረው ወንጀል በከፍተኛ ደረጃ በመቀነሱ የህብረተሰቡም ስጋት ቀንሷል። በዚህ መልኩ ብዙ ስጋቶች መቀነሳቸውን እንደማሳያ መጥቀስ ይቻላል።

**አዲስ ዘመን፡- ስጋቱን ከመቀነስ ጎን ለጎን ለቡድኑ ታጣቂዎች የተሃድሶ ስልጠና ተሰጥቷል?**

**አቶ ቸንኮት፡-** አዎ! እነዚህ ታጣቂዎች ከአንድ ወር በላይ የተሃድሶ ስልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል። በተሃድሶው አገራዊ ህገ-መንግስቱን በተመለከተ እና መከበር ስለሚገባቸው ህጎች በሚገባ ሰልጥነዋል። የሠላም ዕሴት ግንባታ እና አስፈላጊነት እስከምን ድረስ ነው? የሚለው ላይም በሰፊው የተሃድሶ ስልጠና ወስደዋል። ልምዶች እና ህጎችን እንዳይቀላቀሉም ስልጠናዎችን በሰፊው ተሰጥተዋል።

**አዲስ ዘመን፡- ከውስጣዊ ችግሮች በተጨማሪ ከደቡብ ሱዳን የሚነሱ የሙርሌ ጎሳዎች ተደጋጋሚ ጥቃት የክልሉ ጸጥታ ስጋት ነበር። በዚህ ዓመትስ?**

**አቶ ቸንኮት፡-** የሙርሌ ጎሳዎችን ጥቃት በተመለከተ በተለያዩ መድረኮች እያነሳን ነው። እስካሁን ሁነኛ መፍትሄ አልተገኘም። በአሁኑ ወቅትም ጭምር በአኙዋኽ ዞን የእነዚህ ጎሳዎች እንቅስቃሴ አለ። በኑዌር ዞንም የሙርሌ ጎሳ ጥቃት እና እንቅስቃሴ አልፎ አልፎ ይስተዋላል። እነዚህ ጎሳዎች በተበታታነ መንገድ ይመጣሉ። አንዳንዴ ደግሞ ተደራጅተው ይመጣሉ። ሆኖም ጉዳት ከማድረስ አልታቀቡም። እኛም የሚያደርሱትን ጉዳት ዝም ብለን እየተመለከትን አይደለም። ባለን የፀጥታ መዋቅር እየመለስናቸው ነው።

ይህም ሆኖ በቅርቡ በኑዌር ዞን ላይ ትልቅ ጥቃት አድርሰዋል። የአስር ሰዎችም ሕይወት አልፏል። በአኮቦ ወረዳም በተመሳሳይ ችግር ነበር። እስካሁንም የእነዚህ አካላት እቅስቃሴ አለ። እኛም በሚሊሻዎች እየተጠቀምን ነው። ሚሊሻዎቻችን በየጫካው አሰሳ ያደርጋሉ። እስካሁን ድረስም ሚሊሻዎቻችን በየጫካው ይገኛሉ። ይህ ሁሉ ጥረት በቂ አይደለም።

**አዲስ ዘመን፡- የሚደረገው ጥረት በቂ ያልሆነበት ምክንያት ምንድን ነው?**

**አቶ ቸንኮት፡-** ከደቡብ ሱዳን ጋር ሰፊ ድንበር እንዋሰናለን። በጣም ሰፊ ከመሆኑም የተነሳ ክፍት ነው። በዚህ አካባቢ በሰፊው ህገ ወጥ የጦር መሳሪያ ለማስገባት ጥረት ይደረጋል።

ድንበሩ ክፍት በመሆኑ ሙሉ ለሙሉ መጠበቁ አስቸጋሪ ነው። ወሳኝ የሆኑ ቦታዎችና ለኮንትሮባንድ አመቺ ይሆናሉ ተብለው በሚታሰቡ አካባቢዎች የተጠናከረ ጥበቃ ይደረጋል። እንደዚህም ሆኖ የሚያደርሱትን ጥቃቶችና ችግሮች ሙሉ ለሙሉ ማስቆም አልተቻለም።

እስካሁን ችግሮችን መመከት የቻልነው የራሳችንን ኃይል በማጠናከር ነው ። በአሁኑ ወቅት የአገር መከላከያ ሰራዊት ወደ ድንበር አካባቢ በሰፊው በመንቀሳቀስና ከሚሊሻዎቻችን ጋር ተናበው እየሰሩ በመሆናቸው ብዙ ለውጦች እየተመዘገቡ ነው።

በሚደረገው ጥረት ሙሉ ለሙሉ የእነዚህን ጎሳዎች ጥቃት ማስቆም አልተቻለም። እንደሚታወቀው በአገራዊ ሪፎርሙ ሥራ መሰረት የክልላችን ልዩ ኃይል ወደ ሪፎርም የገባ በመሆኑ ክፍተት አለ። እነዚህን ሃይሎች የሚተካ ሌላ የፀጥታ ኃይል እንዲመደብ ከሚመለከታቸው የፌዴራል መንግስት አካላት ጋር ተነጋግረን ነበር። በዚህም መሰረት



የተመደቡ የፌደራል ፖሊስ አባላት አሉ።

የአገር መከላከያ ሰራዊት አባላትም አሉ። ይሁንና ግን ካለው ወቅታዊ ሁኔታ አኳያ የተመደበው ኃይል በቂ አይደለም። በዚህ ላይ ክፍተቶች አሉ። በሂደት ግን በተነጋገርነው መጠን እንደሚገቡ ይጠበቃል። በእንቅስቃሴ ላይም በርካቶች እንዳሉ ይታወቃል። ይህ ከሆነ የሚገመተው ስጋት እንዳይደርስ ያደርጋል። ይህም ብቻ ሳይሆን የሙርሌ ጎሳዎችን ጥቃት ከመከላከል አልፎ ያሰቡትን በፍፁም እንዳያሳኩ የማድረግ አቅም መፍጠር ይቻላል።

**አዲስ ዘመን፡- በችግሩ ዙሪያ ከደቡብ ሱዳን የአገር ሽማግሌዎች ጋር ለመምከር አልተሞከረም?**

**አቶ ቸንኮት፡-** የደቡብ ሱዳን የአገር ሽማግሌዎች ጋር ለመወያየት ብቻችንን አንወስንም። በሁለቱ አገራት መካከል የሚደረገው ግንኙነት የሚወስነው የፌደራል መንግስት መሆኑ ይታወቃል። በመሆኑም በተወሰነ ደረጃ በድንበር አካባቢ የምንወያይበት መንገድ ቢኖርም እኛ በራሳችን ስልጣን ብቻ የምናደርገው የለም። ይህ በራሱ በጥንቃቄ መያዝ ያለበት ጉዳይ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የእነዚህን ጎሳዎች ጥቃት ለመመከትና ድንበር አካባቢ ጥበቃ አስተማማኝ ለማድረግ ምን መደረግ አለበት ይላሉ?**

**አቶ ቸንኮት፡-** በኢትዮጵያ እና ደቡብ ሱዳን ድንበር አካባቢ የተጠናከረ ጥበቃ ማድረግ ይገባል። ችግሩን በአንድ ጊዜ ማጥፋት እንደማይቻል እሙን ነው። ነገር ግን በተናበበ እና በተጠናከረ ጥበቃ ችግሩን በከፍተኛ ደረጃ ማቃለል እንችላለን። ይህን ለማድረግ ደግሞ የክልሉ መንግስት ብቻ ሳይሆን የፌደራል መንግስት ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። ከዚህም በተጨማሪ የደቡብ ሱዳን መሪዎችም ድንበር አካባቢ ያለውን ችግር በመገንዘብ መተባበር አለባቸው። በአጠቃላይ የጸጥታ ኃይሎች የተጠናከረ ሥራ መሥራት ይጠበቅባቸዋል። በዚህ ላይ እኛም አቅደን እየሰራን ነው።

**አዲስ ዘመን፡-የክልሉን ሠላም ከሚያደፈርሱት ኃይሎች መካከል አንዱ ከፍተኛ የሆነ የስደተኞች ቁጥር በክልሉ መኖሩና ከካምፕ በመውጣት በሁሉም የክልሉ ከተሞች መንቀሳቀሳቸው እንደሆነ ይነገራል። በዚህ ጉዳይ እርስዎ ምን ይላሉ?**

**አቶ ቸንኮት፡-** የስደተኞች ጉዳይ ብዙ ስጋት አይሆንም። ነገር ግን በክልላችን ያለው የስደተኞች መጠለያ ካምፕ በሌሎች ዓለማት እንደምናየው አይደለም። በሌሎች አገራት የስደተኞች ካምፕ የራሱ የሆነ አጥር አለው። ለብቻው ይከለላል። ወደ ከተማ ለመሄድ ከተፈለገም ዝም ብለው አይገቡም፤ ከተማ ውስጥ የሚገቡት ፍቃድ ሲሰጣቸው ብቻ ነው። ነገር ግን በጋምቤላ እንደዚህ ዓይነት አካሄድ የለም። ስደተኞች እንደፈለጉ ይገባሉ፤ እንደፈለጉም ይወጣሉ። ይህ የሆነው ደግሞ ካምፖቹ በጣም ሰፊ ከመሆናቸው የተነሳ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ምን ያክል ስደተኞች በክልሉ አሉ፤ የፀጥታ ስጋትስ አልሆኑም ማለት ነው?**

> **የ** **ክልላችን ሠላም ለማረጋገጥ ብሎም የኢትዮጵያ ሰላም እውን ለማድረግ ሁላችንም ትልቅ ኃላፊነት አለብን። ህብረተሰቡ ደግሞ የፀጥታ ኃይል ዋነኛ አጋዥ በመሆኑ ሊተባበር ይገባል። ይህን ማሳካት ከተቻለ እና መናበብ ካለ የሚፈለገው ሠላም ይሰፍናል**

**አቶ ቸንኮት፡-** እኔ ቁጥራቸውን በትክክል አላውቅም። ይህን የሚቆጣጠረው ሌላ አካል ነው። ነገር ግን ቁጥራቸው ይብዛ እንጂ ለክልሉ የጸጥታ መዋቅር ስጋት ሆነው አላገኘናቸውም።

**አዲስ ዘመን፡- ከአጎራባች ክልሎች ጋር ያላችሁ ግንኙነት፣ በፀጥታ እና የጋራ ጉዳዮች ላይ ያላችሁ መስተጋብር ምን ይመስላል?**

**አቶ ቸንኮት፡-** እኛ ከአጎራባች ክልሎች ጋር የተሻለ መቀራረብ እና መነጋገር አለ። አንጻራዊ ሠላም አለ። ከኦሮሚያ ክልል፣ ከደቡብ ምዕራብ ክልል፣ ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ጋር እንዋሰናለን በጋራ ጉዳዮችም ጋር እንነጋገራለን። የጋራ መድረኮች አሉን። የህዝብ ለህዝብ ግንኙነቶችም አሉን። በአሁኑ ወቅት ከሁሉም ክልሎች ጋር ያለው የሠላም ሁኔታ በጣም ጥሩ የሚባል ነው። በየመድረኮቹም የሚነሱት እና የተገኙትም ነጥቦች አንድነትን ማጠናከር እንደሚገባ የሚያሳይ ነው። ለዚህ ደግሞ ህብረተሰቡ በጣም ይተባበራል። እኛም ይህንን ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚጠበቅብንን ሥራ እያከናወንን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በክልሉ ከዚህ ቀደም በየዓመቱ ተደጋጋሚ ግጭቶች እየተከሰቱ የበርካታ ዜጎች ህይወት ማለፉን ይሰማ ነበር። በአሁኑ ወቅት ግን ማንነትን መሰረት ያደረጉ ግጭቶች እየተስተዋሉ አይደለም። በአንጻሩ የተሻለ የሰላም ሁኔታ እየታየ ነው። ይህ እንዴት ሊመጣ ቻለ ?**

**አቶ ቸንኮት፡-** እንግዲህ ከዚህ በፊት የነበረው የአኟክ እና የኑየር ግጭት የተዛባ አመለካከት በማህበረሰቡ ውስጥ የነበር በመሆኑ የተፈጠረ ነው። በዚህም አንድ ሰው መሪ ሲሆን፤ ማንነቱን የማስቀደም ነገር ነበር። ይሄ ግን ያለፈ ነገር ነው። ከለውጡ ወዲህ ግን የተደረገ ትልቅ ለውጥ አለ። የለውጡ መሪዎች የውስጥ ፓርቲ አንድነት ተከትለን በእህትማማችነት እና በወንድማማችነት በህብረት በጀመርነው ጉዞ ያለፈውን አራት አመት ያለ ምንም የጎላ ችግር ማሳለፍ እና ለህብረተሰቡም ሰላምን ማስፈን ችለናል።

ባለፉት አራት አመታት ምንም ግጭት ተፈጥሮ ያልነበረ ቢሆነም፤ በቅርቡ በአንድ ሁለት ቀበሌዎች አካባቢ በኑየር እና አኟክ መካከል በተፈጠረ ችግር በከተሞች ረብሻ ተከስቶ ነበር። በአሁኑ ወቅት ግን ሁሉም ነገር ተረጋግቶ አካባቢው ወደቀደመ ሰላም መመለስ ተችሏል። ይህም የሆነው በአጭር ግዜ በውስጥ ኃይል ብቻ በተሰራው ሰፊ ርብርብና ሥራ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ለተፈጠረው ችግር ተጠያቂነት ለማስፈን ምን እየተሰራ ነው?**

**አቶ ቸንኮት፡-** ሠላምን ለማስቀጠል የብልጽግና መስመርን በመያዝ በወንድማማችነትና እህትማማችነት ህብረታችንን በማጠናከር መንግስት በራሱ የጸጥታ አካላት ሠላም በማስከበር የህግ የበላይነትን የሚያረጋግጥ ይሆናል። ከዚሁ በተጓዳኝም አጥፊዎችን በህግ ተጠያቂ የማድረግ ስራም የሚሰራ ይሆናል። በአሁኑ ወቅት የፖሊስ ሚና ምን መሆን አለበት በሚለው ላይ ግምገማ እየተካሄደ ነው። በዚህም በግጭት ወቅት ፖሊሶች ሲሰሩ የነበሩትን ነገር በመገምገም የነበራቸውን ሚና በመለየት፤ በየወረዳው ተጠያቂ የሚሆን ካለ በህጉ መሰረት የሚጠየቁበት አግባብ ይኖራል። ይህ የህግ የበላይነት የማስከበሩ ስራ ወደፊትም ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል።

**አዲስ ዘመን፡- የተደረጉ የአመራር ሽግሽጎች እና አጠቃላይ ክልላዊና አገራዊ ሪፎርሙ ተጨባጭ ለውጥ አምጥቷል ማለት ይቻላል ?**

**አቶ ቸንኮት፡-** ለውጡ ሲመጣ አዲሱ አመራር ሥራውን የጀመረው የሐሳብ ለውጥ በማምጣትም ነው ። የተወሰዱት ትምህርቶችም የፓርቲ አንድነትን እና የአመራር አንድነትን ማጠናከር ትልቅ አስተዋፅኦ አበርክቷል። ይህ ሲታይ በሪፎርም የተከናወኑ ተግባራት ተጨባጭ ለውጥ አምጥተዋል የሚለውን ድምዳሜ ይሰጣናል።

**አዲስ ዘመን፡- ጋምቤላ ክልል የበለጠ ፀጥታውን ለማጠናከር ሌሎች ክልሎች እንደ ተሞክሮ ሊወስዱት ወይንም ሊሰጠው የሚችለው ነገር ምንድን ነው?**

**አቶ ቸንኮት፡-** ከእኛ ክልል በፀጥታው ረገድ ከሌሎች ክልሎች በተለይ ከድሬዳዋ በርካታ ነገሮችን ለመማር ችለናል። በተለይ የማህበረሰብ ፖሊሲ እንቅስቃሴዎችን እንደተሞክሮ በመውሰድ በእኛም ጋር ለመተግበር እየሰራን ነው። አደረጃጀታችን ተመሳሳይ ቢሆንም በእኛ ክልልም የማህበረሰብ አቀፍ ፖሊስ አሰራርን ጀምረን የምናስፋፋው ይሆናል። ይህም ከፀጥታው በተጨማሪ በከተሞች ያሉ ስርቆቶችን እና ሌሎች ወንጀሎችንም ለማስቀረት ስለሚጠቅመን በስፋት የምንሄድበት ይሆናል።

**አዲስ ዘመን፡- ስነበረን ቆይታ እያመሰገንኩ፤ ተጨማሪ ሐሳብ ካልዎት መጨመር ይችላሉ።**

**አቶ ቸንኮት፡-** እኔም አመሰግናለሁ። የክልላችን ሠላም ለማረጋገጥ ብሎም የኢትዮጵያ ሰላም እውን ለማድረግ ሁላችንም ትልቅ ኃላፊነት አለብን። ህብረተሰቡ ደግሞ የፀጥታ ኃይል ዋነኛ አጋዥ በመሆኑ ሊተባበር ይገባል። ይህን ማሳካት ከተቻለ እና መናበብ ካለ የሚፈለገው ሠላም ይሰፍናል።

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## ልዩ ስልት የሚፈልገው የድህረ ጦርነት ኢንቨስትመንት አስተዳደር

አንተነህ ቸሬ

በኢትዮጵያ ሰፍኖ የቆየው ሰላምና መረጋጋት፣ በመሰረት ልማት ዝርጋታ ዘርፍ የተከናወኑ ውጤታማ ተግባራት፣ የኢንቨስትመንት ዘርፍ ማበረታቻዎች እንዲሁም አገሪቱ ያላት የሰው ሀብት፣ እምቅ የተፈጥሮ ሃብት እና ሰፊ የገበያ እድል፤ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን በመሳብ በአፍሪካ ደረጃ ቀዳሚ ከሚባሉ አገራት መካከል አንዷ እንድትሆን አስችለዋታል፡፡ ይህም ለኢንቨስትመንት ዘርፍ ማደግ ዓይነተኛ ሚና የተጫወተ ሲሆን፣ ለአገሪቱ የምጣኔ ሀብት እድገትም ትልቅ ድርሻ አበርክቷል፡፡

የአገሪቱ የኢንቨስትመንት ዘርፍ በየጊዜው ከፍተኛ መሻሻልና እድገት ካስመዘገቡ ዘርፎች መካከል አንዱ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ባለፉት ጥቂት ዓመታት በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች የተፈጠሩት የፀጥታ ችግሮች በተለይ በሰሜን ኢትዮጵያ የተፈጠረው ጦርነት በዓለም አቀፍ ደረጃ ከተፈጠሩት የኮቪድ ወረርሽኝ፣ የምጣኔ ሀብት ቀውስና ጦርነቶች ጋር ተደምረው በአገሪቱ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድረዋል፡፡

በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ከነበረው ጦርነት ጋር ተያይዞ የተፈጠሩ ክስተቶች ለኢንቨስትመንቱ ዘርፍ መሰናከል መሆናቸው በተደጋጋሚ ተገልጿል።

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽንም ባለፈው በጀት ዓመት በኢንቨስትመንት ዘርፍ የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራትንና የተገኙ ውጤቶችን አስመልክቶ ይፋ ባደረገው መረጃ፤ በአገሪቱ ከነበረው አለመረጋጋትና ጦርነት ጋር ተያያዥነት ያላቸው የኢትዮጵያ ከ‹አጎዋ› (AGOA) መታገድ እና የዓለም አቀፍ ሚዲያዎች ጫና በበጀት ዓመቱ ካጋጠሙ የኢንቨስትመንት ዘርፍ ተግዳሮቶች መካከል እንደሚጠቀሱ አመልክቷል፡፡ ለአብነት ያህል በተጠቀሰው በጀት ዓመት የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን በመሳብ ረገድ ማሳካት የተቻለው የዕቅዱን 64 ነጥብ አራት በመቶ (ከሦስት ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ዶላር በላይ) ብቻ እንደሆነ የኮሚሽኑ መረጃ ያሳያል፡፡

ጦርነቱ በአገሪቱ ላይ ያሳደሩት ጫና ለበርካታ ዜጎች የሥራ እድሎችን በፈጠሩና የቴክኖሎጂ ሽግግርን ለማሳካት እገዛ እያደረጉ በሚገኙ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የነበሩ ትልልቅ አምራች ድርጅቶችን ከፍተኛ ጫና ውስጥ አስገብቷቸዋል፡፡ አለመረጋጋቱን ተከትሎ የመጣው የአንዳንድ ምእራባውያን አገሮች፣ የውጭ መገናኛ ብዙኃን እንዲሁም የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ዘመቻና ጫና አምራች ድርጅቶች ተረጋግተው እንዳይሰሩና አዳዲስ ኢንቨስትመንቶች በቀላሉ ወደ ኢትዮጵያ እንዳይመጡ ተፅዕኖ አሳድሮም ነበር፡፡ በተጨማሪም የውጭ አገራት ዜጎች ከኢትዮጵያ እንዲወጡ በአገሮቻቸው ኤምባሲዎች በኩል ከፍተኛ ግፊት ይደረግባቸው ስለነበር አምራቾች በጫና ውስጥ ሆነው ለመስራት ተገደው እንደነበርም ይታወሳል፡፡ በኢንቨስትመንት ተቋማት ላይ የደረሰው ጉዳት የምርት አገልግሎትና አቅርቦት መቋረጥ፣ የምርት ሽያጭ ገቢ መቀነስ፣ የስነ ልቦና ጫናዎችንና ሌሎች ችግሮችን አስከትሏል፤ ተጨማሪ ኢንቨስትመንት በቀላሉ ወደ ኢትዮጵያ እንዳይመጣ እንቅፋት ሆኖ መቆየቱም ይታወቃል፡፡

የኢንቨስትመንት ዘርፉ እንዲቀዛቀዝ ምክንያት ለነበረው የሰላም መደፍረስ መፍትሄ ይሆናል የተባለውና በኢ.ፌ.ዲ.ሪ መንግሥት እና በህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ሕወሓት) መካከል የተፈረመው የሰላም ስምምነት ለኢንቨስትመንት ዘርፉ መነቃቃትና ማንሰራራት ትልቅ ተስፋ ተጥሎበታል፡፡ የሰላም ስምምነቱ በተለያዩ ጫናዎች ሳቢያ ተቋርጠው የነበሩ የማምረት ስራዎች እንዲጀመሩ፣ ተቀዛቅዘው የነበሩ ምርቶችን ለውጭ ገበያ የማቅረብ ስራዎች እንዲያንሰራሩ እና አዳዲስ ኢንቨስትመንቶች ወደ አገሪቱ እንዲመጡ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ በእርግጥም ስምምነቱ እንደተጠበቀው ተጨባጭ ለውጦችን አስገኝቷል፡፡ ስራ አቋርጠው የነበሩ አምራቾች ወደ ስራቸው ተመልሰዋል፤ ወደ ኢትዮጵያ ገብተው በኢንቨስትመንት ተግባራት ላይ ለመሰማራት ፍላጎት ያሳዩ ባለሀብቶች ቁጥር እየጨመረ ነው፡፡

በጦርነቱ ምክንያት የተጎዳው የኢንቨስትመንት ዘርፍ እንዲነቃቃና ቀደም ሲል ከነበረው አፈፃፀምም የተሻለ ቁመና ላይ እንዲገኝ ነባራዊ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ ያስገባ የድህረ ጦርነት የኢንቨስትመንት አመራርና አስተዳደር ስርዓት መተግበር እንደሚያስፈልግ የምጣኔ ሀብት ጥናት ባለሙያዎች ያስረዳሉ፡፡

**በጦርነቱ ምክንያት የተጎዳው የኢንቨስትመንት ዘርፍ እንዲነቃቃና ቀደም ሲል ከነበረው አፈፃፀምም የተሻለ ቁመና ላይ እንዲገኝ ነባራዊ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ ያስገባ የድህረ ጦርነት የኢንቨስትመንት አመራርና አስተዳደር ስርዓት መተግበር እንደሚያስፈልግ የምጣኔ ሀብት ጥናት ባለሙያዎች ያስረዳሉ**

አንጋፋው የምጣኔ ሀብት ባለሙያና ዲፕሎማት አምባሳደር ጥሩነህ ዜና፣ ከጦርነት በኋላ የሚኖር የምጣኔ ሀብት ግንባታ በተለመደው አሰራርና የቢሮክራሲ ሂደት ተመርቶ ውጤታማ ይሆናል ብለው እንደማያምኑ ይገልፃሉ፡፡ እርሳቸው እንደሚሉት፣ ከጦርነት በኋላ በኢንቨስትመንትም ሆነ በሌሎቹ የምጣኔ ሀብት ዘርፎች የሚከናወኑ የመልሶ ግንባታ ስራዎች ፈጣን እርምጃዎችን የሚጠይቁ ናቸው፡፡ ራሱን የቻለና ውሳኔ ሊሰጡ የሚችሉ አካላት በቅርበት የሚከታተሉት እንዲሁም ሁሉም ባለድርሻ አካላት በጋራ ተሰባስበው የሚሰሩበት የአሰራር ዘዴ መተግበር ይኖርበታል፡፡ ይህ ዓይነቱ አሰራር ደግሞ በተለመደው የቢሮክራሲ አካሄድ ሊፈፀም አይችልም፡፡

‹‹ከጦርነት በኋላ መሰረተ ልማቶች የፈረሱበት፣ ቢሮክራሲው የላሸቀበት እና ሰብዓዊ ቀውስ የተንሰራፋበት ነባራዊ ሁኔታ ስለሚኖር፤ እነዚህን ጉዳቶች መልሶ መገንባትና ማካካስ የሚቻለው ከወትሮው በተለየ አካሄድና ስርዓት ነው፡፡ ፈጣን የሆኑ እርምጃዎች ያስፈልጋሉ፡፡›› ያሉት አምባሳደር ጥሩነህ፣ መደበኛው አሰራር ለድህረ ጦርነት ኢኮኖሚ ግንባታ ሊመጥን እንደማይችል አስታውቀዋል፡፡ ‹‹መደበኛውን አሰራር የምንከተል ከሆነ፣ ከችግሩ መውጣት አይቻልም፡፡ ስለዚህ በአዲስ ጉልበትና በአዲስ አሰራር መጓዝ ያስፈልጋል›› ሲሉ አስገንዝበው፣ ክህሎትና እውቀት ያላቸውን ባለሙያዎች በብዛት ማሰማራት እንደሚያስፈልግም ይናገራሉ፡፡

በሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የኢኮኖሚክስ መምህርና በ‹‹ፍሮንቲየርአይ (Frontieri)›› ጥናትና አማካሪ ድርጅት ከፍተኛ ተመራማሪ የሆኑት ዶክተር ሞላ ዓለማየሁ በበኩላቸው፣ በጦርነቱ ምክንያት የተዳከመውን የኢንቨስትመንት ዘርፍ ለማነቃቃት የሚያስችል ልዩ ስትራቴጂ በመንደፍ በልዩ ትኩረት መስራት እንደሚስፈልግ ይመክራሉ፡፡ እርሳቸው እንደሚሉት፤ በጦርነት የወደመ ኢኮኖሚን መልሶ ለመገንባት ከፍተኛ ኢንቨስትመንት ያስፈልጋል፡፡ ይህ ኢንቨስትመንት የመንግሥትን፣ የግሉን ዘርፍና የህዝቡን ትብብር የሚፈልግ ተግባር ነው፡፡

በዚህ ረገድ የጦርነቱን ጫና ሊያቃልሉ ለሚችሉ የኢንቨስትመንት ተግባራት ቅድሚያና ትልቅ ትኩረት መስጠት እንደሚያስፈልግ ጠቅሰው፣ ጦርነቱ የበለጠ ጉዳት የሚያስከትለው በመሰረተ ልማቶች ላይ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ የጦርነቱን ጫና ሊያቃልል የሚችለው ዐቢይ ተግባርም በጦርነቱ የተጎዱ መሰረተ ልማቶችን መልሶ መገንባት መሆኑን ነው ያመለከቱት፡፡ በጦርነት ጉዳት የደረሰባቸው ባለሀብቶች፣ ዘርፈ ብዙ ጫናዎችንና ጉዳቶችን ያስተናገዱ በመሆናቸው፣ ከጦርነት በኋላ ስራቸውን ለመቀጠል አስተማማኝ ዋስትና ይፈልጋሉ። ስለሆነም መንግሥት ለኢንቨስተሮች ዋስትና መስጠት ሌላው ተግባሩ ይሆናል ሲሉ ያመለክታሉ፡፡

አምባሳደር ጥሩነህ በጦርነቱ የደረሱ ጉዳቶችን መልሶ መገንባት የሚቻለው ከወትሮው በተለየ አካሄድና ስርአት ነው ሲሉ የገለጹትን ዶክተር ሞላም አጠናክረውታል፣ ዶክተር ሞላ ከጦርነት በኋላ የሚኖረውን አጠቃላይ የምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴ ከጦርነት በፊት በነበረው አሰራር መምራትና ማስተዳደር እንደማይቻል ጠቅሰው፣ የድህረ ጦርነት ኢንቨስትመንት አስተዳደር ስራ አስገዳጅ አሰራሮችን እንደሚፈልግ ጠቁመዋል፡፡ ‹‹በጦርነቱ የተጎዱት የምጣኔ ሀብት ዘርፎች እንዲያገግሙ ለማድረግ ዘርፎቹ ከጦርነቱ በፊት ሲያስመዘግቡ ከነበረው እድገት በተሻለ አቅም እንዲያድጉ ማድረግ ይጠበቃል፡፡ ስለዚህ ይህን ውጤታማ ሊያደርግ የሚችል አዲስ አሰራር ነድፎ መንቀሳቀስና ጉዳቱን ማካካስ ያስፈልጋል›› በማለት የድህረ ጦርነት ኢንቨስትመንት አስተዳደር ስራ የተለየ አካሄድ እንደሚያስፈልገው ያብራራሉ፡፡

በድህረ ጦርነት ኢኮኖሚ ግንባታ ሂደት ወሳኝ ሚና ካላቸው ግብዓቶች መካከል አንዱ የፋይናንስ አቅርቦት ነው፡፡ በጦርነቱ የተጎዳው የኢንቨስትመንት ዘርፍ እንዲነቃቃ የሚተገበረው የአመራርና አስተዳደር ስልት ከፋይናንስ አቅርቦት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አለው፡፡ ብቁ የሆነ የድህረ ጦርነት ኢንቨስትመንት አመራር ስልት አስተማማኝ የፋይናንስ አቅርቦት እንዲኖር ያስችላል። የኢትዮጵያ መልሶ ማቋቋምና ግንባታ ፕሮግራም ሰሞኑን ይፋ ሲደረግ፣ በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍልና በሌሎች ክልሎች የነበረው ግጭት ያስከተለውን ውድመት መልሶ ለመገንባት 20 ቢሊዮን ዶላር እንደሚያስፈልግ ተገልጿል።

የድህረ ጦርነት ኢንቨስትመንት ፋይናንስ የዓለም አቀፍ ተቋማትን ንቁ ተሳትፎ እንደሚፈልግ የሚናገሩት አምባሳደር ጥሩነህ፣ በመልሶ ግንባታው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ተቋማት፣ የዓለም ባንክ፣ የዓለም የገንዘብ ድርጅት (IMF)ን ጨምሮ ለጋሽ መንግሥታትን ማሳተፍ በእጅጉ አስፈላጊ እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡

ዶክተር ሞላ፣ ‹‹ጦርነቱ ‹ምን ዓይነት ጉዳቶችን አደረሰ? በጣም የተጎዱት ዘርፎች የትኞቹ ናቸው? ምን ዓይነት ኢንቨስትመንቶች ያስፈልጋሉ? የሚሉት ጉዳዮች በጥንቃቄ ከተለዩና ከተጠኑ በኋላ የፋይናንስ ምንጩ ከየት እንደሚገኝ ማሰብ ያስፈልጋል›› ይላሉ፡፡ ‹‹የፋይናንስ ምንጭ መፈለግ ወሳኝ ጉዳይ ነው›› የሚሉት ዶክተር ሞላ፣ ከመንግሥት በተጨማሪ፣ ባለሀብቶች፣ የልማት አጋሮች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ድጋፍ ማድረግ እንደሚኖርባቸው ይገልፃሉ፡፡ እርሳቸው እንደሚሉት፤ ተቋርጠው የነበሩ ግንኙነቶችን በማስቀጠል፣ እቅዶችን በመከለስ እና ሀብትን በአግባቡ በመጠቀም የፋይናንስ አቅርቦትን ማሳደግ ያስፈልጋል፡፡

ባለፉት አራት ዓመታት መንግሥት ዘርፈ ብዙ የምጣኔ ሀብት ማሻሻያ መርሃ ግብሮችን ተግባራዊ አድርጓል፡፡ ከእነዚህ መርሃ ግብሮች አንዱ፣ አገር በቀል የምጣኔ ሀብት ማሻሻያ መርሃ ግብር (Homegrown Economic Reform Program) ነው፡፡ የመርሃ ግብሩ ዓላማ አምራች የሆነውን የሠው ኃይል የሚሸከም የሥራ እድል እና የተረጋጋ የማክሮ-ኢኮኖሚ ከባቢ በመፍጠር እንዲሁም የግል ዘርፍ መር (Private Sector-Led) የሆነ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በመገንባት ዘላቂና ፈጣን የምጣኔ ሀብት እድገት ማስመዝገብ ነው፡፡ የኢንቨስትመንት አዋጅና የንግድ ሕግ ማሻሻያዎች፣ ብሔራዊ የንግድና ቢዝነስ ስራ አመቺነት ማሻሻያ መርሃ ግብር (National Ease of Doing Business Initiative) እንዲሁም ከዓለም አቀፍ የግብይት ስርዓት ጋር ዘመናዊ ትስስር ለመፍጠር የፋይናንስ ዘርፉ ለውጭ ባለሀብቶች ክፍት እንዲሆን ተወስኖ ውሳኔውን ለመተግበር እየተደረጉ ያሉ ዝግጅቶች የምጣኔ ሀብት ማሻሻያ መርሃ ግብሩ አካል ናቸው፡፡

አዲሱ የኢንቨስትመንት አዋጅ (1180/2012) ኢትዮጵያን ተወዳዳሪና ተመራጭ የኢንቨስትመንት መዳረሻ እንደሚያደርጋት ታምኖበታል፡፡ አዋጁ ለግሉ ዘርፍ በተለይም ለውጭ ባለሀብቶች ሰፊ የኢንቨስትመንት እድል የሚፈጥርና ገደብ የማያስቀምጥ አዋጅ በመሆኑ ኢትዮጵያ ውስጥ በኢንቨስትመንት ስራ ላይ የመሰማራት ፍላጎት ያላቸው ባለሀብቶች ሰፊ እድል ያገኛሉ፡፡ ቀደም ሲል አገሪቱ ትጠቀምበት የነበረው የኢንቨስትመንት ፖሊሲ የግሉ ዘርፍ ኢንቨስተሮች ኢትዮጵያ ውስጥ መጥተው ሊሰማሩባቸው የሚችሉ የኢንቨስትመንት ዘርፎችን የሚገድብ (Positive Listing Approach) ነበር፡፡ ይህ አሰራር ኢንቨስተሮቹ ሊሰማሩባቸው ከሚችሉባቸው ዘርፎች ውጭ ባሉት ሌሎች ዘርፎች ላይ እንዳይሳተፉ ገደብ የሚጥል ነው፡፡ ይህ የቀደመው አሰራር በተሻሻለው አዋጅ (1180/2012) ተቀይሯል፡፡ አዲሱ የኢንቨስትመንት አሰራር ባለሀብቶች ሊሰማሩባቸው የማይችሉባቸውን ዘርፎች የመዘርዘርና የቀሩትን ክፍት የማድረግ አቅጣጫ (Negative Listing Approach) በመሆኑ ለውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡

የኢንቨስትመንት ሕግጋት መሻሻልን ጨምሮ ሌሎቹ የምጣኔ ሀብት ማሻሻያ እርምጃዎች በድህረ ጦርነቱ ወቅት የሚኖረውን አገራዊ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ በማሳደግ ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅዖ እንደሚኖራቸው ዶክተር ሞላ ያስረዳሉ፡፡ እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ የኢንቨስትመንት አዋጁ መሻሻል የኢንቨስትመንትና የፋይናንስ አማራጮችን በማስፋት፣ የአገልግሎት አሰጣጥን በማዘመንና ብዙ ባለሀብቶችን በመሳብ ለኢንቨስትመንት ዘርፍ ማደግ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፡፡ የፋይናንስ ዘርፉ ለውጭ ባለሀብቶች ክፍት እንዲሆን የተላለፈውን ውሳኔ ተከትሎ ትልቅ አቅም ያላቸው ባንኮች ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ ከሆነ ለፋይናንስ አቅርቦት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋሉ፡፡

የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን ዘላቂ የአገሪቱ የምጣኔ ሀብት አንቀሳቃሽ ማድረግ ስለሚያስፈልግ ልዩ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ ባለሀብቶቹ የወጪ ንግድንና የተኪ ምርቶችን ምርት በሚያሳድጉ የኢንቨስትመንት ዘርፎች ላይ እንዲሰማሩ ማድረግ ያስፈልጋል፤ ምርቶችንና አገልግሎቶችን በማቅረብ ከሚኖራቸው ሚና ባሻገር ለዜጎች የሥራ እድል በመፍጠር፣ ገቢ ምርቶችን በመተካት እና የወጪ ንግድን በመጨመር ትልቅ አስተዋፅኦ ስለሚኖራቸው ይህን ሚናቸውን የበለጠ እንዲያሳድጉ በመንግሥት ድጋፍ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡

ከጦርነት በኋላ የሚኖር የኢኮኖሚ ግንባታ፣ በተለይም የኢንቨስትመንት ዘርፍ አስተዳደርና አመራር፣ የተለየ አሰራር እንደሚፈልግ ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን በአስረጂነት ማቅረብ ይቻላል፡፡ ‹‹የማርሻል እቅድ›› (Marshall Plan) በመባል የሚታወቀውና ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ የምዕራብ አውሮፓን ምጣኔ ሀብት ለማነቃቃት የተተገበረው የምጣኔ ሀብት ማገገሚያ መርሃ ግብር (Economic Recovery Act of 1948) ለዚህ ግንባር ቀደም ማሳያ ነው፡፡ በኢትዮጵያም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ መንግሥት እና በህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ሕወሓት) መካከል ከተፈረመው የሰላም ስምምነት በኋላ ለኢንቨስትመንት ዘርፉ መነቃቃትና ማንሰራራት ዋስትና ሊሆኑ የሚችሉ የድህረ ጦርነት የኢንቨስትመንት ማነቃቂያ ስትራቴጂዎችን በማዘጋጀትና በብቃት በመተግበር የሀገራዊ ምጣኔ ሀብቱን ግንባታ ማፋጠን ይገባል፡፡

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ጎሜ

## ጠኔ አርካሽ ቀዳሽ

**ሙሉቀን ታደገ**

ለበርካታ ወራት ተሰውሮ የነበረው ወፈፌው ይልቃል አዲሴ ዛሬ በሰፈራችን ተከስቷል፡፡ ሰማይ የአህያ ሆድ ሲመስል ተነስቶ በሰፈራችን ከሚገኘው ዋርካ ስር ቆሞ ይጮሃል፡፡ ጊዜው የሰፈራችን ሰዎች ወደ «በተስኪያን» የሚሄዱበት ሰዓት ነበር፡፡ በእኛ ሰፈር ያሉ ሰዎች በሙሉ በተስኪያን ሳይሄዱ በፊት ምንም አይነት ሥራ አይጀምሩም፡፡ ወፈፌው ይልቃል አዲሴ ከብዙ ቀናት መሰወር በኋላ ዛሬ ስለተከሰተ ዋርካው ስር መጮህ ሲጀምር በሰፈራችን የሚገኙ ሰዎች ሁሉ በተስኪያን መሄዳቸውን ትተው የይልቃ አዲሴን ንግግር ለማዳመጥ እየተቻኮሉ ወደ ዋርካው ስር ተሰባሰቡ፡፡

የሰፈራችን እና የእድራችን መሪዎች እንዲሁም ተፎካካሪዎቻቸው ወፈፌው ይልቃል አዲሴ በሚመራው ስበስባ ላይ መገኘታቸው የዛሬውን ስብሰባ ልዩ ያደርገዋል፡፡ ይልቃል አዲሴ ሁልጊዜም እንደሚያደርገው ዛሬም ሁሉም የሰፈራችን ሰዎች ወደ ዋርካው ስር እስኪሰበሰቡ ድረስ "ጥሩ የሰሩ ሰዎች ቢሞቱም ቢኖሩም አይጨነቁም ! አለ ሶቅራጥስ" እያለ የተለመደ ዲስኩሩን በጩኸት ይናገር ነበር ፡፡

የሰፈራችን ሰዎች ወደ ዋርካው ተሰባስበው ቦታ ቦታቸውን መያዛቸውን ከተመለከተ በኋላ ይልቃል አዲሴ፣ ራሱን ለንግግር እያዘጋጀ እህ.. እህ... ብሎ ጉሮሮውን ጠራረገ። ንግግሩንም እንዲህ ሲል ጀመረ፤ ‹‹በዛሬው ስብሰባ የሰፈራችን እና እድራችን መሪዎች እንዲሁም ተፎካካሪዎቻቸው መገኘታቸውን ተከትሎ በሰፈራችን የሚገኝ አንድም ጥሩንባ ነፊ አልቀረም ቢባል ማጋነን አይደለም፡፡ የሚገርመው የጡርንባ ነፊዎች መገኘት ብቻ አይደለም፡፡ ከዚህ ቀደም ይልቃል አዲሴ በመራቸው ስብሰባዎች አንድም ቀን ተገኝተው የማያውቁት አታሞ ደላቂዎች መገኘታቸው ነው ፡፡

እኔን የሚገርመኝ የጡርንባ ነፊዎች ነገር ነው፡፡ ጥሩንባ ንፉ ከተባሉ ዝም ብለው ይነፋሉ። የሰፈራችን እና የእድራችን መሪዎች እንዲሁም ተፎካከሪዎቻቸው አንድ ነገር ትንፍሽ ካሉ፤ የቱንም ያህል ንግግራቸው ስህተት ቢኖረው እንኳን ንግግራቸውን ምንም ሳያርሙ የቆሻሻ ማስወገጃ ቱቦ ይመስል እንዲሁ እንደወረደ ያነበንቡታል። የቆሻሻ ማስወገጃ ቱቦ እንኳን የተወሰነ ደለል እና ቆሻሻ ያስቀራል፡፡ የእኛ ሰፈር ጡርባ ነፊዎች ግን እንኳንስ ከተነገራቸው ሊቀንሱ ይቅርና የእድራችን ሰብሳቢ ያሉትን ለማሽሞንሞን በማሰብ የእድራችን ሰብሳቢው ያላሉትን ብቻ ሳይሆን ያላሰቧቸውን ቃላት በመፍብረክ የሰፈራችንን አየር በጩኸት ይሞሉታል ፡፡

አንድ ቀን አንዱ ጡርባ ነፊ የእድራችን ሰብሳቢ ወግ ለማሽሞንሞን አስቦ የእድራችን ሰብሳቢ ከተናገሩት የሚጣረስ ቃላቶችን ተናገረ፡፡ ምንም ስህተት የማያልፉት የእድራችን ሰብሳቢም ጡሩምባ ነፊውን ወዲያውኑ ከስራው ከማባረር አልፈው ወደአልታወቀ ስፍራ ወስደው እንዳስቀጠቀጡት ሰማን፡፡ ስለእውነት ይህንን የእድራችን ሰብሳቢ ውሳኔ እጅጉን ወድጀዋለሁ፡፡

ከላይ እንደነገርኳችሁ የዛሬው ስበሰባ ከጡሩምባ ነፊዎች ባሻገር በአታሞ ደላቂዎች የታጀበ ነው። አታሞ የሚመታው የብሄር ብሄረሰቦችን ሙዚቃ መሰረት ተደርጎ መሆኑን ስመለከት አግራሞቴን የባሰ ከፍ አደረገው ፡፡ በሰኔ ስለእርሻ ማውራት ሲገባን እንዴት የብሔር ብሔረሰቦች ሙብት እያልን ለማላዘን እንኳትናለን ? ጎበዝ !

"የሆነው ሆኖ ዛሬ ወደ ተሰበሰብንበት የስበሰባ አጀንዳ ልመልሳችሁና" አለና ወፈፌው ይልቃል አዲሴ ንግግሩን ቀጠለ... ‹‹ አሁን ወቅቱ ሰኔ ነው ። በሰኔ በሬ እና ገበሬ ዝምድናቸው የሚጨምርበት፤ አብረው ውለው አብረው የሚያድሩበት ነው። ገበሬዎችም በእንጉርጉሮ እና በተለያዩ ጣዕመ ዜማዎች ለበሬዎቻቸው ብሶታቸውን የሚነግሩበት ፤ ችግራቸውን የሚያወያዩበት ፤ ሚስጥራቸውን የሚያካፍሉበት ነው፡፡ በአጠቃላይ በሰኔ የበሬ እና የገበሬ ፍቅር የተለየ ነው፡፡ ሳንባችንን አጋጥመን በአንድ አፍንጫ እንተንፍስ የሚሉበት ወቅት ነው።

**ምነው አርሶ አደሩም፣ አውርቶ አደሩም ፣ አርብቶ አደሩም ፣ በልቶ አደሩም ፣ዋሽቶ አደሩም ፣ ወጥቶ አደሩም ፖለቲከኛ እንሁን አለ?**

በተለይ እንደኛ ሰፈር ተጨባጭ ሁኔታ እና የእኛ ሰፈር ኢኮኖሚ በእርሻ ላይ እንደመመስረቱ ወርሐ ሰኔ ለእኛ ሰፈር ገበሬዎች እና ነዋሪዎች የተለየ ትርጉም አለው፡፡ የእድር እና የሰፈራችን መሪዎችም የሚቀጥለው ዓመት ገበያ የተትረፈረፈ እንዲሆን በማሰብ ከወዲሁ የምርጥ ዘሩን እና የማዳበሪያውን ግበዓት ለአርሶ አደሩ ለማሟላት ከላይ ታች የሚሉበት ነው፡፡

ተፎካካሪዎች እና አንዳንድ ማህበራትም የምርጥ ዘሩን እና የማዳበሪያውን አቅርቦት እየተመለከቱ የየራሳቸውን አስተያየት በማዥጎደጉድ ለአርሶ አደሩ ምርጥ ዘር እና ማዳበሪያ እንዲቀርብ ለማድረግ በእድር እና በሰፈራችን መሪዎች ላይ ግፊት የሚያደርጉበት ወቅት ነው፡፡

ከዚህ ቀደም በነበሩት ሰኔዎች ከሊቅ እስከ ደቂቅ የሚገኙ እድራችን እና ሰፈራችን ነዋሪዎች እንዲሁም መሪዎች እና ተፎካካሪዎቻቸው ለእድራችን እና ለሰፈራችን የቀጣይ ዓመት የምግብ ፍጆታ ምርቶችን ለማምረት የሚኳትኑበት ጊዜ ነበር፡፡ በዘንድሮው ሰኔ ግን አልፎ አልፎ በፖለቲከኞች የሚፈጸሙ ያለተገቡ ነገሮች እየተስተዋሉ ነው፡፡ እውነት እኛን ለመሰለ የዓመት ዝናብን ጠብቆ ለሚዘራ እና ራሱን የሚመግብ ህዝብ በሚገኝበት ሰፈር እና እድር በሰኔ ምን የሚሉት ፖለቲካ ነው ? ሰኔ ላይ በእኛ ሰፈር የሚፈለገው አውርቶ የሚኖር ሳይሆን በተግባር ምርጥ ዘር እና ማዳበሪያ ለገበሬው የሚያቀርብ ሰው ነው፡፡

"ዋዘኛ ገበሬ ይሞታል በሰኔ መባል ያለባቸው እንደእነዚህ አይነት ፖለቲከኛ ነን ባዮችን ነው። ሰው ምርጥ ዘር እና ማደበሪያ በሚፈልግበት ወቅት በፖለቲካ መጎሻሸም ምን የሚሉት ነው?" ብሎ ይልቃል አዲሴ እየተናገረ እያለ፤ ሁሌም ሳይፈቀድለት የሚናገረው አብሿሙ ከንፈ ጉደታ እንደተለመደው ዛሬም የይልቃልን ንግግር አቋረጠው።

አብሿሙ ከንፈ ጉደታ፣ የይልቃልን ንግግር ሙሉ በሙሉ እንደሚደግፈው ገልጾ፤ ንግግሩን እንዲህ ቀጠለ... "ዘላዕስ ነፍሱ ይኤብስ ለመኑ ኄረ ይከውን (ለራሱ የሚነፍግ ለማን ቸር ይኖናል ?) እንዲሉ በእኛ ሰፈር ሚገኙ አንዳንድ ፖለቲከኞች እንደዚህ አይነት ሰዎች ናቸው ፡፡

መላው የሰፈራችን እና የእድራችን ነዋሪዎችን እንዲሁም መሪዎችን እና ተፎካከሪዎችን እየመገበ ያለን አርሶ አደር በወርሃ በሰኔ ተልካሻ የፖለቲካ ምክንያት እየፈጠሩ ምርት እንዳይመረት ጋሬጣ መሆን ምን የሚሉት ፖለቲከኝነት ነው ?

የሚገርው ደግሞ ውሸታችሁ ነው ፡፡ አንዳችሁ ከአንዳችሁ አትሻሉም ፡፡ ሁላችሁም አንድ ናችሁ።" ይኄይስ ህዳጥ በዘጽድቅ እምብዙኅ ብዕለ ኃጥአን (ውሸት ከመናገር ዲዳነት ይሻላል፡፡) እንዲሉ ምን አለበት ፈጣሪ ክፉ አሳቢ ፖለቲከኞችን ወርሃ ሰኔ እስኪያልቅ ልሳናችሁ በዘጋው ብዬ ተመኘሁ ፡፡

ምክንያቱም "ጻማ ከናፍር (ጉንጭ አልፋ)" እንዲሉ ሁሌም ትከራከራላችሁ፤ ሁሌም ትነታረካላችሁ፤ ፖለቲካን አብሳላችሁ ታነኩራላችሁ ነገር ግን ክርክራችሁ አንድም ቀን መፍትሄ አምጥቶ አያውቅም፡፡ እንዲሁ ክርክር!፡፡ የእናንተ ንትርክ መሬት ቆፍሮ አገር የሚቀልበውን ገበሬ ጭምር ያናጠበ መሆኑን ስመለከት አርሶ አደሩ ማሳውን አለስልሶ ዘሩን እንዳይዘራ መድሃኒት አልባ ደንቀራ ሁናችሁ ትታዩኛላችሁ፡፡

ሁሌም ምታደርጉት ክርክር የራሳችሁን ጥቅም ለማሳደድ እንጂ የሰፈራችሁን አርሶ አደሮች ጥቅም ለማስጠበቅ እና ለማሻሻል እደንዳልሆነ ስመለከት በፅኑ ያበግነኛል፡፡

በነገራችን ላይ አሁን አሁን በሰፈራችን እየተስተዋለ ያለው ፖለቲካን እየጋገሩ የማንኮር ተግባር በአርሶ አደሮቻችንም ተጋብቶ ተመለከትኩ። በእርሻ ላይ እያለ ገበሬ ድሮ ድሮ በሬዎቹን ሲያበረታታ

**"እያ በሬ በሬ፤**
**ልቀበር ባገሬ፤**
**በገዛ ድንበሬ ፡፡"** ይል ነበር፡፡ አሁን ላይ ግን ሁሉን እርግፍ አድርጎ ትቶ ለበሬው የሚዘፍነው እና የሚያንጎራጉረው የፖለቲካ ግጥሞችን የያዙ ስንኞችን ነው፡፡ ለምሳሌ ባለፈው ታች መንደር የሚገኝ አንድ አርሶ አደር ...

**"በርዬ በርዬ በአንተ ጉልብት አርሰን ካልሆነ ነገሩ፤**
**ከዙፋን ተጠግተን እንዝረፍ ከብሩ፡፡**
**ማዳበሪያም ያለ ከዙፋኑ ስር፤**
**ድሎቱም ያለው ከዙፋኑ ስር፤**
**ምነው እኔ እና አንተ በብርድ እንረር?"** ሲል ሰማሁት ፡፡ እርሻውን ትቶ የፖለቲካ ወንበር መፈለጉን ከግጥሙ ተገነዘብኩ ፡፡ ስለእዕውነት ይህንን አባባል መሬት ቆፍሮ ሀገር ከሚቀልበው አርሶ አደር መስማት ያማል፡፡ ወዴት እየሄድን ነው? ስል ራሴን ጠየኩ። ምክንያቱም የተማረውም ያልታማረውም ፤ ፖለቲከኛውም ሌላ ስራ የሚሰራውም በፖለቲካው ግብቶ መፈትፈት ከጀመረ በሰፈራችን አንድ የከሸፈ ነገር እንዳለ ይሰማኛል ፡፡ ምነው አርሶ አደሩም፣ አውርቶ አደሩም ፣ አርብቶ አደሩም ፣ በልቶ አደሩም፣ ዋሽቶ አደሩም ፣ ወጥቶ አደሩም ፖለቲከኛ እንሁን አለ?

እየሄድንበት ያለንበት መንገድ ትክክል አይደለም። ሁሉም የሚመለከተውን እና የሚችለውን ቢሰራ አትራፊ እንሆናለን፡፡ ነገር ግን ፖለቲካን ተገን አድርጎ አንዱ እየሰራ ሌላው ለመስረቅ መሞከር ተገቢ አይደለም ፡፡ አሁን ላይ በሰፈራችን ባለው ተጨባጭ ፖለቲካን ለስርቆት እና ለወንጀል መደበቂያ ምሽግ የማድረግ አዝማሚያ በአንዳንድ ሰዎች ይስተዋላል። ይህ ትክክል አይደለም ፡፡

"ሌላ በሰራው ስራ ለመክበር የሚሞክርን ሰው ስመለከት በ1952 በአዲስ ዘመን ጋዜጣ የታተመውን "ምን ይባላል ?" የተሰኘውን የማሞ ውድነህ አንድ ግጥም ያስታውሰኛል፡፡ ማሞ ወድነህ በግጥሙም

**መዶሻ ሲሰራ ሲቆፍር በአካፋ ፡፡**
**ሲጥር ሲግደረድር ስማስፍ ፈተና፤**
**ምኑንም ያንንም ሲጀምረው ገና ፡፡**
**ነጋ አልጋ ብሎ ስሥራ ሲነሣ ፤**
**በስራ ሲደክም ሲቀበል አበሳ ፡፡**
**አንደኛው ዝም ብሎ ቆሞ መመልከቱ**
**ኩራት ነው ስንፍና ምንድን ነው ብልሃቱ።**
**ወሬ ማውራት ብቻ ለምዶ ድሮውን**
**ስራ መስራት ተወ እየት ይህንን፡፡** ሲል ተቀኝቶ ነበር" ብሎ አብሿሙ ከንፈ ጉደታ ወደ መቀመጫው ተመለሰ፡፡

አብሿሙ ከንፈ ጉደታ ወደ መቀመጫው መመለሱን የመለከተው የሰፈራችን እና የእድራችን ሰብሳቢ ጉሮሮውን ለንግግር እየጠራረገ ንግግሩን እንዲህ ሲል ጀመረ፤ በባለፉት ወራት የሃምሳ ሺህ ዩሮ መጽሀፍ ስለገዛች አንዲት አርሶ አደር በስፋት ሲዘገብ ሰምቻለሁ፡፡ ምነው ይች ሰው ተሞክሮዋን ለእኛ ሰፈር አርሶ አደሮች ብታካፍል? ስል ተመኘሁ፡፡

አሁን ላይ የሰፈራችንን ምርት ለመጨመር ከታሰበ የሃምሳ ሺህ ዩሮ መጽሐፍ የገዛቸውን አርሶ አደር ተሞክሮ በተለያዩ ክፍሎች በማደራጀት እና የሥልጠና ማንዋሎችን በማዘጋጀት በመላው ሰፈራችን ለሚገኙ አርሶ አደሮች እሁድ እና ቅዳሜ ሥልጠና ሊሰጥ ይገባል፡፡

አንድ አርሶ አደር በማሳ ያመረተው ምርት ከእርሱ አልፎ ሃምሳ ሺህ ዩሮ አውጥቶ መጽሐፍ መግዛት ካስቻለው፤ የዚህን አርሶ አደር ተሞክሮ ለሰፈራችን እና ለእድራችን አርሶ አደሮች በተሞክሮነት ማሠልጠን ያስፈልጋል ባይ ነኝ ፡፡ ምክንያቱም የእዚህችን አርሶ አደር ተሞክሮ የወሰደ የሰፈራችን ሠልጣኝ አርሶ አደር የሃምሳ ሺህ ዩሮ መጽሐፍ መግዛት ባይችል እንኳን፤ ሃምሳ ለሚሆኑ የሰፈራችን ሰዎች በአነስተኛ ዋጋ የምግብ ፍጆታ ማቅረብ የሚያስችለው ይመስለኛል፡፡ ከዚህም ባለፈ በሰፈራችን እና በእድራችን የተጀመረውን ስንዴን ወደ ውጭ የመላክ ጅማሮ አጠናክሮ የሚያስቀጥል ይሆናል።

"ስለሆነም በሃምሳ ሺህ ይሮው መጽሐፍ የገዛቸው ገበሬ የአመራረት ተሞክሮ በሰፈራችን ለሚገኙ መላው አርሶ አደሮች ስልጠና ሊሰጥ ይገባል፡፡" ብሎ ወደ መቀመጫው ተመለሰ፡፡

ይህን ተከትሎ ይልቃል አዲሰም ከሥልጠና ጋር ተያይዞ "እኔም የምናገረው ነገር አለ፡፡" ብሎ ንግግሩን ቀጠለ... ‹‹በዓለማችን የውሃ እጥረት ከሚያሰቃያቸው አገራት አንዷ የሆነችው እስራኤል ከ70 በመቶ በላይ የሚሆኑትን የዜጎቻን ቀለብ የምትሸፍነው ራሷ ባመረተችው ምርት መሆኑን ሳስብ አብዝቼ እደነቃለሁ፡፡ እናም! እስራኤል ዜጎቿን በዚህ ልክ ልትቀልብ የቻለችበትን ተሞክሮ ለእኛ ሰፈር ሰዎች ማስተማሩ ለነገ የሚባል ተግባር አይደለም ፡፡ ዝም ብሎ ኩታ ገጠም ፤ ስም ገጠም ፤ ምን ገጠም ቢሉት ዋጋ የለውም ፡፡

ይልቃል አዲሴ ንግግሩን ቀጥሎ..."በዓለማችን ተክኖሎጂን ተጠቅሞ ሰው ሰራሽ ዝናብ መጀመሩን በተመለከተ፤ በ1952 ዓ.ም ቻይና በደቡብ ቻይና የሚገኝን አስር ሺህ ካሬ ኪሎ ሜትር በላይ በሆነ ደረቅ ቦታ ላይ ማዝነቧን በወቅቱ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዘግቦት ነበር፡፡

በቅቡም ይህ አካሄድ በእኛ ሰፈር መጀመሩንም ሰምተናል፡፡ ያው ወደ ቴክኖሎጂው መግባታችን በጎ ቢሆንም ነገር ግን ብዙ ወጭ ሊያስጣ ይችላል። ስለሆነም አገራችን ለእንደዚህ አይነቱ ቴክኖሎጂ ወጭ ከምታወጣ ለምርጥ ዘር እና ማለዳበሪያ መግዣ ብታደርግ፤ እንዲሁም ያለሙያቸው ፖለቲካ ውስጥ ገብተው የሚፈተፍቱ እና ዜጎች በተሰማሩበት ስራ ምቾት ተሰምቷቸው እንዳይሰሩ የሚያደርጉ አካላትን አደብ ለማስገዛት በሚደረግ ስራ ላይ ወጪ ቢደረግ መልካም ነው ፡፡" ብሎ ንግግሩን ሲጨርስ የሰፈራችን ሰዎችም ለይልቃል ያላቸውን አድናቆት በጭብጨባ ገልጸው ስብሰባው ተበተነ።

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

## የጉማ ሽልማት ለፊልም መነቃቃት

**ዋለልኝ አየለ**

በየዓመቱ የሚካሄደው ጉማ የፊልም ሽልማት ከተጀመረ እነሆ ዘንድሮ ፃኛ ዙር ላይ ደርሷል፡፡ ባለፈው አርብ ሰኔ 2 ቀን 2015 ዓ.ም የፃኛው ዙር የጉማ ፊልም አሸናፊዎች ታውቀዋል፡፡

ጉማ የፊልም ሽልማት የፊልም መነቃቃት ይፈጥራል፤ ፈጥሯልም፡፡ ምንም እንኳን ሽልማቱ በተሰሩ ፊልሞች ላይ ቢሆንም፤ ወደፊት በሚሰሩ ፊልሞች ላይ ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል፤ መነቃቃትንም ይፈጥራል፡፡

የፊልም መነቃቃት ይፈጥራል ሲባል፤ ዕጩዎች ከቀረቡበት ጊዜ ጀምሮ ስለፊልም ይወራል፡፡ ስለተዋናዮች ብቃት ይወራል፤ ስለፊልሞች ይዘት ይወራል፡፡ የትኛው ፊልም ይሸለም ይሆን በሚል ፊልሞችን የመዳሰስ ሥራ ይሰራል፡፡ በተለይም በዕጩነት የቀረቡ ፊልሞች ስም ሲዘረዘር፤ ፊልሞችን ያላዩ ሰዎች አፈላልገው እንዲያዩት ያደርጋል፡፡

የተዋናዮች ማንነት ይታወቃል፡፡ በተለይም ወጣት ተዋናዮች ሥራዎቻቸውና ብቃታቸው እንዲታይላቸው ያደርጋል፡፡ ጉማ የፊልም ሽልማት እንቅስቃሴ ከሚጀመርበት ሰሞን ጀምሮ በመገናኛ ብዙኃንም ሆነ በመድረኮች ስለፊልም ይወራል፣ ስለዕጩ ተዋናዎችና ሥራዎቻቸው ይወራል፡፡ በዚህ ሁሉ ውስጥ የፊልም መነቃቃት እየተፈጠረ ነው ማለት ነው፡፡ በአዘቦት ስለፊልም የማይሰሩ መገናኛ ብዙኃን ሁሉ በዚህ ሰሞን ይሰራሉ ማለት ነው፡፡ እግረ መንገድም አንዳንድ ፊልሞች ላይ ዳሰሳዎች ይሰራሉ ማለት ነው፡፡

በሌላ በኩል ጉማ የፊልም ሽልማት የተለያዩ ዘርፎች ስላሉት፤ የተለያዩ የፊልም ሙያዊ መመዘኛዎችን ወደ ፊልሙ ዘርፍ የሚገቡ ሰዎች ይማሩበታል ማለት ነው። ፊልም ሲባል ብዙዎቻችን የምናውቀው ያለቀለትን ሥራ ነው፡፡ ዘርፎቹ ተዘርዝረው ስናየው ግን ከጀርባው ብዙ ቴክኒካል ነገሮች እንዳሉ እናያለን፡፡ ይዘቱን ብቻ ሳይሆን ከማጀቢያ ሙዚቃው ጀምሮ የሜካፕ ባለሙያዎችን ሁሉ ብቃታቸውን እናይበታለን ማለት ነው፡፡

እነዚህን የፊልም ጥበቦች ብዙዎቻችን ልብ ስለማንላቸው በጉማ የፊልም ሽልማት ምክንያት ትኩረት ይሰጣቸዋል ማለት ነው፡፡ እኛም ስለፊልም ያወራነው በዚሁ ሽልማት ምክንያት ነው፡፡

ፊልም በተለያዩ ዘርፎች ቢከፈልም፤ የሰውን ልጅ የአሁኑን የትናንቱንና የነገውን ሁኔታውን የሚያስተላልፍበት መገናኛ መንገድ ነው፡፡ የፊልም ሥራዎቻቸው ባደጉት በትላልቆቹ ዓለም ደግሞ ያሉበትን ሉዓላዊነት ማንፀባረቂያ፣ ያላደጉትን አገራት ማስፈራርያ እና መማረኪያ ንብረታቸው ነው፡፡ ራሱን የቻለ የኢንዱስትሪ ዘርፍ ነው፡፡

ወደ ኢትዮጵያ ስንመጣ ግን፤ ኢትዮጵያና ፊልም ያላቸው ትውውቅ ከአንድ ክፍለ ዘመን የተሻገረ ቢሆንም የዘመናዊ ፊልም ታሪኳ ግን ከሃያ ዓመታት ያልተሻገረ ነው፡፡

ፊልም እንደ ኢንዱስትሪ መታየት ጀምሮ በብዙ ጎኖች አልፎለት በሲኒማ ቤቶች ደረጃ መታየት የጀመረው ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ነው፡፡ እንደ ጉዲፈቻ፣ የበረዶ ዘመን፣ ስላንቺ፣ የወንዶች ጉዳይና የመሳሰሉት ፊልሞች የኢትዮጵያ ዘመናዊ የፊልም ታሪኳ ውስጥ በምሳሌነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

እነዚህን ፊልሞቻችንን ይዘን ጉማ የፊልም ሽልማት ተጀመረ፡፡ ከሃምሳ ምናምን ዓመታት በፊት በሚሼል ፓፓታኪስ የተሠራው እና በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ባለቀለም ፊልም በሆነው ‹‹ጉማ›› ፊልም መጠሪያውን ያደረገው ጉማ የተሰኘው ሽልማት ስለፊልሞች በሰፊው እንዲወራ አስደረገ፡፡

ሽልማቶች ለፊልም ኢንዱስትሪው እያበረከቱት ያለውን አስተዋፅዖ ማንም ወደ ፊልሙ ተጠግቶ የማያውቅ እንግዳ ሰውም ሊያውቀው የሚችለው ጉዳይ ነው፤ ሽልማትና ምሥጋና መነቃቃትን ይፈጥራል፡፡ የተለያዩ ጉዳዮችን የሚዳስሱ ፊልሞችን እየያዘ የሚመጣው ጉማ የፊልም ሽልማትም በየዓመቱ




ደመቅ ባለ መልኩ ነው የሚከናወነው፡፡

በነገራችን ላይ ጉማ የፊልም ሽልማት በ2012 ዓ.ም የተከሰተውን የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት በማድረግ አልተካሄደም ነበር፡፡ በ2013 ዓ.ም ነው እንደገና በደማቁ የተጀመረው፡፡

በኢትዮ ፊልም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ድርጅት የሚዘጋጀው ጉማ ፊልም ሽልማት ጥሩ ብቃት ላሳዩ ፊልሞች እና አርቲስቶችን ክብርና እውቅና መስጠት ዓላማው እንዳደረገ አዘጋጆች በተለያየ ጊዜ ተናግረዋል።

ተደጋጋሚ ወቀሳ የሚሰነዘርበት የኢትዮጵያ የፊልም ኢንዱስትሪ እንዲህ አይነት የማነቃቂያ ሽልማቶች ያስፈልጉታል፡፡ የፊልም ኢንዱስትሪውም ወቀሳው ብዙ ስለተደጋገመበት እንጂ በዓለም አቀፍ ደረጃ የታዩ ተወዳጅ ፊልሞችም ተፈጥረዋል፡፡

በተለይም ባለፉት 20 ዓመታት የጎሉ እንቅስቃሴዎች ታይተውበታል። ለምሳሌ፤ በጀርመን ታዋቂ በሆነው ዓለምአቀፍ የፊልም ውድድር በርሊና መድረክ እና በዩናይትድ ስቴትሱ የሰንዳንስ ፊልም ፌስቲቫል ላይ ሽልማትን ያገኘው የኢትዮጵያው «ድፍረት» የተባለው ፊልም ተጠቃሽ ነው።

በፊልም ስራ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርቱን በአሜሪካ ያጠናቀቀውና በርካታ ፊልሞችን እንደሰራ የሚነገርለት የጉማ ፊልም ሽልማት ዋና አዘጋጅ አቶ ዮናስ ብርሃነ መዋ፤ የጉማ ፊልም ሽልማት የተጀመረ ዓመት ለዶቼቬሌ እንደተናገረው፤ ዝግጅቱ የፊልም ጥበብንና ጥበበኞችን ለመደገፍ የታሰበ የሽልማት ሥነ ሥርዓት ነበር፡፡ እነሆ አሁን እዚህ ደረጃ ላይ ደርሶ ብዙ መነቃቃትን ፈጠረ፣ ፊልሞችም በጥራት መሰራት ጀመሩ፡፡

በጉማ የፊልም ሽልማት ሥነ ሥርዓት ላይ በተለያዩ ዘርፎች ከሚሰጠው ሽልማት በተጨማሪ ደግሞ፤ ለውድድር የማይቀርብ ዘርፍ አለ፤ ይህ ዘርፍ ‹‹የሕይወት ዘመን ተሸላሚ›› ነው፡፡ የሕይወት ዘመን ተሸላሚ የሚሆነውን ሰው መርጦ ማውጣት ነው።

የመጀመርያው የጉማ ፊልም ሽልማት ላይ የሕይወት ዘመን ተሸላሚ የነበሩት፤ ከአርባ ዓመት በላይ በፊልም ጥበብ ስራ ላይ የቆዩትና የመጀመርያው የኢትዮጵያ ፊልም ዳይሬክተር ሚሼል ፓፓታኪስ ናቸው።

ሚሼል ፓፓታኪስ፤ አባታቸው አዲስ አበባ ውስጥ የፊልም ቤት የከፈቱ የግሪክ ዜጋ ሲሆኑ እናታቸው ደግሞ ኢትዮጵያዊትና ትውልዳቸውም ኢትዮጵያ ውስጥ ነው።

የፊልም ሽልማት ሥነ ሥርዓቱን ጉማ ሲል መጠርያ የሰጠው የሥነ ሥርዓቱ ዋና አዘጋጅ እና የፊልም ስራ ባለሙያው ዮናስ ብርሃነ መዋ በወቅቱ ለዶቼቬለ እንደገለጸው፤ በሚሼል ፓፓታኪስ የተሰራው ጉማ ፊልም፤ ስያሜውን ከአፋን ኦሮሞ ቋንቋ እንደወሰደና፤ ካሳ ማለት እንደሆነ ተናግሯል፡፡

ፊልሙ በኦሮሞ ማህበረሰብ ውስጥ ስላለው የግጭት አፈታት ባህል ላይ የሚያውጠነጥን ዘጋቢ ፊልም ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት ፊልሙ በኢትዮጵያ ብሄራዊ ሙዚየም ወመዘክር ውስጥ ይገኛል፡፡

ጉማ የፊልም ሽልማት ሥነ ሥርዓት አሁን አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ በስፋት እየታየ ላለው የቪዲዮ ፊልሞች ምርት መሰረት የጣሉትን ሰዎች ያስታወሰ፤ በዳኝነትም ሆነ አንጋፋ የፊልም ተዋናዮችን ታሳቢ ያደረገ መድረክ ነው፡፡

የፊልም ኢንዱስትሪው እንዲያድግና፤ በኢኮኖሚው ውጤታማ እንዲሆን ሁሉም የተቻለውን ጥረት እንዲያደርግ ያነሳሳል፡፡ ሆኖም ግን ከሚመለከታቸው አካላትም ድጋፍ መደረግ አለበት፡፡ ምክንያቱም ፊልሞች የኢትዮጵያን ባህል በማስተዋወቁም ረገድ ሆነ ዓመታዊ ገቢን ከፍ እንዲል በማድረግ ከፍተኛ ሚና ይኖራቸዋል፡፡

በኢትዮጵያ የፊልም ስራ ዕድገት፣ ጥራትና ኢትዮዮጵያዊ ደረጃን የጠበቀ እንዲሆን የፊልም ሰራተኛ ማህበሩ ጥረት እያደረገ መሆኑንም የዘርፉ ሰዎች ሲናገሩ ቆይተዋል፡፡ ስለዚህ እንዲህ አይነት ሽልማቶች፤ መንግሥትንም፣ የፊልም ባለሙያውንም፣ የፊልም ተመልካቹንም መነቃቃት ይፈጥሩለታል ማለት ነው፡፡

የፊልም ተመልካቹ ላይ ግን አንድ ትዝብት እናጋራ። ሁልጊዜ የፊልም ኢንዱስትሪውን መውቀስ ብቻውን ለውጥ አያመጣም፡፡ የኪነ ጥበብ ዘርፍ እና ስፖርት አንፃራዊ ነፃነት ስላለው ይመስላል ሰዳቢው ብዙ ነው፡፡ ከማድነቅ ይልቅ መተቸቱ የሚቀል ይመስላል፡፡ እርግጥ ነው ወቀሳ ስለበዛበት ነው ያላደገ ማለት አይቻልም፤ ቢሆንም ግን ጥሩ የተሰሩ ፊልሞችን ማድነቅና እውቅና መስጠት ደግሞ የበለጠ ያበረታታል። ስለዚህ እንደ ጉማ አይነት የፊልም ሽልማቶች ሲደረጉ ከፊልም ባለሙያው በተጨማሪ ተመልካቹም ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

ለምሳሌ፤ በባለፉት ዓመታት ሁሉ የተደረጉ የጉማ ፊልም ሽልማት አስተያየቶችን እናስታውስ፡፡ በመድረኩ በተለያየ ዘርፍ ከተሸለሙ ፊልሞች ይልቅ አጀንዳ ሆኖ የነበረው የሴት አርቲስቶች አለባበስ ነበር። የተሸለሙትን ፊልሞች የይዘትም ሆነ የቴክኒክ ጥራት ከመገምገም ይልቅ የአርቲስቶች አለባበስ የሳምንት አጀንዳ ሆኖ ይቆያል፡፡ እንዲያውም አሸናፊ የሆኑ ፊልሞች እስከሚረሱ ድረስ ዋናው መከራከሪያ አለባበስ ሆኖ ይታያል፡፡ የዕለቱ የመድረክ አለባበስ ለዚያ ቅጽበት እንጂ በተሸለሙበት ፊልም ላይ የሚጨምረውም ሆነ የሚቀንሰው ነገር የለውም፡፡

በአጠቃላይ የአገራችን የፊልም ኢንዱስትሪ የሚያድገው በኪነ ጥበብ ባሙያውም፣ በታዳሚውም በመንግሥትም የጋራ ፍላጎት ነውና ከሁላችንም የሚጠበቀውን እናድርግ! በመጨረሻም በዘንድሮው ፃኛው የጉማ ፊልም ሽልማት የተሸለሙ የፊልም ዘርፎችንና ባለሙያዎችን እናስታውስ፡፡

**ምርጥ አጭር ፊልም፡-**

**የጉድ ሀገር መንገድ /ብስራት ተስፋ**

**ምርጥ የተማሪ አጭር ፊልም፡- መሐይማን /አማኑኤል ተሾመ**

**ምርጥ ተከታታይ ኮሜዲ ድራማ ፡- አስኳላ**

**ምርጥ ውርስ ትርጉም ድራማ፡- አደይ**

**ምርጥ ዶክመንተሪ፡-ባሌ ብሄራዊ ፓርክ /አዚዝ አህመድ**

**ምርጥ ውርስ ድራማ ተዋናይት፡- በእምነት ሙሉጌታ / አደይ**

**ምርጥ ውርስ ድራማ ተዋናይ፡- አስማየሁ ታደሰ / አጋፋሪ**

**ምርጥ የፊልም ሙዚቃ፡- የሱፍ አበባ**

**ምርጥ ስኮር፡- ረመጥ / ብሩክ አሰፋ**

**ምርጥ ሜካፕ፡- ተሚማ ሁሳላ / ረመጥ**

**ምርጥ ፊልም ፅሁፍ፡- ረመጥ / ዳንኤል በየነ**

**ምርጥ ቅንብር፡- የሱፍ አበባ /እስክንድር ተፈራ**

**ምርጥ ሲኒማቶግራፊ፡- የሱፍ አበባ / ዋለልኝ አደገ**

**ምርጥ ተስፋ የተጣለበት ተዋናይነት፡- ክሱት / እየሩሳሌም አሰፋ**

**ምርጥ ተስፋ የተጣለበት ተዋናይ፡- ፊናፍ / ብሩክ ግርማ**

**ምርጥ ረዳት ሴት ተዋናይት፡- የማር ውሃ / መስከረም አበራ**

**ምርጥ ረዳት ተዋናይ፡- ጥላዬ / እንግዳሰው ሀብቴ**

**ምርጥሴት ተዋናይት፡- ክሱት / ጠረፍ ካሳሁን**

**ምርጥ ወንድ ተዋናይ፡- ሄኖክ በሪሁን /ረመጥ**

**ምርጥ ዳይሬክተር፡- ረመጥ/ ዳንኤል በየነ**

**ምርጥ ፊልም፡- የሱፍ አበባ /ስገሰ ገነቱ**

**የህይወት ዘመን ተሸላሚ፡- አርቲስት ኪሮስ ኃይለስላሴ**

**የሔርሜላ አሸናፊ፡- ገነት ከበደ**

**አርአያ ሰብ ከያኒ፡- አርቲስት መሰረት መብራቴ**

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## ሰው ተኮር የረድኤት ተግባር

ሰላማዊት ውቤ

ባለፉት ሶስት አመታት እንደ አገር በተለይም ከሰሜኑ ጦርነት ጋርና ከሌሎች ፖለቲካዊ ችግሮች ጋር ተያይዞ በርካታ ግጭቶች ተከስተዋል። ይህንንም ተከትሎ በርካታ የህብረተሰብ ክፍሎች ለሞት፣ ስደትና መፈናቀል ተዳርገዋል። ቤት ንብረታቸውንም አጥተዋል፡፡ ታዲያ በዚህ ሁሉ ቀውስ መሃል እነዚህን ወገኖች ለመርዳት ሲሉ ራሳቸውን መስዋዕት የሚያደርጉና የግል ምቾታቸውን አሳልፈው የሚሰጡ የህብረተሰብ ክፍሎች በርካቶች ናቸው፡፡

ከነዚህ ውስጥ አንዷ ራሷን ለዚህ የተቀደሰ ዓላማ በመስጠት ሳሊተ ምህረት ቤተክርስቲያን አካባቢ የሚገኘውን ወገን ለወገን በጎ አድራጎት ልማት ድርጅት የተቀላቀለችው የሃያ አንድ ዓመቷ ወጣት አፀደ ሰማን ናት፡፡ ወጣቷ በሙያዋ ፋርማሲስት ስትሆን ወደ ሥራ ዓለም ከተሰማራች ሁለተኛ ዓመቷን ይዛለች፡፡ ተወልዳ ካደገችበት ሰሜን ጎንደር ዞን ጭልጋ ወረዳ መጥታ ነው ድርጅቱን በአባልነት ተቀላቅላ እያገዘች ያለችው፡፡

አፀደ በጎ አድራጎት ድርጅቱን የተቀላቀለችው በአንድ አጋጣሚ ነበር። ባህር ዳር ከተማ የምትኖረው አክስቷን ልትጠይቅ በሄደችበት አጋጣሚ ወደ ድርጅቱ ይዛት ሄደች። አክስት ወጣቷ በተቻላት አቅምም ድርጅቱን እንድትደግፈው መከረቻት፡፡ ወጣቷ ከዚህ በፊት ከጦርነትና ግጭት ጋር ተያይዞ ብዙ ተስፋ አስቆራጭ ሁኔታዎች ገጥመዋታል፡፡ በተለይ እሷ ትኖር በነበረችበት ቅማንት በሚባለው አካባቢ ረብሻ፤ ሁከትና ግርግር እንደነበር ታስታውሳለች፡፡

በዚህ ምክንያት ብዙዎች ቤታቸውና ንብረታቸው በእሳት እንደጋየም ታውቃለች። ብዙዎች ለሞት፤ ለስደት፤ ለረሀብና መፈናቀል ሲዳረጉም ተመልክታለች፡፡ ይህ ቅማንት ብቻ



ወጣት አፀደ ሰማን፣

ሳይሆን በማይካድራና ጦርነቱ በነበረባቸው አከባቢዎች ሁሉ የሚስተዋል ችግር እንደነበረም ትገልፃለች፡፡

ከዚህ አንፃር እነዚህን ወገኖች በመርዳት የተቀደሰ ዓላማ ውስጥ መሳተፍ ለወጣት አፀደ እጅግ አስፈላጊ ነበር፡፡ አዲስ አበባ ያለው ጽህፈት ቤት በመጣችበት አጋጣሚ ስለተቀደሰው ዓላማ የበለጠ ተረዳች፡፡ ወደ ጭልጋ ተመልሳ በሄደች በሦስት ወሯ ተመልሳ መጣችና ማህበሩን ተቀላቀለች፡፡

አሁን ላይ ድርጅቱ ምንም ዓይነት የራሱ ገቢ ስለሌለው ለድርጅቱ ገቢ ለማሰባሰብ ዝግጅት እያደረገች ትገኛለች፡፡ ገቢ ለማሰባሰብ የሚያስችል ድንኳን ለመትከል አንዲት ካሬ በ አንድ ሺ ብር እንዲገዛ ከማድረግ ባለፈ የሥራ እንቅስቃሴዎችን በመሸፈን የጉልበት እገዛ እያደረገችም ነው፡፡ ድንኳን ሲፈቀድ ደግሞ የእርዳታ ገንዘቡን ለማሰባሰብ በዝግጅት ላይ ትገኛለች፡፡

ድርጅቱን የማገዝ ሀሳብ ሰንቃ እዚህ አዲስ አበባ ከመጣች ወዲህ 3ሺ 500 ብር ቤት ተከራይታ የምትኖር መሆኗን የምትጠቁመው ወጣት አፀደ፤ ማህበሩን ለማጠናከርና ቤት ኪራይ መሸፈኛ የሚሆን ገቢ ለማሰባሰብ የተለያዩ ሥራዎችን እየሰራች እንደምትገኝ ትጠቅሳለች፡፡

ወላጆቿ አርሶ አደሮች መሆናቸውንና እነርሱ ባይማሩም እሷን ግን ማስተማራቸውንም ነው የምትገልፀው፡፡ ለራሳቸውና ከእርሷ በታች ላሉ እህትና ወንድሞቿ እንደማያንሱና ከእርሷ ምንም እንደማይጠብቁም ትናገራለች፡፡ ሙሉ የወጣትነት ጊዜዋንና ገንዘቧን ለድርጅቱ ለማዋል መወሰኗንም ታስረዳለች፡፡ ‹‹ሰውን ለመርዳት ሰው መሆን በቂ ነው›› የሚለውን መርህ ተከትለው ለወገን እየደረሱ ያሉ የህብረተሰብ ክፍሎችም ሆኑ ማህበራት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተበራከቱ መምጣታቸውንም ትናገራለች፡፡

እነዚህ ከየትኛውም ሀይማኖትም ሆነ የፖለቲካ ድርጅት ነፃ ሆነው የሚንቀሳቀሱ የተቀደሰ ዓላማ ያነገቡ ድርጅቶች በተለይ በሰሜኑ ጦርነትና ግጭት ጋር ተያይዞ የተፈናቀሉና እርዳታ የሚፈልጉ ዜጎችን ለመደገፍና ለመቋቋም ቁጥራቸው እየጨመረ መምጣቱንም ወጣት አፀደ ትናገራለች፡፡

የወገን ለወገን በጎ አድራጎት የልማት ድርጅት መሥራችና ሥራ አስኪያጅ አቶ ጌትነት እንዳለ በበኩላቸው፣ መቀመጫውን በአማራ ክልል ዋና ከተማ ባህር ዳር አድርጎ እንደ አገር በስፋት እንቅስቃሴ እያደረገ ይገኛል፡፡ በቤኒሻንጉል ጉምዝ አሶሳ፤ በአዲስ አበባ፤ በአፋር ሰመራ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት የከፈተም ከፍቷል፡፡ በሌሎቹ የአገሪቱ አካባቢዎች ተጨማሪ ቅርንጫፎችን ለመክፈትም እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን ለተጎዱ ወገኖች ድጋፍ ማድረግና አደረጃጀቱን ማጠናከር የሚያስችለውን ገቢ ያሰባስባል፡፡

ድርጅቱ በእሳቸውና በአንዲት እህት አማካኝነት በጦርነትና ከጦርነት ጋር በተያያዙ በሌሎች ምክንያቶች የተጎዱ፤ የተፈናቀሉና ከቀያቸው የተሰደዱ፣ ለርሃብ የተጋለጡና በመጠለያ እጦት የሚንገላቱ ወገኖችን ለመደገፍና ለማቋቋም ዓላማ አድርጎ ነሀሴ 23 ቀን 2014 ዓ.ም ተመስርቷል። ማህበሩ አምስት የቦርድ አመራር ያሉት ሲሆን ሦስቱ ወንዶች ሁለቱ ደግሞ ሴቶች ናቸው፡፡ በነዚህ አመራሮችና እና አንድ፤ አንድ እያሉ ድርጅቱን በተቀላቀሉት አባላት አማካኝነት በጉልበት፤ በዕውቀትና በገንዘብ እየተደገፈ አቅሙን በማጎልበት ላይ ይገኛል፡፡

አሁን ላይ ወደ ሥራ ለመግባትና ወገንን ለመደገፍ ያስችለው ዘንድ ድርጅቱ አደረጃጀቱን እያጠናከረ ይገኛል፡፡ ከቀበሌ፤ ወረዳ፤ ዞንና ከሌሎች አካላት ጋር ተቀናጅቶ የመስራት ፍላጎት አለው፡፡ ድርጅቱ የሚደግፈውም የተቸገሩ ወገኖችን ነው፡፡ ለዚህም ድርጅቱ ከወረዳ፤ ቀበሌና ዞን ጋር በመቀናጀት ትክክለኛ ተረጂ የሆኑትን ወገኖች የመለየት ስራ እየሰራ ይገኛል፡፡ ይህም ለዘላቂ ድጋፍ ያመቻል፡፡

# ዓለም አቀፍ

## የሰው ልጆች ቀደምቷ ሉሲ ቀጥ ብላ ትራመድ እንደነበር ተመራማሪዎች አስታወቁ

በጋዜጣው ሪፖርተር

ከ3.2 ሚሊዮን ዓመታት በፊት በምድር ላይ ትኖር የነበረችው የሰው ልጆች ቀደምቷ ሉሲ ቀጥ ብላ ትራመድ ነበር ሲሉ የካምብሪጅ ዩኒቨርሲቲ ተመራማሪዎች ገለጹ።

ቅሪተ አካሏ እአአ 1974 በኢትዮጵያ የተገኘው ሉሲ በምድር ላይ ሳለች እንቅስቃሴዋ እንዴት እንደነበረ ምርመራዎች ተደርገው ውጤቱ ከትናንት በስቲያ በሮያል ሶሳይቲ ኦፕን የሳይንስ ጆርናል ላይ ታትሟል። ተመራማሪዎች ታዲያ ሉሲ ቀጥ ብላ ከመራመዷ በተጨማሪ በዚህ ዘመን እንዳሉት የጦጣ ዝርያዎች በዛፎች ላይ መኖር ትችል እንደነበረ ቅሪተ አካሉን መርምረን ደርሰንበታል ብለዋል።

ይህም ማለት ሉሲ የነበራት የሰውነት አቋም በአሁኑ ወቅት ካለ ከየትኛው ፍጥረት ጋር



ተመሳሳይነት የለውም። የሰው ልጆች እግሮቻቸው ቀጥ ብለው ስለሚቆሙ ሚዛናቸውን ጠብቀው ይቆማሉ፤ የጦጣ ዝርያዎች ግን ሊቆሙ ቢሞክሩ እግሮቻቸው ሙሉ በሙሉ ተዘርግተው ቀጥ ብለው መቆም አይችሉም። በዚህም ምክንያት እጅ እና እግሮቻቸውን በጋራ በመጠቀም መንቀሳቀስን ይመር ጣሉ ይላሉ ተመራማሪዎች።

ሉሲ ግን ከሰው ልጆችም ሆነ አሁን ላይ ካሉት የጦጣ ዝርያዎች በመለየት በሁለት እግሯ መራመድ ትችላለች። እንዲሁም በዛፎች ላይ መኖር ትችላለች።

አውስትራሎፒቲከስ አፋረን ሲስ የሰው ዝርያ የምትመደበው ሉሲ 40 በመቶ የሚሆነው ቅሪተ አካሏ መገኘቱ ይታወሳል። በካምብሪጅ ዩኒቨርሲቲ ያሉ ተመራማሪዎች በቴክኖሎጂ እገዛ የታችኛው የሰውነት ክፍሏን ዲጂታል ሞዴል ሠርተዋል።

ተመራማሪዎቹ ሉሲ የጉልበት መገጣጠሚያዎቿን መዘርጋት ትችላለች ሲሉ ደምድመዋል። ይህም ሉሲ ቀጥ ብላ መቆም እንደምትችል እና ሳር የሚያድግበት ሜዳማ አካባቢ መኖር ትችል እንደነበር የሚያረጋግጥ ነው።

ሉሲ ቁመቷ አንድ ሜትር ገደማ ሲሆን፤ የአእምሮዋ መጠን ደግሞ አሁን ላይ በምድር ከሚኖረው የሰው ልጅ አእምሮ ሲሶውን ብቻ የሚያክል ሲሆን የፊቷ ቅርጽ ደግሞ ከጦጣ ዝርያ ጋር የሚመሳሰል ነው። አውስትራሎፒቲከስ አፋረንሲስ ዝርያዎች ላይ ምርመራ ማድረጉ የሰው ልጆች በሁለት እግር ቀጥ ብሎ መራመድ እንዴት እንደጀመሩ ምልከታ ይሰጣል ይላሉ ተማራማሪዎች።

## ፑቲን የዩክሬን የመልሶ ማጥቃት ዘመቻ ውጤት አልባ እየሆነ ነው አሉ

በጋዜጣው ሪፖርተር

የሩስያ ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን የዩክሬን የመልሶ ማጥቃት ዘመቻ ውጤት አልባ እየሆነ ነው አሉ።

ፕሬዚዳንቱ ለጦርነት ዘጋቢዎች ሲናገሩ ሩሲያ ላይ የተከፈተው ዘመቻ በዩክሬን ጦር ላይ ከፍተኛ ኪሳራ እያደረሰ ነው ብለዋል።

ፑቲን ምንም አይነት ማስረጃ ሳያቀርቡ ዩክሬን 160 ታንኮች ሲወድሙባት ሩስያ ያጣችው 54 ታንኮችን ብቻ ነው ብለዋል። ፑቲን ጨምረውም የዩክሬናውያን ወታደሮች እልቂት ከሩስያ ጋር ሲነጻጸር በ10 እጥፍ ይበልጣል ብለዋል።

ኪዬቭ “በየትኛውም ዘርፍ ውጤታማ አይደለችም” ብለዋል ፑቲን። ይህ የፑቲን አስተያየት በገለልተኛ ወገን የተረጋገጠ አይደለም። የዩክሬኑ ፕሬዚዳንት ቭሎድሚር ዜሌንስኪም ከፑቲን የተለየ አስተያየት ሰጥተዋል።

“ወደፊት እየገሰገስን ነው” ያሉት ዜሌንስኪ፤ የዩክሬንን አንድ ስንዝር መሬት “ከሰይጣናዊው የሩስያ ኃይል ነጻ እያወጡ ላሉ ዩክሬናውያን ወታደሮች ምስጋና ይድረስ” ብለዋል።

ዩክሬን በሩስያ ኃይሎች ላይ የመልሶ ማጥቃት ዘመቻ ከፍቻለሁ ካለች በኋላ በዶኔስክ እና ዛፖሬዢያ ጥቂት መንደሮችን ነጻ ማውጣቷን አስታውቃለች። ትናንት ማክሰኞ ቢቢሲ በምሥራቅ ዶኔስክ የዩክሬን ወታደሮች ከሩስያ ኃይል ነጻ ያወጡትን ስፍራ መጎብኘት ችሏል።

የሰሜን አትላንቲክ የጦር ቃል ኪዳን ድርጅት (ኔቶ) ዋና አዛዥ ጄንስ ስቶለተንበርግ ገና በመጀመሪያ ደረጃ ላይ ብንገኝም የሩስያ ወታደሮችን በማስወገድ ለውጦች እየመጡ ነው ብለዋል። “በትክክል የምናውቀው ነገር ዩክሬናውያኑ ብዙ መሬት ነጻ አወጡ ማለት በድርድር ጠረጴዛው ላይ የበላይነት ይኖራቸዋል” ሲሉ ዋና አዛዡ ለፕሬዚዳንት ጆ ባይደን በዋይት ሃውስ በነበራቸው ስብሰባ ተናግረዋል።

ቭላድሚር ፑቲን የዩክሬንን መልሶ ማጥቃት ዘመቻ በተመለከተ የሰጡት አስተያየት በአሜሪካ ባለስልጣናትም ውድቅ ሆነዋል። በስም ያልተጠቀሱ አንድ የአሜሪካ መንግሥት ከፍተኛ ባለስልጣን ሁኔታውን በተመለከተ ፑቲን የሰጡት አስተያየት ‘እውነት አይደለም’ ብለዋል።

ፑቲን በትናንቱ ንግግራቸው ዩክሬን በድንበር ዘለል ጥቃቶች ሩስያን ዒላማ ያደረገችባቸውን ጥቃቶች ለመመከት የጦር ኃላፊዎቻቸው የተሻለ ዝግጅት ማድረግ ይችሉ ነበር ሲሉ መከላከሉ ላይ ክፍተት መኖሩን አምነዋል። ከዚህ



በተጨማሪም ፑቲን ምንም እንኳ ከባለፈው ዓመት ወዲህ የጦር መሳሪያ ምርት ቢጨምረም ጦራቸው፤ “የተተኳሽ፣ የግንኙነት መሳሪያ፣ ድሮን እና የመሳሰሉት” እጥረት እንዳለበት አልካዱም።

# ስፖርት


## የለሜቻ ግርማ የዓለም የቤት ውስጥ ክብረወሰን ፀድቋል

ቦጋለ አበበ

ኢትዮጵያዊው ጀግና አትሌት ለሜቻ ግርማ ከወራት በፊት በፈረንሳይ ሌቪን የቤት ውስጥ ውድድር ያሻሻለው የሦስት ሺ ሜትር መሰናክል የዓለም ክብረወሰን ፀድቋል። ለሜቻ ለሃያ አምስት ዓመታት ሳይደፈር የቆየውን የርቀቱን የቤት ውስጥ የዓለም ክብረወሰን በ7:23.81 መስበሩ የሚታወስ ነው፡፡ የቀድሞው ክብረወሰን በኬንያዊው አትሌት ዳንኤል ኮመን እኤአ በ1998 ሃንጋሪ ቡዳቤስት ላይ 7:24.68 ሰዓት የተያዘ ነበር፡፡

በተለያዩ ውድድሮች የሚሰበሩ የዓለም ክብረወሰኖችን እውቅና ለመስጠት ወይም ለማፅደቅ የፀረ አበረታች ንጥረ ነገር ምርመራ ውጤት እስኪረጋገጥ ረዘም ያለ ጊዜ የሚወስድበት የዓለም አትሌቲክስም የለሜቻን የቤት ውስጥ የዓለም ክብረወሰን ከትናንት በስቲያ ማፅደቁን አስታውቋል።

ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ውጤታማ እየሆኑበት በሚገኘው የሦስት ሺ ሜትር መሰናክል ውድድር ትልቅ ትኩረት እያገኘ የመጣው ወጣቱ አትሌት ለሜቻ የርቀቱን የዓለም የቤት ውስጥ ክብረወሰን በገባው ቃል መሰረት ባለፈው አርብ በፈረንሳይ ፓሪስ ዳይመንድሊግ ውድድር መስበሩ ይታወቃል። እጅግ ስኬታማ የውድድር ዘመን እያሳለፈ የሚገኘው ይህ ድንቅ አትሌት በወራት ልዩነት ሁለት የዓለም ክብረወሰኖችን በመስበሩም




አድናቆት እየጎረፈለት ይገኛል፡፡

ለሜቻ የውድድር ዓመቱ አራተኛ የዳይመንድ ሊግ መዳረሻ በሆነችው ፓሪስ ባለፈው አርብ ያስመዘገበው የዓ ለም ክብረወሰን 7:52.11 ሲሆን ይህም ከቀድሞው ክብረወሰን በ1.52 ሰከንድ የተሻለ ሆናል። የቀድሞው ክብረወሰን በትውልደ ኬንያዊው የካታር አትሌት ሴይፍ ሳኤድ ሻሄን 7፡53፡63 በሆነ ሰዓት እኤአ 2004 ላይ የተመዘገበ ነበር።

በ2019 የዶሃ የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ላይ በርቀቱ ለኢትዮጵያ በታሪክ የመጀመሪያ የሆነ ውን የብር ሜዳሊያ ያስመ ዘገበው አትሌት ለሜቻ ግርማ ከዚያ በኋላ በተለያዩ መድረኮች ማንፀባረቁና ተጨማሪ ታሪክ መስራቱን ቀጥሏል። በቶኪዮ 2020 ኦሊምፒክም የርቀቱን የብር ሜዳሊያ በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ያስመዘገበ ሲሆን በተመሳሳይ ባለፈው የኦሪገን የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮናም ተመሳሳይ ድል አስመዝግቧል።

ወጣቱ አትሌት በርቀቱ ስኬታማ የሆነው ድንገት በታላላቅ ውድድሮች ብቅ ብሎ ቢሆንም ከዓመት ዓመት ብቃቱን እያሳደገ ዘንድሮ የተለየ አቅም መፍጠር ችሏል።

ይህም ከጥቂት ወራት በኋላ በቡዳፔስት በሚካሄደው የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ከወዲሁ ለወርቅ ሜዳሊያ እንዲታጭ አድርጎታል፡፡

ለሜቻ በፓሪስ የዓለም ክብረወሰን ከማሻሻሉ አስቀድሞ የገባውን ቃል በተግባር ማሳየቱ ብዙዎችን ያስገረመ ነበር፡፡ እሱም ከድሉ በኋላ ‹‹በውጤቱ ተደስቻለሁ፣ ከሶስት ቀናት አስቀድሞ ክብረወሰኑን እንደማሻሽል ስናገር ነበር፣ ወንድሜ አሰልጣኜም ጭምር ነውና ክብረወሰኑን በእጄ እንደማስገባ ያለውን እምነት ነገረኝ፣ እኔም አምኜው አሳካሁት›› ያለ ሲሆን ዘንድሮ የብቃቱ ጥግ ላይ እንደመገኘቱ ተጨማሪ ታሪኮችን ሊሰራ እንደሚችል ፍንጭ ሰጥቷል፡፡

ለሜቻ ልምምድ ሲያደርግ ጥሩ ስሜትና ጥሩ አቋም ላይ እንደነበር፣ በተጨማሪም በዕለቱ በስታዲየሙ በርካታ ተመልካቾች መመልከቱን ተናግሯል፡፡ ከዚህ ድል በኋላም በዘንድሮ የሃንጋሪያ ዓለም ቻምፒዮና በርቀቱ ለማሸነፍ እንደሚፈልግ አስረድቷል፡፡

የሦስት ሺ ሜትር የቀጥታና የመሰናክል ሩጫ ባለክብረወሰኑ የ22 ዓመቱ ለሜቻ፣ በቀጣይ በግል ውድድሮች፣ በዓለም ቻምፒዮና እንዲሁም በፓሪስ ኦሊምፒክ ከፍተኛ ግምት ካገኙ አትሌቶችም ቀዳሚው ነው፡፡